ከአውግቸው ተረፈ



ወይ ፍቅር ሕልም

እና ሌሎች አጫጭር ልብወለዶች

ወይ አዲስ አበባ ...

እና ሌሎች

አጫጭር ልብወለዶች

ከአውግቸው ተረፈ



ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፱

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ ቁጥር Tel. 112719
ፖስታ ሣ. ቁ. P. O. Box 30,933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
All Rights Reserved

የሽፋን ሥዕል — ሱታስ እማረ

ቦሌ ማተሚያ ቤት

ማ ው ጫ

ርዕስ ገጽ

1. ስንብት 5
2. ስኩላርሺፕ 21
3. አዲሱ ሕልም 43
4. ወይ አዲስ አበባ 81
5. የጴጥሮስ ውሳኔ 113

ስንብት

ድጉል አደባባይን ሻገር ይልና ፣ ሲኒማ አምፔር ፊት ለፊት የሚገኙትን መደዳ ሱቆች ዐልፎ ፣ አንድ ትልቅ የጌጣ ጌጥ መደብር አለ ። ሱቁ ያልያዘው የዕቃ ዐይነት የለም ። ንጉሤ እዚህ ሱቅ ውስጥ ተቀጥሮ ሲሠራ ዐሥር ዓመት ዐልፎታል ። የሱቁ ባለቤት አቶ ጠንክር በማሻሻጥ ችሎታው ይመኩበታል ። ግን የሰሞኑ ሁኔታው አቶ ጠንክርን አሳስቧቸዋል ፤ ፍትር እንደ ያዘው አይተዋል ፤ ልጅቷንም ያውቋታል ።

በንጉሤ አስተሳሰብ ፣ አበበች ለብዙ ሴቶች የሚበቃውን ውበት ለብቻዋ ይዛለች ። ሐር መሳዩ ጸጉሯ ከወገቧ ዐልፎ ዳሌዋ ጋ ይደርሳል ። ሞላ ሞላ ያሉት ጉንጮችዋ የበሰለ ብርቱካን ይመስላሉ ። ዐይኖቿ ፣ ጥርሶቿ ፣ ሽንጧ ፣ ዳሌዋ ፣ ባቷና የግር ጣቶቿ ታዋቂ ሠዓሊ ቀስ እያለ ፣ በጥንቃቄ የሠራቸው ይመስላሉ ። ፈገግታዋ ልብ ያነሆልላል ፤ አስተያየቷ ብርክ ያሲዛል ፤ ንጉሤ በዐይኑ ሙሉ ሊያያት አይደፍርም ። እንደ ምሽት ኮከብ የሚ ያበሩ ዐይኖቿን ሁሉ ይሸሻቸዋል ። እሷን ፊት ለፊት ከማየት ይልቅ ፣ አንገቱን ደፍቶ ወይም ዐይኖቹን ጨፍኖ ቢያስባት ይመ ርጣል ፤ ይተለዋልም ።

ንጉሤ ፣ አበበችን የሚያውቃት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ነው ። ወዳጅነታቸው ያዝ ለቀት እንደ መሆኑ ይገናኛሉ ፤ ይጠፋፋሉ ። የተገናኙለት በሐሳብ ሳይግባቡ ይቀሩና ተጣልተው ይለያያሉ ። ታዲያ ፣ ሁለቱም እልኸኞች ስለሆኑ ፣ እንዳቸው መሸነፍ አቅቷ ቸው ነው እንጂ በጣም ይዋደዳሉ ። ቁርጥ ያለ ጠብ ተጣልተው ለመለያየት ያህል አይጨክኑም ።

ንጉሤ ፣ ከሷ ከተለየበት ቅጽበት ጀምሮ ጭንቅ ይይዘዋል ። ስለሷ ማሰብ ነው ፤ መናደድ ነው ። አበበችም እንደሱ ትናደዳ ለች ። ወዳው ፣ ፈልጋው ስትሔድ ላንዲት ሴት ማሳየት የነበረበትን፣ ፍቅርን ፣ ትሕትናን ፣ ፈገግታን ይነፍጋታል ። እሷን ሲያይ እናቱ ገበያ እንደ ሔደችበት ሕፃን ጠባዩ ይጠፋል ። አፍንጫውን ነፍቶ እንደ ተራበ አንበሳ ዐሥሬ እያዛጋ ይንጎራደዳል ። 'ሳናግ

ራት አላናግራት' እያለ ሲጨነቅ ይቆያል ። እንደበቱ በስንት መከራ ሲፈታለት የሚናገረውም ያላሰበውን ነው ። በነገር ጠቅ ያደር ጋታል ። አኩርፉ ትሔዳለች ።

በነጋታው ፣ በሳምንቱ ወይም በሌላ ቀን ትመጣለች ። እግሯ ላይ ወድቆ ይቅርታ ሊጠይቃት ያስባል ። ያያታል ፤ ታየዋለች ፤ ቀድማ አንዲት ቃል ከተናገረችማ እግሯ ላይ ወድቆ ፣ 'ይቅርታ እጠይቃታለሁ' ብሎ ይጠብቃታል ። ቀድሞ 'ይቅርታ ከጠየቀኝ ሁሉንም ነገር ለመርሳት ዝግጁ ነኝ' ብላ ትወስናለች ፣ በልቧ ። ይተያያሉ ። ማን ቀድሞ ያናግር ! እሱ ወይስ እሷ ?

ንጉሤ ፣ ገበያተኞችን በማስተናገድ ሥራ የበዛበት መስሎ ይታያል ። እሷም በሰፊው ሱቅ ውስጥ ዕቃ የምትመርጥ ትመስላለች ። ትዟዟራለች ። ቢሆንም እየተሰራረቁ ይተያያሉ ።

እበበችና ንጉሤ የተዋወቁት ፣ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሳለች ነው ። መነን ትምህርት ቤት እንደምትማር ያወቀ በደረበችው ደማቅ ሰማያዊ ሹራብ ነበር ። ከትውውቁ በኋላ ያንን ሹራብ የለበሱ ተማሪዎች ሲያይ ልቡ ይደነግጥበታል ። በተለይ እሷ በጠፋችበት ሰሞን በር ላይ ቆሞ ፣ ወደ ትምህርት ቤት የሚ ሔዱትንና ከትምህርት ቤት የሚመለሱትን ተማሪዎች ማየት አይ ለለቸውም ። እንደ ተዋወቁ ሰሞን ቶሎ ቶሎ ይገናኙ ነበር ። ሱቁ ሲዘጋ ቶሎ ወደ ቀጠሮው ቦታ ይሮጣል ። ያኔ እበበች 'ወደ ሱቅ አልመጣም' እያለች ታስቸግረው ነበር ። ሲኒማ አምፒር የቀጠሮ ቦታቸው ሆነ ። ያኔ ንጉሤ ለሱቁ አዲስ በመሆኑ ያቶ ጠንክርንና የባለቤታቸውን ጠባይም አያውቀው ስለ ነበር ፣ ሱቅ ባለመምጣቷ ደስተኛ ሆነ ። ቀጠሮ አፍርሳ ሲጠፋ ፣ መስኩቱ አጠገብ ትቆምና እስኪያያት ድረስ ዕቃ የምትመርጥ መስላ ትጠብቀዋለች ። ዋጋ የሚነግር መስሎ በቀጠሮው ቀን ሹክ ይላትና ተመልሶ ይገባል ።

አንድ ቀን ንጉሤ ፣ ባንኮኒውን ተደግፎ ፍዝገዝ ብሎ ወደ ውጭ ሲያይ ፣ አቶ ጠንክር አዩትና ፣ "ና ወዲህ" አሉት ። ፈጠን ብሎ ሔደ ። ገበያተኛ አልነበረም ። "ምን ያፈዝሃል? ሸሚዝ ሲጠይቁህ ሹራብ ፣ ኮት ሲጠይቁህ ቀሚስ ማሳየት ከጀመርክ ውለህ አድረሃል ። ከልጅቱዋ ጋር ተጣላችሁ?"

"ከየቱዋ ልጅ ጋር?" ሲል መልሶ ጠየቃቸው ።

"የማላውቅ እንዳይመስልህ ። ሁሉንም ዐውቃለሁ ። ሌላ ነገር ደርቦብህ እንደሆነ ብዬ ነው እንጂ! የማውቀውን ነገር ልት ሸፍጠኝ ነውን?"

"ለውየው ቆቅ ናቸው ። ያወቅኳቸው ሲመስለኝ ለካስ ምንም አላወቅኳቸው ። እንዲህ ከሆነማ ምን አስደበቀኝ" ብሎ አሰበ ። ላቶ ጠንክር የሰጣቸው መልስ ግን ይሸኛው ነው ።

"ጌታዬ ምንም ነገር አልደረሰብኝም ። እሷው ናት ጤና የነሣችኝ ፤ 'ሒጂ' ስላት ትመጣለች ፤ 'ነይ' ስላት ትሔዳለች ። ቋንቋችን ሁሉ የባቢሎን ቋንቋ ሆኖብን ተቸግረናል" አለ ንጉሤ ። እንዴ ቀጣሪ ሳይሆን ፣ እንደ አባት ስላሰቡለት ልቡ በርኅራኄ ተነክቶ ፣ ከሳቸው የሚደብቀው ምንም ነገር አለመኖሩን ማሳየት ፈለገ ።

"ና ቁጭ በል አጠገቤ" አሉ አቶ ጠንክር የእንግዳ መቀመጫ ወንበር ላይ እየተቀመጡ ፣ "ና ተቀመጥ ። እሁን መቸም ገበያተኛ ስለሌለ እንዴ ልብ ማውራት እንችላለን ። ምንም ነገር ሳትደብቅ ንገረኝ ። የምታገባት ከሆነ እንዴ አባትህ ሆኜ እድር ሃለሁ ። ካልሆነም መፍትሔውን እፈልግልሃለሁ ።"

አባባላቸው እውነተኛ መሆኑን ንጉሤ አልተጠራጠረም ። እንኳን እሱን ፣ በታማኝነት ካሥር ዓመት በላይ ያገለገላቸው ታማኝ ሠራተኛቸውን ፣ ለሌላም መልካም ነገር ከማድረግ እንዴ ማይቆጠቡ ያውቃል ።

"ምኑን ልንገርዎ?" አለ ንጉሤ ፣ ከየት እንደሚጀምር ግራ ገብቶት ።

"እንዴት እንዴ ተዋወቃችሁ? ትወዳት እንደሆን ፍቅራችሁን ፣ ትጠላት እንደሆን ጥላቸሁን ፣ ትቀናኑ እንደሆን ቅናታችሁን ፣ አንድ ባንድ ንገረኝ ።"

"ሳውቃት ብዙ ጊዜ ሆኖኛል ። ግን የማውቃት አዳም ሔዋንን ባወቀበት መንገድ ሳይሆን ውጫዊ ዕውቀት ነው ። ያወ

ትኋት እዚህ ቡቅ ውስጥ ዕቃ ልትገዛ መጥታ ነው ። ደጋግማ መጣች ። ብዙ ዕቃም ገዛች ። ግን እኔ ከደንበኞቻችን እንደ እንዱ ስቄጥራት እቢ አልቁጠርም አለች ። ሴሎች ደንበኞቻችን የሚፈልጉትን ዕቃ ከገዙ በኋላ ፣ እመስግነው ወይም ተራግመው ቶሎ ይሔዳሉ ። እቢ ግን ዕቃ ከገዛች በኋላ ቶሎ አትሔድም ። ገበያተኛ ሲበዛ እየዘረች ትመርጣለች ። ገበያተኛ ሳይኖር ትመጣና ታወራኛለች ።

"ታዲያ ስታወራኝ ይጨንቀኛል ። "ሱቁ ሲዘጋ ሲኒማ እም ፔር በር ላይ ጠብቂኝ" አላታለሁ ። እሺ ብላ ትሔዳለች ። እንገና ኛለን ። ምርጥ ልብሶቼን እለብስና ፣ መነጽር አደርግና ፣ ባርኔጣ አደርግና ፣ የቁልፍ መያዣ ሐብሴን ጣቴ ላይ እየጠመጠምኩና እየፈታሁ እሔዳለሁ ። ስታየኝ ምንም የተለወጥኩ አይመስላትም። ሱቅ ውስጥ የምለብሰውን የሥራ ካፖርት የለበስኩ ይመስል ያለ ምንም መገረም ትቀበለኛለች ። ስስታም ወይም ገብጋባ እንዳት ለኝ ትልቅ ሆቴል ወስጂ ያለኝን አራግፌ እጋብዛታለሁ ። እቢ ግን አምስት ሣንቲም ያወጣሁም አይመስላት ።

"የማደርግላት ነገር ሁሉ ኢምንት ነው ። የማወራት ሁሉ ፍሬ ከርስኪ ነው ። ሣቂ ለቅሶ ነው ። ዝም ብዬ ጐኗ ስቀ መጥ ፣ 'ምን ሆንክ? ተጫወት እንጂ?' ትለኛለች ። ያስታታል ወይም ያስገርማታል ብዬ ያሰብኩትን ማውራት ጀምሬ ገና መኸል ሳላደርሰው ፣ 'ታዲያስ ፍጻሜው ምንድን ነው? ንገረኝ!' ትለኛለች ።

"አይ ምንም ፍጻሜ የለው" አላታለሁ ድንግር ይለኝና ።

"እንደበትህ የተሳሰረብህ ትመስላለህ ። ምን ሆንክ?' ብላ ትጠይቀኛለች ። እያወቀች — እንዳላወቀች ፣ ስታብለኝ ስታባብ ለኝ ። 'አይ... አ... ምንም አልሆንኩ' አላታለሁ ። አንዳች ከመሆን ዐልፎ ላብ እንደ ውሃ እየተቀዳኝ ፣ የፊቴን ላብ በመሐረብ እየጠረግሁ ። መሐረቤ መራሱን ስታይ የራሷን መሐረብ እንድ ጠቀምበት ትሰጠኛለች ። አይሆንም ብልም በጂ አትልም ።"

"ከቢ ጋር ስትሆን ትደነግጣለህ ማለት ነው?"

"በጣም እንጂ! ወላ እንደ ያዘው ሰው ሰውነቴ ይርገፈገ ፋል ፣ የሆነ ነገር ውርር ያደርገኛል ። አፌ ይተሳሰራል ።"

"እንደምትወዳት ነግረሃታል?" አሉና ጠየቁት አቶ ጠን ክር ። እጮኛው የሆነች መስኳቸው ነበር ። እየፈጩ ጥሬ መሆ ኑን ከንጭጫ እንደበት ሲሰሙ የማይሆን ሆነባቸው ።

"እንደምወዳትማ ነግራአታለሁ ። ቀን በውኔ ፣ ሴት በሕ ልሜ እንደምትመጣብኝ ከነገርኳት በኋላ ነው ቀስ በቀስ መጥ ፋት የጀመረች ።"

"ከሌላ ወንድ ጋር እየሔደች ይሆናል ፣ ማለት ሌላ ወንድ ይኖራት ይሆናል ፣ የምትወደው ። ለመሆኑ እንደምትወድህ ነግ ራሃለች?"

"እንደምትወደኝ?...እ..." ትወደው እትወደው እንደሆነ ለማወቅ በሰቂለ ሕሊና ለማሰብ ሞከረ ። በሙከራው ሊደርስበት እንዳልቻለ ሲገነዘብ ፣ "ትወደኝ እትወደኝ እንደሆነ ለማወቅ አል ችልም ። ትመጣለች ብየ ሳምንት ሙሉ ስጠብቃት ሰንብቼ ፣ ስት ቀር ፣ ወይም በስንት ጥበቃ ቀጠሮ አሳልፋ ስትመጣ ፣ እትወዴ ኝም ብዬ እደመድማለሁ ። እቢን በማሰብ ብቻ ሕሊናየ ይረበ ሻል ። አካሌም አእምሮዬም ይደክማል ። እቅበጠበጣለሁ ። እን ጫነጫለሁ ። ብትወደኝ እንዲህ ታደርገኛለች?"

ጥያቄው ለራሱ ይሁን ለጌታው አያስታውቅም ። አቶ ጠንክር ግን፣ እሳቸውን የጠየቃቸው ስለ መሰላቸው መልስ ሰጡት።

"በኛም ዕድሜ በወዳጆች መካከል ቲያትር መሰል ጨዋታ ይካሔድ ነበር ። እንዲት ሴት አፍቃሪዋን ወንድ ለሳምንት ትቀ ጥረዋለች ። የምትመጣበትን እርግጠኛ ሰዓትም እትነግረውም ። ቤት ሰበቼ ወጣ ሲሉ ቹልክ ብየ እመጣለሁ ስለምትለው ፣ ዉት ቁርሱን በልቶ ወዲያ ወዲህ ሳይል ሲጠብቃት ይውላል ። የምሳ ሰዓት ቢያርሰም እይሔድም ። የመጣች እንደሆነ አጥታው እንዳ ትመለስ ይፈራል ። ሴቶች ይህን ዘዴ የሚጠቀሙ ምን ያህል እንደሚወዱ ለማወቅ ነው ። ወንድየው መምጣትና አለመምጣ ቱን ለማወቅ ተደብቀው ያዩታል ። ወይም ኩታ ተከናንበው ማዩ

ግዶውን ያልፋሉ ። 'ቀረች—መጣች' እያለ ፍቅረኛውን በናፍቆት የሚጠብቅ ወንድ ስለሷ ብዙ ባሰበ ቁጥር ፣ ፍቅሩ እየጨመረ ይሔዳል ብለው ያስባሉ ወይም ያምናሉ ። ያንተይቱም እንዲያ ዐይነቱን ጨዋታ እየተጫወተች ይሆናል ፤ ብዙ ናፍቀሃት ስትመጣልህ ከሷ መለየት ሞት መስሎ ይታይሃል ።"

"እንዲህ ዐይነቱን ጨዋታ እኔ አልፈልገውም ። መምጣት—መምጣት ነው ። መቅረት — መቅረት ነው ። ብቅ ጥልቅ ምን ያደርጋል ? እወድሃለሁ ወይም አልወድህም ብሎ ቁርጡን መንገር ነው ። እኔ የምፈልገው ግልጽ ነገር ነው ጌታዮ" አለ ንጉሤ ጌታውን ቀና ብሎ እያየ ።

"ታዲያ ለምን እትነግራትም ? ልክ አሁን ለኔ እንደ ነገርከኝ አደርገህ ለሷ ንገራት ። እምቢ ካለች የምትሆንህን ትፈልጋለህ ። የምትሆንህን ካጣህ ያመቴን ልጅ ታገባለህ ። ዓመቴ የኔ ሠራተኛ ናት ። ቁም ነገረኛ ልጅ አለች ፣ ለባል የደረሰች ። ብታያት እንደምትወዳት ርግጠኛ ነኝ ።"

"ይቀልዳሉ እንዴ ጌታዬ ?" አለ ንጉሤ ። ለብዙ ዓመታት አብረው ስለ ኖሩ ፣ ጌታና አሽከር እኩል መቀላለድ ለምደዋል። በቁም ነገር መኻል ቀልድ ሲያስገቡ ግን ሰምታቸው አያውቅም።

"መቀለዴ አይደለም ንጉሤ ። የምሬን ነው ። ከሷ ጋር ሳይህ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል ። ስትጃጃል በማየት ተናደድኩ ። እነግርሃለሁ ብዬ እያሰብኩ ፣ በሥራ ብዛት እየተረሳኝ ነው ። ላንተ እንደ ማትሆንህ ሳልገምት የቀረሁ አይመስለኝም ። ርሷ ቢጠ ናት ። ባለባበሷ ታስታውቃለች ። እንተ የፍቅር ጣኦት ስላደረግሃት አልታይህ ብሎ ነው እንጂ ብዙ ቦታ ከወንድ ጋር አያታለሁ ። ለምን እንደ ተጠጋችህ ግን ገርሞኛል ። ገንዘብህን ለማጫረስ ነው እንዳልል ደሞዝህ ከቤት ኪራይና ከቀለብ አያልፍም ። ይህን ግማታም ሜማ መቀየር አቅቶህ ቤቱን ጭምር ስታገማው ብዙ ጊዜህ ነው ። ትወድሃለች እንዳልል የሥቃይህ ምንጭ መሆኗን እየነገርከኝ ነው ። ግራ የሆነች ፍጥረት ናት ! አንተም ግራ የሆንክ ፍጥረት ነህ!"

"ከቤተሰብሽ ጋር አስተዋውቂኝ ብዬ ብጠይቃት ዛሬ—'ነገ ትላለች ። እኔ ለሷ የማንሳት ከሆነ አታስተዋውቀኝ ይቅር ። እኩያ ነን ካለች ታስተዋውቀኝና ቀለበቱን የዛሬ ሳምንት እናድርገው ፤ ካልሆነ...ወይስ በቤተ ሰቦቿ ታፍራለች ልበል?"

"አንተን ልጠይቅህ እንጂ?" አሉ አቶ ጠንክር ።

የንጉሤን ፊት ሲያጠኑ ቆይተው እንደገና ቀጠሉ ።

"የምታፍር ባንተ ይሁን ፣ ወይም በቤተሰቦቿ አጣርተህ ማወቅ የነበረብህ አንተ ነህ ። ለዛሬ ዘመን ሴቶች ይህን ያህል ክብር መስጠትህ እንዴ ወንጀለኛ ያስቆጥርሃል ። ዛሬ ጊዜ ፣ እሁን፣ ባንዲት የቤት እመቤትና ዶሮ ማነቂያ ባለች ሽርሙጣ መካከል ምን ልዩነት አለ? ሁለቱም ያው ናቸው ። የልጅ አባት ተብለህ ፣ ልጅ እንዴ ጫጩት እያስቀፈቀፍክ ለመኖር አምርህ ካልሆነ በቀር ፣ ላንተ ዕጮኛ ወይም ፍቅረኛ ምን ሊያደርግልህ ነው? ደሞዝህ ለጫማ ሊሆናት ነው ወይስ ለሽቱ? ለኬክ ሊሆናት ነው ወይስ ለዳቦ? ይልቅ ዐርፈህ ብትማር ይሻልሃል ። ደሞዝ በተተበልክ ቁን የቤት ኪራይህንና የቀለብህን ሒሳብ ግሮን ውስጥ ቅበርና ቀሪውን ይዘህ ወዴ ዶሮ ማነቂያ ፣ ቢሻህ ጣሊያን ሰፈር ብቅ በል ። እንቅልፍህን ሳታጣና ብዙ ሳትጃጃል ፍላጎትህን እሚልተህ ትመለሳለህ ። ሁላችንም እዚህ የደረስን እንተ ከነበርክበት ተነሥተን ነው ። ሁለተኛ ስትተክዝ ወይም ስታስብ ፣ ወይም ስትንገላጀጅ ባይህ ከሥራ መባረርህ ነው ። በገቢያተኞች ፊት ፈላስፋ መስለህ እንድትታይ አልፈልግም ። ሹራብ ሲጠይቁህ ጀኬት ስትሰጥም እንዳላይህ ። በል ተነሥና አሁን የገቡትን ሰዎች ምን እንደሚፈልጉ ጠይቃቸው" ብለውት ከሱቅ ወጣ አሉ ።

ያቶ ጠንክር ሠራተኞች ፣ ጌትዮው ስለ ደሞዝ የሚያነጋግሩት መስሏቸው የሚሉትን ለመስማት ይቁነጠነጣሉ ። ሁሉንም ነገር ባይሆንም ከሚያወሩት በከፊል የሰማች ገንዘብ ተቀባይዋ አስቴር ነች ። አጠገቧ ቢቀመጡም ንግግራቸው በደንብ አልተሰማትም። ወዲያው አቶ ጠንክር እንዴ ወጡ ተሽቀዳድማ ጠራትው ፣ ያመለጣትን ማማሽ ወሬ ለማጣላት ። ሴሎችም ወሬው እንዳያ መልጣቸው ተሰበሰቡ ። አልማዝ ፣ ንጉሤን ጥየቃ በመጣች ቁጥር

ልጃገረድ ናት፣ ልጃገረድ አይደለችም' እያሉ ሲንሾካሾኩ ሰምታቸዋል ። ግን አስቴር እስከዚያች ቀን ድረስ ሰነገሩ እንግዳ ባትሆንም ፣ ክብደት ሰጥታው አታውቅም ነበር ። አቶ ጠንክር እድርሃለው ሲሉት ከሰማች በኋላ ፣ ነገሩን በጥልቅ የማወቅ ምኞት አደረባት ። ያ ምኞት በሩብ ሰዓት ውስጥ ተወንሶ ሆዷ ውስጥ የሚላወስ የዘጠኝ ወር ሽል ሆነ ።

'ለምን አታገባትም?' ብላ ጠየቀችው አስቴር ፣ ንጉሤ ሌሎች ጥያቄዎቿን በየተራ ከመለሰላት በኋላ ።

"ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ሳትደርስ አላገባትም።"

"እስከዚያው ድረስ ለምን በወዳጅነት አትቆዩም?"

"ታረግዛለች ብዬ ፈራሁ ።"

"ብታረግዝ ምንድን ነው? በመድኃኒት ታስወርደዋለች ።"

"መድኃኒቱ አታጥሎ ፣ ለብልቦ የገደላትስ እንደሁ?"

"በነፍስ ገዳይነት እንዳትያዝ ፈርተህ ነው?"

"የሕሊና ወቀሳ ፈርቼ ነው ። እሷ ብትሞት የውስጥ ሰላሜ ከሷ ጋር ይሞትብኛል!"

"እንግዲያውማ ተዋት" አለች አስቴር በቁጣ ።

"እንዴት አድርጌ ልተዋት ፣ መቻል ያቃተኝ እሱ አይደል? መተው እንዴት እችላለሁ? ቀድሞ ነገር መቸ በራሴ አዛለሁ? አዛገር እሷ ናት ። ስትፈልግ ትመጣለች ። ሳትፈልግ ትቀራለች ። እንደ ጨረቃ ከተወለደች በኋላ ፣ በወሩ መጨረሻ ላይ መልሳ ትሞታለች ። ማን ከልካይ አለባት?"

"ግራ የሆንክ ፍጥረት ነህ!" አለች አስቴር አሁንም በቁጣ ። በጥፊ በይው በይው የሚል ስሜት ከውስጥዋ ገፋፋት ፣ ግን አልመታችውም ። "ይህን ያህል ከወደድካትማ ተዋት ቢለሀም አትተዋት ማለት ነው ። ልብህ ውስጥ ዙፋን ዘርግታለች!"

"በቂ ምክንያት ካገኘው አተዋታለው ። እንድጠላት የሚያደርገኝ አጋጣሚ ወይም ምክንያት ስፈልግ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል ። ለጠብ መነሻ ይሆነኛል ብዬ ስንትና ስንት ሴሊቶች ያለ እንቅልፍ አሳልፈ ፣ ያፈለቅኩትን ዘይ ባንድ ፈገግታ ገደል ትከተዋለች ። በቂም በተል ያጠጠርኩትን ልቤን እንደ ቅቤ ታቀልጠዋለች ። በውስጤ የታመቀውን የሐሳብ ትግል ያላየ ሰው ላይ ላዩን በማየት ብቻ እንደ ደካማ ፣ እንደ ጅል ይቁጥረኛል" አለ ንጉሤ ንቀትና ጥላቻ የተዳፈነበትን ያስቴርን ፊት ሲያነብ ሰውነቱ በቁጣ እየጋለ ።

"እባክህ ጋሼ የተናገሩት እውነታቸውን ነው ። እንተ ጂል ሆነህ ነው እንጂ ለዛሬ ዘመን ሴት ይህን ያህል ልምምጥ አያስፈልግም ። የቤት እመቤቶችና ሸርሙጦች ፣ ልጃገረዶችና የቢሮ ሠራተኞች ፣ 'እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ' እያሉ ፒያሳና ለገሐርን ከዳር ዳር በሚያስቡበት ዘመን ፣ ካንዲት ሴት ጋር የሙጥኝ ማለት ካምስት መቶ ዓመት በፊት የቀረ ፍልስፍና ነው" አለች አስቴር ፣ ከቁጣዋ በረድ ስትል ምክር ለበስ አስተያየት እየለገሰችው ።

አስቴር ባለ ትዳር ፣ የልጆች እናት ናት ። እንደ ሌሎች ሴቶች ለብሳ መታየት የምትፈልግ ፣ ግን ደግሞ ዐቅሟ ባለ መፍቀዱ ልብስ እንደ ልብ ለመቀያየር ያልታደለች ፣ ከብዙ ወንዶች ቀጠሮ የምትቀበል ፣ ግን ደግሞ ሱቅ ውስጥ ታስራ በመዋሏ ካንዱም ጋር ለመውጣት ዕድል ያልገጠማት ሴት ናት ።

"ተይ አስቴር! ባለትዳር ሆነሽ እንዲህ አትናገሪ ፤ ደግሞም ፍቅር ይዞሽ ያውቅ ይሆናል ። ባይዝሽ አታግቢም ነበር" ብሎ ወደ ባንኩው ሲያመራ አስቴር ዝግ ባለ ድምፅ እንዲህ አለች ።

"ድንቄም ፍቅር! ድንቄም ፍቅር !"

የዛንለት ማታ ንጉሤና አበበች ፣ ሲኒማ አምፒር በር ለመገናኘት ቀጠሮ ነበራቸው ። ማታውኑ ቁርጥ ውሳኔ ለመድረስ በልቡ ማለ ። ሱቅ ውስጥ ግን ላንዳቸውም አልተናገረ ፣ ድንገት ቢከሽፍበት ማላገጫ እንዳያደርጉት ሰለ ፈራ ። ከተሳካለትና ቁርጡ ከታወቀ ግን ጉራውን ሊነሰንስባቸው ዝቷል ። ዛቻውም በልቡ ውስጥ ነው ።

ባንኮኒዉን ተደግፎ ገበያተኛ እየተጠባበቀ በሐሳብ ወደ ሰማይ መጠቀ ። እንደ ወፍም በረረ ። 'በቃ! ከዛሬ ጀምሮ የሚ ሆንሽን ፈልጊ' እላታለሁ ። የሷንም የኔንም ዕድል እንድታበላሽ አልፈቅድላትም ። ምናልባት በጉጕት የምትጠብቀው አንድ ነገር ይኖር ይሆናል ። እሱም የወላጆቿን ሞት ይሆን ይሆናል ። ያ ሞትም ውርስ ያስገኝላት ይሆናል ። ነገሩን በምሥጢር ይዛ ትቆይና ውርሱን እጅ ስታደርግ ያኔውኑ ቤትና መኪና ገዝታ 'እንጋባ' ትለኝ ይሆናል ። ወይም አንድ የምትወደው ዕጮኛ ይኖራት ይሆናል ። በመምጣቱ ወይም በመቅረቱ እርግጠኛ አይደለችም ። ስለዚህ እኔን ተጠባባቂ ማድረጓ ነው ። ዕጮኛዋ ከቀረ እኔን ታገባኛለች ። ከመጣም "ዞር በል ከፊቴ" ትለኛለች ። እስከ ዚያው ግን በጣም አታርቀኝም ። በጣምም አታቀርበኝም ። እንዲ ያው በድርበቡ በቅናት አለንጋ ሾጥ እያደረገች ልታስጠብቀኝ ትፈልጋለች ። በቅናት አባክና ልትገድለኝ ማለት ! አይደረግም ። እ...ቢደረግስ! ለመሆኑ እሷን ብተዋት ምን እሆናለሁ? እሞት ይሆን? ሞትማ ቀላል ነው ። የባሰው ነገር ጭንቀቱ ነው ። ሌት ተቀን መባነኑ... ደስ የማይል ነገር መስማቱ... ከሷ በቀር የሚ ወደደው ነገር ሁሉ መጠላቱ... መሰልቸቱ... ጠባይ መክፋቱ... በቃ ዛሬ ማታ የመጨረሻችን ይሆናል ። ወይ እንቀራረባለን ፤ ወይ እንራራቃለን ፤ ኦፋ !! ትልቅ ዳገት እንደ ወጣሁ ሁሉ ደካከ መኝ' አለና በረገሮሙ እያዛጋ የደረበውን ሽርጥ አወለቀው ። ሰውነቱም ፣ አእምሮዉም ዛለ ።

የሱቁ ሠራተኞች በመቆርቆር ስሜት የሚያቀርቡለትን ሐሳብ እንዳልተቀበላቸው ሲያዩ ፣ ሁሉም 'እኛን ምን አገባን?' ብለው ተዉት ። ተሾመ ግን እንደ ሌሎቹ ፣ 'ምን አገባኝ' ብሎ አልተወውም ። በሱቅ ውስጥ አብረው በመሥራታቸው ብቻ ሳይሆን ፣ የቅርብ ጓደኛዉና ምሥጢረኛዉ በመሆኑ ፣ ችግሩን አብሮ መካፈል እንዳለበት ተሰማው ። በዚሁም ላይ ከንጉሤ ጋር አንድ ቤት ነው የሚኖሩ ። የሁለቱን ፍቅር ገና ከጅምሩ ያውቀዋል ። ማታ ማታ አልጋቸው ላይ ተጋድመው የሚያወሩት የሁለቱን ፍቅር ነው ። በተለይ ያንድ ቀን ድርጊቱ ተሾመን ሁሌ ያስቀዋል ።

'አበበች ሌላ ፍቅረኛ አላት ። ከወንድ ጋር ስትማግጥ ነው የምትውል' ብሎ ተሾመ ለንጉሤ ደጋግሞ ስለ ነገረው ፣ ይህንኑ ለማጣራት አንድ ቀን ባለ ሱቁን አስፈቅዶ ቀደም ብሎ ይወጣል ።

የፀሐይ መነጽር አድርጎ ፣ ትልቅ ባርኔጣ ደፍቶ መጀመሪያ ሴቶች የሚገቡባቸውን ኬክ ቤቶችና 'ሚኒ ባሮች' ተዘዋውሮ ያያል ። ያጣታል ፤ ከዚያ ፒያሳ ውስጥ መዘዋወሩን ይቀጥላል ። መንገዱ ሰው በሰው ሆኗል ። ግፊያው ሌላ ነው ። ከፊት ለፊት እራት አምስት ወጣቶች እጅ ለእጅ ተያይዘው ይመጣሉ ። ከወዲህ አምስት ስድስት ልጃገረዶች መንገዱን ሞልተው ብቅ ይላሉ ። እጅ ለእጅ እንደ ተያያዙ ለመተላለፍ በሚደረገው እሽቅድድም የድብብቆሽ ጨዋታ የመሰለ ትርምስ ይፈጠራል ። ንጉሤ ፣ ለፒያሳ ባይተዋር ባይሆንም ፣ ሱቅ ውስጥ ቆሞ ሲያየው ምንም አይመስለው የነበረው መንገደኛ ፣ ያለ ቅጥ ተጋፊ ሆነበት ። አበበችን የመሰለች ሴት ያየ መስሎት ፣ እሷን እሷን እያየ ሲሔድ ካንዱ ወይም ካንዷ ጋር ይጋጫል ።

ከአበበች ሌላ ሴት ያለ አይመስለውም ነበር ። የፒያሳን ቆንጆዎች ሲያይ ግን ፣ እማያውቀው አገር ውስጥ የገባ መሰለው ። እይታው ሁሉ አዲስ ሆነበት ። አበበችን የምትመስል ቆንጆ ያለ አይመስለውም ነበር ። ግን የሚበልጡ አየ ። ቢሆንም አምኖ መቀበል አልሆነለትም ። ሕሊናው ሞገተው ። በትርምሱ መኻል ወደ ግራና ወደ ቀኝ እየሸሸ ፣ አንዳንዴም መኻል ለመኻል እየዋኘ ሲጋጭ አምሽቶ ወደ ቤቱ ሔደ ። ወዲያው ያየውን ሁሉ ረሳው ። በሕልም ያየው መሰለው ። ከሴቶች ሁሉ አበበች ልቃ ታየችው ።

ቤት ከመድረሱ ተሾመ በጥያቄ ተቀበለው ፤ 'አበበችን ከወንድ ጋር ያዝካት?'

'ትቀልዳለህ? ከዚያ ሁሉ ግፊያ መኻል ነፍሴን ይገር መውጣቴም እኔ በመሆኔ ነው ። አበበችን ፒያሳ ውስጥ ፈልጎ ከማግኘት ግመል ሰርቆ አጎንብሶ መሔድ ይቀላል ። እንደ ባሕር ዓሣ ማለት ናቸው— የፒያሳ ሴቶች ። ከመመሳሰላቸው ፣ ብዛታቸው ። ዐይንህ ቀድሞውኑ አንዲት ሴት ላይ ዐርፎ የማይቆየውን? ይችስ አቻም አይገኝላት ብለህ ስትደመድም ፣ የበለጠች ቆንጆ ትመጣለች ። እሷንም የቆንጆዎች ቆንጆ አድርገህ መውሰድ አትችልም ። ኦ! ግን...ለኔ አበበች ትበልጥብኛለች ።" ንጉሤ እንደሚማፀን ሁሉ መዳፎቹን ወደ ላይ ዘርግቶ አርገበገባቸው ።

'ከእንግዲህ ፒያሳ ላትፈልጋት ወስነሃል?' አለው ተሾመ
እንደ ጥያቄም እንዳስተያየትም አድርጎ ።

'አልሞክርም' አለ ንጉሤ የቀኑ ውሎዉ እያንገሸገሸው ።
'አልሞክርም ። ይልቅ ሰው ሲናፍቀኝ ፣ ቆንጆ ማየት ሲያምረኝ ፣
ውበት እንደ ውሃ ሲጠማኝ ፣ ከሲኒማ ኢትዮጵያ እስከ አርቲስቲክ
ሕንፃ ሦስት አራቴ መመላለሴ አይቀርም ። ከሳምንት ሁለት ቀን ።
ሱስ ከሆነብኝ አራት ቀን ፤ ወይም አምስት ቀን !''

ጥቂት ተሳሥቀው ዝም ተባባሉ ፤ ወደየግል ሐሳባቸው ገቡ ።
የንጉሤና የተሾመ ጠባይ በጣም ይለያያል ። ተሾመ ፣ 'ደስ አለችኝ
እንጂ ፣ አፈቀርኳት የሚላት ሴት የለችም ። ደስ ከማሰኘት ዐልፋ
ብፍቅርዋ ነደድኩ' የሚላት ሴት አልገጠመችውም ።

ንጉሤ 'አይዲያል' ፍቅር ያጠቃዋል ፤ ደስ ያለችውን ሴት
ደጋግሞ ያያታል ። ውላ አድራ ነፍሱ ውስጥ ትገባለች ። ቆይታ
ጣኦቱ ትሆናለች ። ከዚያ በኋላ ሥጋ የለበሰች አትመስለውም ።
አበበችን በጣም ከማፍቀሩ በፊት እንደ ተራ ሴት ፣ እንደ የወደ
ፊት ሚስት ነበር የሚያስባት ። ፍቅሯ በውስጡ ሥር ከሰደደ
በኋላ ግን ፣ ሲያስባት ውስጡን እንደ ጧት ጮራ የምታሞቀው
ሆነች ። ሕልሙ ፣ ሰቀቀኑ እሷ ሆነች ። ይህ የንጉሤ ደካማ ጎን ፣
ተሾመን ያበሽቀዋል ።

ንጉሤ በበኩሉ በተሾመ ይቀናበታል ። ይመቀኘዋል ሳይሆን ፣
ይቀናበታል ። ኮስታራነቱ ያስደስተዋል ። አንዲትን ሴት በወረት
ይዞ ኋላ ፣ 'በቃሽኝ' ይላታል ። ለስላሳ ምላስ ወይም እንባ
አይበግረውም ። 'ምነው ከሱ ልብ ቆርሶ ለኔም ቢሰጠኝ' ብሎ
መንፈሳዊ ቅናት ይቀናበታል ። 'አበጀህ ! እንኳን ለማንም አል
ተበለጥክ' ይላል በልቡ ልብ ውስጥ ። አንዳንድ ጊዜም በጨ
ዋታ መኻል ይነግረዋል ።

'ለምን ብየ!' ይለዋል ተሾመ እየሣቀ ። 'አንዷ ብትሔድ
ሌላዋ ትመጣለች ። የሰማች ስትሔድ ፣ ያልሰማች ትመጣለች ። እኔ
ቆራቢ አይደለሁ !''

''ቅድም ጌቶች ምን አሉህ?'' ብሎ ተጠጋው ንጉሤን ።
ምን እንደ ተነጋገሩ ለማወቅ ሳይሆን ከቀን ሕልሙ ለማንቃት ።

'ተዋት ነው ያሉኝ ።'

ተሾመ ፣ አበበችን ዱሮውንም አልወደዳትም ። 'ክፉ ናት
ጮሌ ናት ፤ ሰይጣን ናት' ብሏታል ። ቆይቶ ደግሞ ፣ 'ጠባይዋ
አይታወቅም ። ሞኝ-መሰል እስስት ናት' አላት ። በየቀኑ
አዲስ ስምና አዲስ ጠባይ ስለሚሰጣት ፣ ተሾመ ባለበት እሷ አት
ኖርም ። ከኖረች ባሽሙር ይዋረፋሉ ።

''እኔ ቀድሞኑ ነግሬሃለሁ ፤ ተዋት ፤ ኮከባችሁም አልገጠ
መም ። እንደምመክርህ ስለምታውቅ ነው የጠላችኝ ። እንኳን
ለሷ ለማንም አልደነግጥ ። ግን ተዋት ፣ ነግሬሃለሁ ።''

''ዛሬ ማታ ምንነታችን ይለያል!''

''የምርህን ነው ንጉሤ?'' ማለቂያ የሌለው ግንኙነታቸው
ፍጻሜ አግኝቶ ለማየት ጓጓ ።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሱቁ ተዘጋ ። ሲኒማ አምፔር አጠገብ
ከአልማዝ ጋር የመጨረሻውን ቀጠሮ አድርጓል ። ንጉሤ ቀድሟት
ደረሰ ።

ዐሥር ደቂቃ ያህል እንደ ጠበቃት ሰለቸው ። መምጣቷ
አጠራጠረው ። ጀርባውን ለሕንፃው ስጥቶ የማታውን ሲኒማ
ለማየት የሚመጡትን ሴቶች አንድ ባንድ ያተኩራል ። ወደሱ
በቀጥታ የመጣችቱ ሴት ዞር ብላ ወደ ሲኒማ ቤት ስትገባ ፣
ለመቶኛ ጊዜ 'ኤጭ' ብሎ ራሱን በምሬት ነቀነቀ ። ወደ ቤቱ
ለመሔድ አምስት ርምጃ ያህል እንደ ተራመደ ፣ ስሙ ሲጠራ የሰማ
መሰለው ። ዞር ብሎ ሲያይ አበበች ወደሱ እየመጣች ናት ።

''ልትሔድ ኖሯል?'' እጅዋን ለሰላምታ እየዘረጋች ጠየ
ቀችው ።

''ታዲያ ቆሜ ላድር ኖሯል?''

''ገና አንድ ሰዓት ተኩል አልሆነምኮ!''

እዚው ሠታ ሲገናኙ ራታቸውን የሚበሉ [ተራራ ሆቴል ስለሆነባእንዶ ተሰመይው በዝምታ ወደዚያው እመሩ። አልማዝ እፈት እራቱ ትሔዳለች ። ለመጨረሻ ቀን የሚያየውን ከወገቧ ቀጠን ፣ ከዳሌዋ አበጥ ያለውን ሰውነቷን በስንብት አመለካከት አየው ። ትከሻዋ ላይ የወደቀውን ጸጉሯን ባይኑ ሳመው ። ብዙ ስላስጠበ ቀችው ቢናደድም ፣ ሁሌ ቢያየው የማይጠግበውን ፣ ደግሞ የሚያበ ሳጨውን ውብቷን ፣ ጠቅላላ ቅርጿን ከማድነትና ከመውደድ አልተቆጠበም — እሷ እያወቀችበት ሳይሆን ውስጥ ውስጡን ።

ራታቸውን በልተው እስኪጨርሱ ምንም አልተነጋገሩም ። ቅን ስለማይመላለሱ ፣ ለመናገር ያሰቡትን ከራታቸው ጋር እየጎ ረሱ ዝም ተባባሉ ። በልተው ከጨረሱ በኋላ ስለሚፈጠረው ጠብ አስቀድሞ ያስባል ፤ ያስላስላል — ንጉሤ ። ቆይቶ ቆይቶ ፣

"ቢራ ይምጣልሽ?" ብሎ ጠየቃት ።

"ቢራ እዚህ ቤት መች ይገኛል!"

"እንግዲያውስ ወደ ሌላ ቦታ እንሒድ ።"

ሒሳቡን ከፍሎ ወጡ ።

"ዛሬ ደግሞ ፊትህ ያለቅጥ ተጸጥሯል ። የሆንከው ነገር አለ?"

"የሆንኩትን በኋላ እነግርሻለሁ ።"

"እምብዬው አውን ንገረኝ ።"

"መንገድ ላይ? ምነው ምን መዓት መጣ?"

"እየሔድን አይደል ዱሮስ የምናወራ?"

"ደስ ካለሽ ምን ችገረኝ? እነግርሻለሁ ። ነገሩ እንኳ ሌላ አይደለም ። ያው የኔና ያንችው ጉድ ነው..."

"እኔና አንተ ምን ጉድ አለን?" ብላ ከረር ባለ አንደበት ስትናገር ፣ እንኳን 'ዐይኗን ያላየሁት' አለ ንጉሤ-በሐሳቡ ። ስትቆጣ

ቀርቶ ስትሥቅ እንኳ ዐይኗን ማየት አይደፍርም ። መንገድ ላይ ሳይሆን ሆቴል ውስጥ አጠገብ ላጠገብ ፣ ወይም ፊት ለፊት ተቀምጠው ቢሆኑ ኖሮ እንደበቷ ብቻ ባስበረገገው ነበር ።

"እኔና አንች ጉድ የለንም ፤ ግን አንድ ውሳኔ ላይ ደርሰን... ዛሬ ቁርጡን ለማወቅ እፈልጋለሁ" !

"የምን ቁርጥ ነው አሱ?"

"ትወጅኛለሽ ወይስ አትወጂኝም?"

"ባልወድህ አንተ ጋ ምን አመላለሰኝ!"

የንጉሤ የልብ ትርታ ጨመረ። እጅዋን አፈፍ አደረገና ደጋግሞ ሳመው ። የልቡን ደስታ ግን ጨርሶ የገለጠለት አልመሰለውም ።

"እንግዲያው ከቢተሰብሽ ጋርም ታስተዋውቂኛለሽ ማለት ነዋ!"

"በደስታ!" አለች ሁለት እጆቿን እንዶ ክንፍ ዘርግታ ።

"እንግዲያው! መቸ?"

"ነገ ማታ ነዋ!"

እስከ ዛሬ ለምን እምቢ ስትለው እንደ ቆየችና ዛሬ ለምን እሺ እንዳለችው እጅግ ገረመው ።

"የማታ የማታ ፣ ለምን ነሬ አይሆንም?"

አበበች ሁለቱን ፊደሎች[ከሚገባ በላይ አራዝማ ፣ "አእአይ! ዛሬ አይደለም ፤ ነገ ነው" አለች ።

"በዛሬና በነገ መኻል ብዙ ልዩነት አለ እንዴ!"

"ብዙ እንጂ! በጣም ብዙ ። አየህ ፣ ነገ ማታ ቢታችን ውስጥ የመሰነባበቻ ግብዣ ተደግሷል ። የማውቃቸውን ሰዎች ሁሉ ጠር ቻለሁ ። አንተንም ዛሬ እነግርሃለሁ ብዬ ተዘጋጅቼ ነበር ፣ አንተ ቀድመህ ጠየቅኸኝ እንጂ!"

"የምን መሰነባበቻ ነው?"

"እሱንም ዛሬ እነግርሃለሁ ብዬ አስቤ ነበር ። አየህ ዕጮ ኛዬ ወደ ውጭ አገር ሊሔድ ነው ። 'አንቺ ቤት ካልደገስኩ ሞቼ እገኛለሁ' ብሎ አፋጠጠኝ ። እኔ ምን ችገረኝ ብዬ እሺ አል ኩት..."

ንጉሤ ራሱን የተመታ ያህል ጆሮ ጥላው ሳይ ጭው አለበት። ከራስ ጸጉሩ እስከ ግር ጥፍሩ ሰውነቱን ወረረው ። ባመረረ ጥላቻ ትክ ብሎ አያትና፣ "ዕጮኛ እንዳለሽ ለምን እስከ ዛሬ አልነገር ሽኝም? " አላት ።

"መቼ ጠየቅኸኝና እነግርሃለሁ?"

"ለምን 'እወድሃለሁ' አልሺኝ?"

"አሁንስ ቢሆን ማን 'አልወድህም' አለህ? ከዛሬ ነገ ትጠይ ቀኛለህ ብዬ ስንት ዓመት ሙሉ ደጅ ጠናሁህ ። ከጥላቻና ከንት ርክ ዐልፈህ የምታውቀው አንድ ቃል ብቻ ነው ። 'ከቤተሰብሽ ጋር አስተዋውቂኝ' የሚለውን ። ቤተሰቤ ምን ያደርግልሃል? መጠ የቅ የነበረብህ እኔን ነው ። ምን ቤተሰብ አለኝ? አባቴ ከሞተ ዘመን የለውም ።እናቴ በመኪና አደጋ ከወገቧ በታች ሽባ ሆና ያልጋ ቁራኛ ከሆነች ዘመን የላትም !"

"ይህን ያህል ጊዜ የተሠቃየው በከንቱ ነዋ!"

"እሱ በገዛ እጅህ ያመጣኸው ነው ። ፊት ለፊት ሐሳብህን መግለጽ ስትችል ፣ ውስጥ ውስጡን ነገር ስትበላ በከንቱ ቀረህ ። በል በታክሲ አሳፍረኝና ወደ ሠፈሬ ልሒድ!"

ንጉሤ ፣ በሁለት እጆቹ ራሱን እንደ ያዘ ያሳለፋቸው የሥቃይ ዓመታት እንደ ባቡር ፉርጎ እየተከታተሉ በፊቱ በዐይነ ሕሊናው ዐለፉ ...

ስኩላርሺፕ

አበበ ፣ ተወልዶ ያደገው ፒያሳ ሠራተኛ ሠፈር ነው ። አራዳ ተወልዶ አራዳ ይደግ እንጂ ጮሌ አይደለም — ማለት አይብ ለጠለጥም ። እንዳራዳ ልጆች ሁሉም ቦታ አለው አለው ፣ ሁሉንም ዐውቃለሁ ፣ ከሁሉም ሰው ጋር ልታይ ልታይ አይልም ። ከልጅነቱ ጀምሮ የልጅ ዐዋቂ ነው ፤ በሳል ነው ። 'የተባረከ ልጅ ነው ፣ እግዜር ያሳድገው ! እንጀራ ይውጣለት !' ብሎ ያል መረቀው ሽማግሌ በሰፈሩ አይገኝም ። ያሮጊቶች ምርቃትም አላ መለጠውም ።

አበበ ፣ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ድረስ የተማረው ዳግማዊ ምኒ ልክ ትምህርት ቤት ነው ። የልብ ጓደኛው ሀብታሙ ነበር ። ከስምንተኛ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ አልተለያዩም። አብረው ነው የተማሩት ።

ሀብታሙ ፣ ከፈረንጅ አስተማሪዎች ጋር የመግባባት ችሎታ ነበረውና አንድ ፈረንጅ ስኩላርሺፕ ፈልጉ ወሰደው ። ሀብ ታሙም በፈንታው ለአበበ ስኩላርሺፕ አፈላልጉ አገኘለትና ከነአውሮፕላን ትኬቱ ላከለት ። ሀብታሙ ሲበዛ ቁም ነገረኛ ነው ። ሲወድ ከልቡ ፣ ሲጠላም ከልቡ ነው ። ለወደደው አን ጉቱን ይሰጥለታል ፤ ቃሉን ያከብራል ።

አበበ ጉበዝ ተማሪ ነው ። ትምህርት ይወዳል ። በተለይ ሳይንስ ሲሆነው እንደ ወግ አይደለም ። በየትኛውም የሳይንስ ዘርፍ እኩል ችሎታ አለው ። ያክስቱ ልጅ ፍስሐ ፣ ኢንጂኔር ሁን ይለዋል ። አበበ ግን ፣ ሐኪም የመሆን ፍላጐት ነው ያለው ። አዘውትሮ የሚያጠናውም ባዮሎጂና አናቶሚ ነው ። በሀገራ ችን የሳይንስ ዕውቀት ባለማደጉና የሳይንቲስቶች ቁጥር በጣም አነስተኛ መሆኑን በመገንዘብ ፣ ሕይወቱን ለሳይንስ ለመስጠት ወስኗል ። ደክመኝ ፣ ሰለቸኝ ላይል ራሱ ለራሱ ቃል ገብ ቷል ። የአናቶሚ መጽሐፍ ከእጁ አይለይም ። 'ዓላማዬና ምኞቴ ተፈጸም ሲለው ሀብታሙን ወደ ፈረንጅ አገር ላከልኝ ። ይህም

ለዓላማዬ መታናት ዐይነተኛ ዘርፍ ሆነልኝ' ይላል፣ ወደ ውጭ የመሔዱን ነገርና የሀብታሙን ውለታ ሲያስበው ፣ ልቡ በደስታ እየዘለለ ። ዕድሜ ከሀብት ጋር አይንፈገውና ሀብታሙ ከልቡ ሰው ነው!

ከሀብታሙ ቀጥሎ ፣ እንደ ጓደኛም እንደ ዘመድም የሚቀርበው ያክስቱ ልጅ ፍስሐ ነው ። የሚያስደስት ነገር የሚነግረው ለሱ ነው ። የሚያበሽቀውም ሲያገኝ ያው ለሱ ነው የሚነግረው ። እና ፣ ስኩላርሽፕ የማግኘቱን ወሬም መጀመር ስለ ነበረበት ሳይውል ሳያድር ሔዶ ነገረው ።

ፍስሐ ፣ አበበ የነገረውን አላመነውም ነበር ። የዩኒቨርስቲውን የፈታድ ደብዳቤና የአውሮፕላኑን ቲኬት ሲያይ ግን እውነት መሆኑን አረጋገጠ ። መቅናቱ ወይም መደሰቱ ፊቱ ላይ አይታወቅም ። ፍስሐ በቁም ነገር መሻል ቀልድ ፣ በቀልድ ፣ መሻል ቁም ነገር መደባለቅ ስለሚወድ ፣ ቀልዱና ቁም ነገሩ ተለይቶ አይታወቅም ።

'እንግዲህ ዝግጅት አድርግ' አለ ፍስሐ ካንገት በላይ እየሣቀ ። 'ፓስታና ማካሮኒውን ከወዲሁ ልመደው ። እዚያ ስትሔድ እንዳትቸገር ። አሜሪካ እንጀራ በወጥ የሚገኝ አይምስልህ ። ተሳስቻለሁ ወንድሜ ፣ እንጀራ በወጥ ነው እዘውትረህ መብላት ያለብህ ፣ እስኪሰለችህ ድረስ ። እሱ ነው እዚያ የማይገኝ ። በኋላ በርበሬ ላኩልኝ እንጀራ ላኩልኝ እንዳትል ።'

ዝም አለው አበበ ።

'ያገር ባህል ልብስም መያዝ አትርሳ ፣ ጠባብ ሱሪና እጀ ጠባብ ። ጥበብ ኩታና ሰበዝ ባርኔጣ' ቀጠለ ፍስሐ ሣቅ እያፈነው ።

'በጂ ፣'

'በርበሬና ዳቦ ቆሎም መያዝ ይኖርብሃል ።'

'ጨረስክ ?'

'ሴላውን ሴላ ቀን' አለ ፍስሐ አውንም እየሣቀ ። በመ ቀጠልም ፣ 'ኦ ረስቼው ! አንድ ከረጢትና አንድ ዱላ መርሳት የለብህም !'

'እኔኮ የምሬን ደስ ብሎኛል ። አንተ ግን ትቀልዳለህ ። ለኔኮ በሕይወቴ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ ድርጊት ነው ። ለኔ ምን ማለት መሆኑን ከኔ አኩል ጠልቆ የተሰማህ አይመስለኝም ። የኔ ልብ በደስታ ሊፈነዳ ደርሷል ። እስከምሔድበት ቀን ድረስ የረባ እንቅልፍ አይወስደኝም ። የሀብታሙን ውለታ በሕይወቴ ሁሉ ችዬ የምመልስለትም አይመስለኝም ። ባሁኑ ዘመን የሥጋ ወንድም እንኳ የሱን ያህል መልካም ውለታ አይውልም' አለ አበበ ። መቀጠል አልሆነለትም ፣ የደስታ እንባ አጀረጠው ። ድምፁም ተቀየረበት ።

'ደግሞ ደስታ ያስለቅሳል እንዴ? ይልቅ ፓስፖርትህን አውጣና ቶሎ ሒድ ። ዛሬ ነገ ስትል የትምህርት ጊዜህን እታጥፋ፤ አሜሪካ ከሔድክ እቸገራለሁ ብለህ ማሰብ የለብህም ፤ እዚያ ወንድሜ እንኳን ለሰው ለመኪናውም ቤት አለው ። ቤት ሲሉህ ደግሞ ቦሌ አካባቢ የምታያቸውን ዐይነት ጎጆዎች እንዳይመስልህ ። አሜሪካ ሁሉም ነገር ግዙፍ ነው ። መንገዶች ሠፋፊ ፣ መኪናዎች ዐርበብ ሠፊ ፣ ፎቆቹ ሰማይ ጠቀስ ፣ ሰዎቹ ጎልያድን የሚያካክሉ ፣ ዳቦአቸው ያራት ኪሎን ሐውልት የሚያካክል ነው!!'

አበበ ፣ ወደ አሜሪካ የመሔዱ ወሬ በሠራተኛ ሠፈር ባንድ ጊዜ ተዛመተ ። በቅርብ የሚያውቁትም ፣ በሩቅ የሚያውቁትም፣ በዐይን የሚያውቁትም ለማነጋገር ይፈልጉታል ። አንዳንዶቹ ስኩላርሺፕ እንዲፈልግላቸው ፣ አንዳንዶቹ ልብስ እንዲልክላቸው ፣ ሴሎች ደግሞ መጽሐፍ እንዲልክላቸው ጠየቁት ። 'ልብስ ላክልን ፣ ካሜራ ላክልን...' ወዘተ የሚሉትን አልተቀበላቸውም ። ጭራሽ ወደ ሐሳቡም አላስገባቸው ። መጽሐፍ ለጠየቁት ግን እሺ ብሏል ፤ የመጽሐፍ ነገር ሞቱ ነውና ። የሆነ ሆኖ የሠፈሩ ሰዎች ወደ አሜሪካ የመሔዱን ወሬ ከሰሙ በኋላ ብርቅ አደረጉት ። የማያውቁት በዝና ስምቱው እዩት ፤ ዐወቁት ። 'እንኳን ደስ' አለህ አሉት ። ቤቶች እፍ አውጥተው ጠየቁት ። 'ካልጋብዝከን' ብለው አፋጠጡት ። 'ሲኒማ አስገባን' አሉት ።

የተልድም የምርም አድርገው ፣ 'አገርህ ፣ ሕዝብህ ፣ ይናፍቅሃል ። እንጀራው ይናፍቅሃል ። ዐፈሩ ሳይቀር ይናፍቅሃል' ብለው የነገሩትን አበበ እንደ እውነት ስለ ወሰደው ፣ ያነሩን ትዝታ በትውስታ ለመቅረጽ የሚያየውን ሁሉ በጥንቃቄ ማስተዋል ይዟል ። የሚረግጠውን መሬት ፣ የሚሰማውን መረ ፣ የሚያየውን ሽማግሌ ፣ ተረቱን ፣ ቀልዱን ፣ እንዲሁም ሁላ ሁሉን ያስተውላል ። ያደገበትን አገር እንደ መጤ ፣ እንደ ባይተዋር ያለ መሰልቸት ያስተውላል ። መቸም የሚያውቱት ሰዎች ሁሉ መንገድ ላይ ሲያገኙት፣ 'እንጋብዝህ' ማለታቸውን ስለ ለመደው፣ ያለ ምንም መግደርደር እሺ ይላቸዋል ። በኋላ በኋላማ ፣ እሱም ተጋባበት መሰል ፣ እንጋብዝህ የሚሉትን ሰዎች እሱ ራሱ ፣ 'ሻይ ሊጋብዛችሁ' እያለ ጉትቶ ወይም አግባብቶ ፣ ወደ ቡና ቤት መስደመጋበዝ አመጣ ። ደስታኑ ሲያስክር ከመጠጥ ይብሳል !!

አበበ ፣ ፓስፖርቱን ለማውጣት ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። የተላከለትን ያውሮፕላን ቲኬት ተቀብለነዋል ብሎ የኢቭር ስቲው የጻፈለትን ደብዳቤ በማየት ብቻ ቶሎ ፈጸመለት ። ፓስፖርቱን ኪሱ ካኖባ በኋላ ፣ አበበ ደስታው ዕጥፍ ድርብ ሆነ ።

አሜሪካ በሕልሙም በውኑም ይታየዋል ። የከተማዎች ታላቅነት ፣ የመኪናዎች ብዛት ፣ ጠቅላላ ሥልጣኔዉ ዝብርቅርቅ ሁኔታ እየፈጠረበት ። የሚማርበት ክፍል ፣ መኝታ ቤቱ ፣ ምግቡ፣ የሚያረግለት እንክብካቤ ፣ መጭውን ደስታውን ዕጥፍ ድርብ እንደሚያደርግለት ተሰማው ።

"ከአሜሪካ ስመለስ አስጎሳሰቤ ሁሉ ይለወጣል ። በዕውቀት እጮለምሳለሁ ። ሌት ተቀን አጥንቼ ጥሩ ዶክተር ነው የምሆን ። ስፔሺያሊስት ፣ ያውም ዝነኛ ስፔሺያሊስት !! እንግሊዝኛ እንደ አማርኛ አቀላጥፌ እችላለሁ ። እና በየጊዜው የማገኛቸውን ጥናቶች ለአሜሪካ የሕክምና መጽሔቶች አቀርባለሁ ፤ ማለት እልካለሁ ። እዚያ ያሉ አሜሪካውያን ጓደኞቼም እኔ ወዳገሬ ከተመለስኩ በኋላ አዳዲስ የሕክምና ግኝቶችን ይልኩልኛል ። መቼም እዚያ አገር ፣ ቢያንስ ስድስት ዓመታት ያህል መቆየቴ አይቀርም ። ታዲያ ያን ያህል ዓመት ስቀመጥ የነጭ ጓደኞች ላላፈራ ነው ? ስድስት ዓመት ሙሉ ምን እሠራለሁ ?

ነብር አላሰምድም ፣ እንኳን ፈረንጅ ! እነሱም ሰው ናቸው ። ይመዳሉ ይጠላሉ ፣ የሰው ልጅ ሲባል የሚመሳሰልባቸው ብዙ የጋራ ባሕርዮች አሉት ። ወዳጅነት ካሳዩት ወዳጅ የማይሆን የለም ። ጠላትነት ካሳዩትም ጠላት የማይሆን የለም ። እና በስድስት ዓመታት ቢያንስ ሦስት አራት የልብ ጓደኞች ይናሩኛል ። ካስተማሪዎችም መርጡ ፣ አይቹ ፣ መዝኔ የማከብረው ይናሬኛል ። እንድ ሰው ክለፋ ፣ ክደከመ መክበር ይናርበታል ። መወደድ ይናርበታል ።' ሲተኛም ሲነሣም ፣ ሲሔድም ሲቆምም እንዲህ እያለ ነበር የሚያስብ ። ፍስሐም በመጣ ቁጥር ፣ በተገናኙ ቁጥር ስለ ሴላ ስለ ምንም አያወራውም ። ስለ ጉዞው ብቻ ነው ።

የፍስሐ እናት ፣ የአበበ አክስት ናት ። ያበበ አባት የናጠጡ ሀብታም ነበሩ ፣ በልጅነቱ ሞቱበት እንጂ ። አቤት ሰው ሲወዳቸው ! እሳቸውም ሰው ሲወዱ ለብቻ ነበር ። እየደገሱ ማብላት ማጠጣት ነው ። ያሳቸው አልበቃ እያለ እየተበደሩ መደገስ ይወዱ ነበር ። የሚከፍሉት ሲያጡ ንብረት መሸጥ ። ታዲያ እንዲህ እያደረጉ ባለቤታቸውን በብስጭት ገደሏት ። እሷ በበኩሏ ቤት እንስራ ፣ ሀብት እናጠራቅም ባይ ነበረች ። ማን ስምታት ! እንደ ተበሳጨች ሞተች ። እሳቸው ካሥር ዓመት በኋላ ተከትለዋት ሔዱ ። ግን እካሔዳቸው የየቅል ነበር ። የሷ ብስጭት ያስከተለው የኩርፊያ አካሔድ ፣ የሳቸው ደግሞ ዱስተኝነት የወለደው የመኳንንት አካሔድ ፣ እየተጀነኑ ። እና ፣ ሲሞቱ ለአበበ ምንም ውርስ አልተዉለትም ። መኖሪያ ቤታቸው ተሸጠ ። ዕዳቸውን እንኳ አልከፈለላቸውም ። ይህም ሆኖ አበበ አይጠላቸውም ። አባቱ በክፉ እንዲነሡበት አይፈልግም ። በሕይወታቸው ሳሉ ከሁሉ ነገር አብልጠው ክብራቸውን ይወዱ እንደ ነበር ስለሚያውቅ ፣ ስማቸው እንዲጐድፍ አይፈልግም ። በዚውም ላይ ሴት አያቱ እንተባረው ነበር ያሳደጉት ።

የፍስሐ እናት ፣ የአበበ ያባቱ ትንሽ እኅት የመጀመሪያይቱም የመጨረሻይቱም ናት ። የቤታቸው ነው ። ዘር ለመተካት ያህል አንዳንድ ይወልዱና ቁጥ ነው ። አበበ እኅት የለው ! ወንድም የለው ! ፍስሐም እንዲሁ ነው ። እኅት የለው ! ወንድም የለው! እናቱ 'ሀ' ብላ እሱን ወለደች ። በዚያው አበቃች ። መውለዱን

አቆመች ። የዘር ነው ። መነን ሊሆኑ ትንሽ ነው የቀራቸው ። ዘራቸውም ሊቆም ትንሽ ነው የቀረው ። የፍስሐ እናት ግን የዘመድ ልጆችን ታሳድጋለች ፣ እንዶ ልጅ አድርጋ ።

የፍስሐ እናት ወይዘሮ አስቴር ፣ ሴት ባትሆን ኖሮ ቢያንስ የፈታውራሪነት ማዕረግ አታጣም ነበር ። ቤት መሥራትና ማከራየት ፣ ገንዘብ ማጠራቀምና ባንክ ቤት ማስገባት የጀመረች ወይዘሮ አስቴር ናት ። በወንድሟ አባካኝነት በጣም ትናደድ ነበር ። ፈታውራሪ በላይ ግን የቧን ነገር አይሰሟትም ነበር ። ለገንዘብ የሚንሰፈሰፍ ሰው ያናድዳቸዋል ። የክብራቸው ነገር ግን አይመንላቸውም ።

ይኸው እንግዲህ አበበ ፣ ዘመናዊ ትምህርት ቀስሞ ከቤተሰቡ የመጀመሪያው ምሑር ሊሆን ነው ። ካባቱ የተለየ ሰው ሊወጣው ነው ባለ ልዩ አስተሳሰብ ።

አበበ በላይ ፣ የፈታውራሪ በላይ ልጅ ሁሉንም ነገር ጨርሶ ያሥር ሺ ብር ዋስ ጠርቶ መሔድ እንደሚችል ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተነግሮታል ።

አበበ ፣ 'ያሥር ሺ ብር ዋስ አምጣ' ሲሉት ፣ በጅ እንዳለ ነገር ስለ ቄጠረው ምንም አልተጨነቀም ። የወይዘሮ አስቴር ቪላ ቤት ከሃምሳ ሺ ብር በላይ ይገመታል ። የሚከፈል ገንዘብም ቢኖር ትከፍልለታለች ።

'ዋስ ጥራ ተባልኩ እኮ ፣ ያሥር ሺ ብር ዋስ ። አክስቴን ማስቸገር ግድ ሊሆንብኝ ነው' አለ አበበ ፣ ፍስሐ የቀልድና የፈዝ ወሬ ከመጀመሩ በፊት በቁም ነገር ወሬ ሊጠምደው ስለ ፈለገ ።

'ዋስ ምን ያደርጋል ? ዋስ ራሴ ብትል እሺ አይሉህም ፣ ግለት አያምኑህም ?'

'እይ አትቀልድ ። ደንብ ደንብ ነው ። እስከ ዛሬ ሲሠራ በት የኖረው ዛሬ ለኔ ሲባል አይሻርም ። ይልቅ ቶሎ ቶሎ ብዬ በዚህ በነሐሴ ወር ጨርሼ በጳጉሜ ውስጥ መሔድ አለብኝ ።'

'እግዬ ፣ ጭት የወጣች አስቀድሳ ነው የምትመለስ ። ከስ ዓት በፊት ልታገኛት አትችልም' አለ ፍስሐ ። ወይዘሮ አስ ቴር ፍልሰታን ታስቀድሳለች ፤ ትጾማለች ፤ ማርያምን ትወዳ ለች ፤ ታዝንራለች ።

አበበ ማታውኑ አክስቱ ቤት ሔደ ። ፍስሐ በጊዜ አልገባም ስላለው ብቻውን ነው የሔደ ። 'እንተ ነህ እንዴ እቤ ? ግባ እንጂ!' ብላ በአክብሮት ነው አበር ድረስ መጥታ የተቀበለችው፣ አክስቱ ።

'ሻይ ይምጣልህ ። ራት ብላ ። ምን ይሻልሃል ?' በጥያ ቄና በትእዛዝ አጣደፈችው ። አበበ ቢቃኝ እስኪል ድረስ በላ፣ ጠጣ ። የሚያወሩትን ያህል አወሩ ። መጨረሻ ላይ የመጣበ ትን ጉዳይ ነገሩት ።

'የዐሥር ሺ ብር ዋስ ? ምን ማለታቸው ነው ? ለትምህርት ከሆነ ለምን እንዲህ አይፈቅዱልህም ?' ሩድን ከፋው ። አበበም ሲከፋት አየ ።

'እይ ደንብ ስለሆነ ነው ። ለስሙ ያህል ፣ ለደንቡ ያህል 'ያሥር ሺ ብር ዋስ' ይላሉ እንጂ ፣ ከዋሱ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም ፣ ማለት ሰውየውን አቅርቢ እያሉ አያስቸግሩሽም ። ብቀር እንኳ' አላት ። እንዴት እንደሚያሳምናት እየጨነቀው ። አክስቱን ለማግባባት ያህል ተናገረ እንጂ ፣ እሱ እንደሆነ በግር ብረት ቢያስሩትም አይቀር ። አሜሪካ ሔዶ መቅረት የሚሉ ነገር በሐሳቡም የለ ። አስቦትም አያውቅ ።

'እንግዲያውስ ለትምህርት ምኒስትሩ አቤት ብትል ይሻ ላል ። እነሱ እንድ መላ ይፈጥሩልህ ይሆናል' አለች ወይዘሮ አስቴር እንዶ በረዶ ቅዝቅዝ እያለች ። ገንዘብ ስለምትወድ አበ ድረኝ ፣ ዋስ ሁኚኝ ሲሏት ይከፋታል ። በተረፈ ዘመድ ትወ ዳለች ። ታበላለች ፤ ታጠጣለች ። ግን ፣ ከገንዘብና ከዘመድ ምረጭ ቢሏት ገንዘብን ትመርጣለች ። 'ገንዘብ ካለ ዘመድ አይገድም ፤ ገንዘብ ከሌለ ግን ዘመድ ከየት ይገኛል ?' የገንዘብን ዋጋ ከባ

ንክ ሹም የበለጠ ታውታለች! ያለትጥ ባታበዛው ይላታል ዘመድ ።

"እምቢ ልትለኝ ነው እንዴ?" ብሎ አሰበ፣ አበበ ። "የሰም ጉዳዩ እስኪገለጥላት ድረስ ነው ። 'አንድ ሰው ውሎ አገር ሔዶ ከቀረ፣ ዋሉ ይያዛል' የሚል አባባል ወይም ወሬ በሰፈሙ ተዛምቷል ። አሷም ከዚህ ውሎ ልትሆን አትችልም ።"

'ዋስ አጥቼ ብቀር ሰውስ ምን ይላል? አስቸጋሪው ነገር ስኩላርሺፕ ማግኘቱ ነበር ። ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላ ተመልሼ አገሬንና ወገኔን የምጠቅም ሰው እንዴት ዋስ አጥቼ ልቅር' አላት በማስተዛዘን ። የእምቢታ መልስ የተጻፈበትን ገጽታዋን በከፊል እየሰረቀ እያየ ። ሙሉ ለሙሉ ለማየት ግን አልደፈረም ።

'ዋስትናስ ከባድ ነገር ነው ። እኔ በዋስትና አይደለም እንዴ የቡና መሬቴን የሸጥኩ! እንዴት ምንም የለበትም ትለኛለህ!'

'እንግዲያውስ ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀሽ ተረጂ፣ ጉዳዩ እንቺ...'

'የሰው ሰው ምን አስጠየቀኝ? እንዴ ሞኝ እየሆርኩ ሰውን ሁሉ ልጠይቅ ነው እንዴ?' አለች እየተቆጣች ። ተቤቱ ውጣ ልኝ ለማለት በቋፍ ላይ ያለች ትመስላለች ። በጣም ተቁነጠነጠች ። ደረቅ ወንበር ላይ እንደ ተቀመጠች ሁሉ ።

'ስንቶቹ እየቀሩ አይደል! ዋሶቻቸው ምን ሆኑ? ለምን ዕድሌን ታበላሺብኛለሽ? ቀሪውን ዕድሜዬን በጎዝን እንድጨርሰው ትፈልጊያለሽ?' አበበ እየፈራ አፋጠጣት ። የሱ ፍርሃት እንዲገባትና እሺ እንድትለውም በጣም ጣረ ።

'ለምን ዕድልህ ይበላሻል? እዚሁ እኛ አገር አትማርም?'

'እኔ የምፈልገው ዐይነት ትምህርት እኛ አገር ስለሌለ ነው እንጂ ቢኖርማ ምን አስኬደኝ?' አለ አበበ "ባገራችን ያለውን ውድድር አታውቅም ወይስ ስታብል ነው?" ብሎ አያሰበ ። 'ደግሞስ የሚፈለገው የትምህርት ዐይነት ሁሉ እዚህ አይገኝ' አለ ።

'እዚህ ያለውን መርጠህ መማር ነዋ!'

'ተይ አክስቴ እንዴሱ አትበይ፣ አቀየምሻለሁ' አለ አበበ የማይፈልገውን ትምህርት መርጦ መማሩን ሲያስብ እየቀፈፈው ።

የዚህን ጊዜ አክስቲቱ የረገበው ቁጣዋ እንደገና ተወጠረ፣ ደሟ ፈላ ። 'ፈጣሪ አይቀየመኝ እንጂ፣ እግዝትን ማርያም አትቀየመኝ እንጂ፣ አንተ ብትቀየመኝ ምን ታደርገኛለህ፣ አታበላኝ፣ አታጠጣኝ፣ ራሴን ችዬ የማድር ስለሆንኩ ልታስፈራራኝ አትሞክር ። እንኳን ባንተ፣ በወለድኩት ልጄ በፍስሐ እንኳ አልመካም ። ደኅና እስክ ሆንኩ ድረስ ደኅና ነኝ ። 'ራስ ደኅና' አለች አሉ ትግል ። ያውም የዘመኑ ልጆች! ማተብ የለሾቹ! ምናችሁ እንዳይተር ነው ።"

'ሰው በሆዱ ብቻ ነው የሚወዱድ? ማለት የማያበላ፣ የማያጠጣ ሰው ቢተየም አይጉዳም ማለትሽ ነው?'

ለዚህ የሚሆን መልስ አክስቱ ማግኘት ስላልቻለች ዝም አለች ። እንዲያው ዝም ዝም ። ይህን አጋጣሚ ሊጠቀምበት ፈለገ - አበበ ። ወደ መረታቱ የተቃረበች ስለ መሰለው፣ ይበልጥ አንጀቷን የሚበላ አነጋገር መናገር እንዳለበት ተሰማው ።

"ዛሬ ጊዜው በፍጥነት እየተለወጠ መሆኑን ታውቁዋለሽ ብዬ አላስብም ። አሁን ያለንበት እና እነአባባ የኖሩበት ዘመን ብዙ ልዩነት አለው ። ባሁኑ ጊዜ ዘመናዊ ትምህርት የሌለው ሰው ደኅና ሥራ ለማግኘት ብዙ ችግር ይገጥመዋል ። እና፣ እኔም ያሁኑ ዕድል ካመለጠኝ አለቀልኝ ማለት ነው ። ይህ ዕድሉ በጅሽ ነው ። እንዴ ፈለግሽ ልታደርጊው ትችያለሽ ። እና፣ ብታስቢበት መልካም ነው ። በግዴየለሽነት ወይም በቸልተኝነት ዕድሌን እንዳትስብሪው ተጠንቀቂ" ብሎ እንባቱን ደፋ፣ ዕድሉ ሲሰበር ለማየት የፈራ ይመስል ።

'እርም የናቴን ሥጋ አልዋስህም' አለች አክስቱ በቁጣ ፤ ከማለች ወደ ኋላ አትልም ። የፈለገው ነገር ቢመጣ ። 'እምዬ ማርያምን አልዋስህም ።' ነገሩ በዚህ አከተመ ።

"በችኩላ አቀራረብ ነገሩን አበላሸሁት" ብሎ ደነገጠ ፤ አበበ ። ለብዙ ዓመታት ተጠራቅሞ የነበረው ምኞቱ በቅዕበት ተናደ ። ተስፋው ገደል ገባ ። አዱኛ ብላሽ ! ትምህርት ብላሽ ! ምኞት ብላሽ! መሶ ሰውነቱ በድንጋጤ እንደ ተሸማቀቀ ለመሔድ ተነሣ ። 'የኔና ያንቺ ዝምድና ከእንግዲህ አከተመ ። ካሁን በኋላ አላውቅሽም ፤ አንችም አታውቂኝ' ብሏት ወጥቶ ሔደ ።

በነጋታው ፤ 'እስኪ ደግሞ ሌሎች ሰዎች ሞክር ። ለምሳሌ ያባትህን ጓደኞች ። ይህን የመሰለ ዕድል በከንቱ አያምልጥህ" ብሎ አንድ ጐረቤቱ መከረው ። ለመሞከር ያህል እሺ ብሎ አንድ ሁለት ሰዎችን ጠየቀ ። ባይሞክር ይሻለው ነበር ። እነሱን አስረድቶ ለማሳመን ከመሞከር ፤ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ማሾለክ ይቀላል ። የዘመኑ ትውልድ ካባቶቹ ጋር ምን ያህል በመንፈስ እንደ ተራራቀ ገባውና አዘነ ። ዘመን እስኪያቀራርባቸውና ልብ ለልብ እስኪተዋወቁ ድረስ ለምን ያህል ጊዜ እንደ ሚቋሰሉ ግን መገመት አልቻለም ።

ከዚህ በኋላ ፤ ምንም ምን ለማንም አልተናገረ ። ትምህርት ሚኒስቴር አመልክቶ አስተማሪነት ተቀጠረና ወደ ገጠር ሔደ ፤ የጐረቤቶቹንና የጓደኞቹን አሉቧልታ ለመሸሽ ሲል ። መሔዴ ነው ብሎ የተሰናበታቸውን ሰዎች ላለመገናኘት ሲል ወደ ገጠር ኮበለለ ። እሔደበትም አገር ከሰው አልተደባለቀም ። ጧት ይወጣል ። ሲያስተምር ይውልና ማታ መጠጥ ቢጤ ቀምሶ ገብቶ ይተኛል ። እምብዛም ከሰው አልተጠጋም ። እምብዛም አልሸሸ ። እንዲያው በድርበቡ ፤ የሆዱን ቁስል በዝምታውና በሣቁ እየሸፈነ ሰባት ዓመት ኖረ ።

በሰባት ዓመቱ ለአንድ ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ መጣ ። ያን ሰሞን ፍስሐም ካሜሪካ ተመልሶ ነበር ።

ያበበ ወደ አሜሪካ ለመሔድ መነሣሣት ፤ ፍስሐን ከእንቅልፉ ቀስቅሶት ስለ ነበር ፤ ሳይውል ሳያድር ገንዘብ እየከፈለ ለመማር

እናትና አባቱን አሳምኖ ፤ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፓስፖርት አውጥቶ ወደ አሜሪካ ሔደ ። በሰባት ዓመቱ ተመልሶ መጣ ። እሱ በመጣበት ሳምንት አበበም ላንድ አቤቱታ ወደ ዋናው መ/ቤት መጥቶ ስለ ነበር መንገድ ላይ ግጥምጥም አሉ ። በማይተላለፉበት ሁኔታ ባይገናኙ ኖሮ በተላለፉ ነበር ።

በአያሌው ተሳሳሙ ።

"ደኅና ነህ አቤ ?" አለ ፍስሐ በፍልቅልቅ አንደበቱ ።

"ደኅና ነህ ፍስሐ?" አበበ ካንገት በላይ ነው የሚመልስለት ።

"አቤት ጊዜ እንዴት ይሮጣል ?"

"በጣም እንጂ !"

"ከተለያየን ሰባት ዓመት መሆኑ ነው !"

"መሆኑ ነው ።"

"እኔ እንኳ ከአሜሪካ የመጣሁለት ነበር ፤ አንተን ለማግኘት የፈለግሁ" አለ ፍስሐ ችኩላው በግልጽ እየታወቀበት ።

"አሜሪካ ሔደህ ነበር እንዴ ?" ሲል አበበ በመገረም ጠየቀው ።

"ወዲያው ነዋ ! አንተ ፓስፖርት ካወጣህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ እኔም አወጣሁ ። ወዲያው ሔድኩ ። ከመጣሁ ገና አንድ ሳምንት እልሆነኝም ።"

"እኔኮ አልሰማሁም ነበር ፤ መሔድህን" አለ አበበ እየተገረመ ።

"ሔጄ መጣሁ ። ትምህርቴን ጨርሼ መጣሁ" አለ ፍስሐ ደስ ደስ እያለው ። አበበን ስላገኘው ደስ ብሎታል ። አገሩ ስለ ተመለሰ ደስ ብሎታል ። የሚያውቀውን ሰው ሁሉ እያቀፈ ይስማል ። አሜሪካ ኩራቱን አጥቦለት በሳልና ትሑት ሆኗል ። የተሰማውን የሚናገር ግልጽና ቅን ሰው ሆኗል ።

መንገድ ላይ ቆመው ብዙ አወሩ ። በጋራ ስለሚያውቋ
ቸው ሰዎች አወሩ ። ስለ አሜሪካ አወሩ ። ስለሌላ ሌላም አወሩ ።

አበበ ፣ ከሰላምታው በኋላ ቶሎ ሊለየው ፈልጎ ነበር — ፍስሐ
እጁን ጥርቅም አድርጐ ይዞ አለቅም አለው እንጂ ። ''መጫወት
አለብን ። ያንተን አላውቅም እንጂ እኔ በበኩሌ ናፍቂሃለሁ ።
ስለዚህ ዛሬ ስንጫወት ማምሸት አለብን ። አንተ የፈለገህን
በል እንጂ እኔ አለቅህም !! ቤት መቀመጥና ያሮጊቶችን ጥያቄ
መመለስ ሰልችቶኛል ። ብቻዬን በየቡና ቤቱ መዞርም አስጠ
ላኝ'' አለ ፍስሐ ነጥቆት ያመልጥ ይመስል ፣ የአበበን እጅ አጥ
ብቆ ይዞ ።

አበበም ፣ በል 'መቸስ ምን አደርጋለሁ !' አባባል እሺ አለ ።
የነበረውን ቀጠሮ ሰርዞም ከፍስሐ ጋር ለማምሸት ተስማማ ።

ካራት ኪሎ ፒያሳ ድረስ በእግራቸው ነው እያወሩ የሔዱ ።
አበበ እንኳ በታክሲ እንሒድ ብሎ ነበር ። 'አገር እያየን እን
ሒድ' ያለ ፣ 'ወክ እናድርግ' ያለ ፍስሐ ነው ። እና ፣ 'ወክ' እያደ
ረጉ ፒያሳ ደረሱ ።

''ታውቃለህ'' አለ ፍስሐ ፣ ''እንኳን ደኅና መጣህ ለማ
ለት አረቄ እየያዙ የመጡ ሰዎች እስከ ዛሬ በመጉረፍ ላይ
ናቸው ። ታዲያ የሰላምታቸው ብዛት ፣ የጥያቂአቸው ብዛት
ያስለቻል ። እንዱ ሰው ጠይቀህ የመለስክለትን ጥያቄ ፣ ሌላዉ
መልሶ ይጠይቅሃል ። ለዚያኛው ስትመልስለት እኮ ሲሰማ
ቆይቶ ነው እንደ አዲስ የሚጠይቅህ!'' አለ ፍስሐ በምሬት ፣ ወደ
ገብረ ሰማያት ቡና ቤት ሊገቡ ትንሽ ስለ ቀሩቸው ፣ መሬውን
ሳይጨርስ እንዳይገባ አበበን መንገዱን እየዘጋበት ።

የገብረ ሰማያትን ቡና ቤት ድሮም ይወዱት ነበር ። መ
ናኛቸውም ፣ መዋያቸውም እዚያው ነበር ። ብዙ ትዝታ አለ
ቸው — በገብረ ሰማያት ቡና ቤት ።

እንደ ዱሮአቸው ፣ እንደ ልጅነታቸው ሰተት ብለው ገቡ
ተው እሚወዱት ሶፋ ላይ ተቀመጡ ። ቡና ቤቱ ውስጥ ከሌ
ቶች በቀር የተለወጠ ነገር የለውም ። ለፍስሐ ግን ሁሉም ነገር
አዲስ ነው የሆነበት ። አይቶት የሚያውቀው ዐይነት አዲስ ፣

አዳራሹ መሻል እንዱ ምሰሶ እቆመው እራት ማዕዘን
ዓምድ ላይ ረጃጅም መስተዋቶች አሉ ። ሴቶች ወንዶችን ፣
በስርቆት የሚያዩባቸው ናቸው ።

አስቴር የምትባለዋ አስተናጋጅ ፣ ዳሌዋን እያወዛወዘች መጥታ
'ምን ልታዘዝ ?' ብላ ጠየቀች ። ደረታ እንዱ ወርቅ ያብለጨ
ልጫል ። ሰውነቷም እንደ ለበሰችው የሐር ቀሚስ ለስላሳ መስ
ኗል ።

አበበ ፣ ሻይ ወይም ቡና ከሁለት አንዱን እንድታመጣለት
ሲያዛት ፣ ፍስሐ ከመቀመጫ በሚፈነቅል አኳኋን ''ና ና'' ብሎ
ጮኸና ''ጅን እምጭልን'' ብሎ አዘዛት ። አቤት ጅን ሲያዛት
የተጀነነው መጀነን ። ግን የፍስሐ መጀነን የኩራት ሳይሆን
የደስታ ነው ፣ ብዙ ጊዜ ሲናፍቀው የነበረውን ሰው ሲያገኝ
የሚሰማ ዐይነት ደስታ ።

አስቴር ፣ ትእዛዝ ተቀብላ ወዱ ባንነኒው ስትሔድ ፣ ፍስሐ
ዐይኑን ከዳሌዋ ላይ ሳይነቅል አያት ። ዳሌዋ ከፍ ዝቅ ይላል ።
ስትራመድ እስክስታ የምትመታ ትመስላለች ።

በብጥሌ መለኪያ እየተለካ የሚቀርብላቸውን ጅን ፍስሐ
ቶሎ ግልብጥ ያደርግና ፣ 'ድገሚኝ' ይላታል ። እበበንም ቶሎ ቶሎ
እንዲጠጣ ያስገድደው ጀመር ። አበበም ከፍስሐ እኩል ለመ
ጨለጥ ተገደደ ። እና በግማሽ ሰዓት ውስጥ ሁለቱም ሞቅ እላ
ቸው ። እንደ ልብም ማውራት ጀመሩ ። ተቆልፎ ተቋጥሮ የነ
በረው ያበበ ልብም ተፈታለት ።

ከዚህ በኋላማ አጠጣጣቸው መጠን አጣ ። ፍስሐ አስቴርን
በሥሬ ነይ ይላታል ። አስቴር ዳሌዋን እያወዛወዘች ይዛላቸው
ከተፍ ነው ። ከዚያም ለስሙ ያህል ፣ ''እምቦ ውሃ ይግባላችሁ ?''
ብላ ትጠይቅና የአወንታና የእምቢታ መልስ ሳትጠብቅ ሳመል
ያህል እዚያም ፣ እዚያም ጠብ ታደርግላቸዋለች ።

ከብዙ ዙሮች ባንደኛው አስቴር አቅርባላቸው ዞር ስትል ፣
ፍስሐ በትዝብት ዐይን አስተውሏት ሲያበቃ ወዱ አበበ ዞር
አለና ፣ 'ለድመት ወተት ስትሰጥ' ትላለች እናቴ'' አለ ፣ በትዝታ

የናቱ ተረት]ትዝ ብሎት ፥ 'ለድመት ወተት ስትሰጥ ትንሽ ውሃ ጠብ አድርግበት ። ለምን? ብትል ለምስክርነት ። ድመት ከገዳ ናት ። እገሌ አበላኝ ፥ እገሌ አሳደገኝ አትልም ። በዚህ በዚህ ከውሻ ዘር በጣም ትለያለች ። ውሻ አሳዳጊውን አይረሳም እንግዳ ሰው ሲያይ ልናከስ ይላል ፤ ይጮሃል ። ድመት ግን ሰው አትመርጥም ። ዘላ ማንም ሰው ላይ ቂጥ ነው የምትል በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን በወዲያኛውም እንዲሁ ናት አሉ ፥

'ድመት ማን አበላሽ ?'

'ማንም' ትላለች ። ሁለት ፍቺ ባለው አባባል ። 'ማንም ሰው አበላኝ ፤ ማንም አላበላኝ'

'ድመት ማን አጠጣሽ?'

''ማንም' መቸም ይሽ ከሀደት ነው ። ድመት ስትከድ እንዲህ ነው እና' ትላለች እናቴ'' አለ ፍስሐ ወሬ ፥ ተረት ከጀ መረ ሳይጨርስ አይተውም ። ''እና ስትሰጣት ምስክር ያስፈ ልግሃል ። ማለት ወተቱ ላይ ትንሽ ውሃ ጠብ አድርግበት ። ታዲያ ድመቲቱ ፈጣሪ ፊት ስትዋሽ ፥ የሰው ልጅ ውሃን ምስ ክር ይጠራል ። ውሃውም ይመሰክርባታል ።''

''ወተቱ ለምን አይመሰክርምን'' ሲል ጠየቀ አበበ ።

''አንድ ምስክር ብቻውን በቂ አይሆንማ ! ''

''ነባኝ ። ግን ይችን ተረት ለምን ተረትካት?'' ሲል ጠየቀው አበበ ።

''አስቴር'' ሲል መለሰለት ፍስሐ ። አስቴርንና የዳሌዋን ውዛ ዋዜ በቁልምጫ አመለካከት እያየ ።

''አስቴር ድመት ናት እንዴ ?''

''አይደለችም ። አስቴር ሰው ናት ፥ ሴት ናት ። ድመቶቹ እኛ ነን ። ወተት ሳይሆን አልኮል የምንጠጣ ድመቶች ።''

''አልገባኝም'' አለ አበበ የፍስሐ ተረት እንቆቅልሽ እየ ሆነበት ።

''እምንጠጣው ጅን ላይ አምቦ ውሃ ላመል ታህል ስትጨ ምርልን አላየህም ? ለምስክርነት እኮ ነው ። በኋላ አልጠጣ ንም ብለን እንዳንክድ ። በኋላ በሰማይ ቤት'' አለ ፍስሐ ።

የፍስሐ ቀልድ ስላልጣመው አበበ እንዲህ አለ ። ''ይሀን ተረት ከስርቻ ውስጥ ነው ፈልገህ ያመጣኸው ። ለብዙ ጊዜ ተቀብሮና ተረስቶ ስለነበር ፥ አቡዋራውን እያራገፍክ ማውራት ስትቀጥል ጉሮሮየን ከረከረኝ ። አሁን ማውራት የነበረብህ ትኩስ ወሬ ነው ። እንዳያቃጥልህ ከፈራህ እፍ እፍ እያልክ ። እና ስለ አሜሪካ ብታወራ ይሻላል ። ለኔ አዲስ የሚሆንብኝ ያሜሪካ ወሬ ነው ።'' አሜሪካ ሲል ሥልጣኔ ፥ ሥልጣኔ ሲል አሜሪካ ማለቱ ነው። አበበ አሜሪካንና የነጭን ሥልጣኔ አንድ አድርጐ ነው የሚያስባቸው ።

ዝም ዝም ተባብለው ቆዩ ።

''አይገርምህም'' ብሎ ጠየቀው ፍስሐ አበበን ።

''ምኑ ?'' ሲል መልሶ ጠየቀው ፥ አበበ ፍስሐን ።

''ያስቴርን ዳሌ ታይልኛለህ ! እንዴት እንደምታወዛውዘው! ቆይ እባክህ አታቋርጠኝ ። ደግሞ አትጐንትለኝ ። ዝም ብለህ አያት ። ዐውቃኮ ነው የምታንቀጠቀጠው ። ከፍ ዝቅ ፥ ብቅ ጥልቅ ስታደርገው እስክስታ የሚወርድ ይመስላል !''

''ያስቴር ዳሌ ለኔ አዲስ አይደለም ። ይልቅ ስለ አሜሪካ ንገረኝ ። ሳይንስ ምን ያህል እንዳደገ ፥ ዕውቀት ምን ያህል እንደ በዛ ይህም ባይሆን ስለ አብርሃም ሊንከን ፥ ስለነጆርጅ ዋሽንግተን ፥ ወይም ስለ ሌላ ሰው ንገረኝ !''

ፍስሐ ፥ ያችን ጉንጭ የማትሞላ ጅን ጭልጥ አደረገና ፥ ''ነይ አንቺ ድግሚኝ'' አለ በብርጭቆዉ ቂጥ ጠረጴዛውን እየደበደበ ።

ከዚያም ወደ አበበ ዞር ብሎ ፥ ''አንተ መስማት የፈለግ ኸው ስለ አሜሪካ ነው ። እኔ ደግሞ ማውራት የፈለግሁ ስላ ገራችን ነው ። የሚረባም ይሁን የማይረባ ፥ ስለ ትልቅም ሆነ

ስለ ትንሽ ፥ ስለ አስቴር እንኳ ቢሆን ስላገራችን ነው ማውራት ያስንኝ ።"

"ካላሰንህ በግድ ስለ አሜሪካ አውራልኝ አልልህም" አለ አበበ የኩርፊያ በመስለ አነጋገር ። ብዙ ለመስማት ፈልጌ ምንም ስላልነገረው እያዘነ ። ብዙ እያወቀ ለምን ቁም ነገር እን ደማያወራው ሲያስብ የናቀው መሰለው ።

"ሐና ትዝ ትልሃለች አቤ? ያች ሐና.....ብሞትም እንኳ የምረሳት አይመስለኝም ። አይ ሐና! አይ ሐና!"

አበበ ፥ አንድ ያልታወቀ ነገር አእምሮውን ሰላም ነሥቶታል። እንደ ቁጭት ፥ እንደ ፀፀት ቢጤ ይሰማዋል ። እና በንዴት እየደ ጋገመ ይጠጣል ። ፍስሐ ያለቅጥ መደሰቱና መወትወቱም አብ ሽቆታል ። ቁም ነገር የማያወራውም ስለ ናቀው መስሎታል ። ግን ፥ ከዚህ ወዲያ አንድ የሚከነክነው ነገር አለ ። የፍስሐ እን ደዚያ መሆን እሱን ለማብሸቅ ፥ እሱን ለማናደድ የፈጠረው የአንገት በላይ ሣቅ መስለው ። እና ፥ በጥርጣሬ ዐይን ያስተው ለው ጀመር ።

ፍስሐ ራቱ ቀልቷል ። ካለባበሱ በቀር በሌላ በሌላው ግድ የለሽ መስሎ ይታያል ፤ ሰውነቱም ገዝፏል ። መጠጡ ራሱ ላይ መውጣት ጀምሯል ። ሁለቱም ብዙ ጠጡ ፤ ብዙ አመሹ ፤ ፍስሐ ግን በጣም ሰከረ ።

"በል እንግዲህ ወደ ቤታችን እንሒድ" ብሎ አበበ አስተ ያየት ሰነዘረ ።

"አድራለሁ" አለው ፍስሐ ትከሻውን እየነቀነቀ ። አባባሉ እውነት ባይመስለውም ፥ አበበ ብዙ ሊከራከረው አልፈለገም ። የራሱ ጉዳይ እንደ ማለት እሱም ትከሻውን ነቅንቆ ፥ "በል እንግዲያውስ ፥ ደኅና እደር" አለው ።

ፍስሐም እጠባቡ ተቀምጣ የነበረችውን አሻሸያጭ ዳበስ እያደ ረገ ፥ 'ታዲያስ?' አላት እንጂ ፥ አበበን 'ደኅና እደር' አላለውም ።

አበበም ወዴት እንደሚሔድ ሳያውቀው ከቡና ቤት ወጣ ። ጥቂት ሔዶት ካለ በሁዋላ ፥ ወዴት እንደሚሔድ ግራ ገብቶት መንገድ ዳር ቆሞ ሲያመነታ ብዙ ቆየ ፥ ፍስሐ ከኋላው ከተፍ እስኪልበት ። "ስ—ማ አ—በ—በ" አለ ፍስሐ እያንዳንዱን ፊደል እየረገጠ፥ "ካንተ ከተለየሁ ሰባት ዓመቴ ነው። አልረሳሁህም ! ሐናንም ካየሁዋት ሰባት ዓመቴ ነው ። እሷንም አልረሳኋትም ። ዛሬ ከሷ ጋር ካላደርኩ ሞቼ እገኛለሁ ። እንደ ምንም ፈልገን ግግኘት ይናርብናል ። አንተም እንደምትወዳት ዐውቃለሁ ። እንዲያውም እንድ ምሽት ፥ 'ከሐና ጋር አንድ ሴሊት አድሬ ፥ ሲነጋ ብሞት አይቆጨኝም' ብለህ የነገርከኝንና በሷ ላይ የነ በረህን ምኞት በደንብ አስታውሳለሁ ።

"ካንተ በፊት እንድ ዘፋኝ እንዲህ ብሷል ብዬ ብነግ ርህ ፥ 'የሱ ዘፈን ሐና ድንግልናዋን ከማስረከቧ በፊትም ይዘፈን ስለነበር እሷን አይመለከትም' አልከኝ ። ትዝ አለህ ?" አበበን ደስ ቢለውም ባይለውም ፍስሐ የመጣለትን ከመናገር አልተቆጠበም። ምሽቱን የመዝናኛ ምሽት አድርጐ ስለ ወሰደው ፥ በዋዛ ፈዛዛ ሊያሳልፈው ወስኗል ። በሐሳብ ለመወጠርማ ሥራ ከጀመረ በሁዋላ ያደርሰዋል ።

አበበ ፥ በመገረምና በቁጣ አስተያየት ፍስሐን እየገረመመው፥ "ታዲያ በየቡና ቤቱ እየዞርን ሐናን ውለዱ ስንል ልናድር ነው? አላበዛኸውም እንዴ?" አለው ። ፍስሐም "ይልቅ ከንዴትህ ቆጠብ በልና ልንገርህ ። ሸንቁጤ በተባለው ወዳጅዋ ትናደድ የነበረው ትዝ አይልህም ? 'ወይ አይጠቀልላትና ሚስት አያደርጋት ። ወይ አይተዋት ። ይህ ገብጋባ ነጋዴ እየቆነጠረ ጨረሳትኮ' ትል ነበር ። እውነትም ያንን ጽጌ ረዳ አበባዋን ብቻውን ነው ቀስሞ የጨረሰው" አለ ።

አበበ ፥ በሸንቁጤ ሲናደድ ምክንያት ነበረው ። ያክስቱም ወዳጅ ስለ ነበር ፤ እና ፥ ሸንቁጤ ደግሞ ይንቃት ስለ ነበርና ፥ ሁል ጊዜ አክስቱ ሸንቁጤን ፍለጋ ስትባክን ያያት ስለ ነበር! ግማሽ እሷ ግማሽ ሸንቁጤ ያናድዱት ነበር ። ፍስሐ ግን ሸንቁጤ የናቱ ወዳጅ እንዴ ነበር እያውቅም ። ደንበኞቹው ብቻ ይመስለው ነበር ።

ዕቃ ከሱ መደብር ብቻ ይገዙ ስለ ነበር ። ይሆን ሲያስብ ሳለ ፍስሐ እጁን ያዝ አድርጉ ፣ "በል እንጂ" አለው ።

"ስማ እኔ ሸንቁጤን አጠላው የነበረው እኮ በሐና ቀንቼ በት አይደለም ። የናትህ ወዳጅ ስለ ነበር ነው ። አቧን ሲጫ ወትባት አይና እሰማ ስለ ነበር ነው ።"

ፍስሐ ደሙ ፈላ ። ስካሩም ብን ብሎ ጠፋ ። "ታዲያ ያን ጊዜ ለምን አልነገርከኝም ነበር ? ዛሬስ ለምን ነገርከኝ ?"

"ያን ጊዜማ እናትህ አክስቴ ስለነበረች ፣ አክብራትም ስለ ነበር ፣ አንተም ያክስቴ ልጅ ትመስለኝ ስለ ነበርና ፣ እንዲህ ዐይነቱን ቆሻሻ ነገር ብነግርህ ይከፋህ እንደ ነበር ስለ ማውቅ አልነገርኩህም" አለ አበበ ። ዛሬ ይንጠስለት ብሏል ፣ 'ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል' እንዲሉ አክስቴ የሠራችውን በደል በምሬት እያስታወስ ። ፍስሐም ሲናደድ ጊዜ ስካሩ ሁሉ እልም ብሎ ሲጠፋ ጊዜ መናደድ ፣ መናደድ አለው ።

"ታዲያ አክስትህ ዋስ አልሆንህም ስላለችህ ፣ ዝምድናዋ ተፋቀ ማለት ነው ?" ብሎ በቁጣ ጠየቀው ።

"እናትህ የሠራችኝ ሥራ ቀላል አይደለም ። በቁሜ ነው የቀበረችኝ ። የኔና የኔ ዝምድና ያከተመ ከሰባት ዓመት በፊት ነው ።" አበበ እስከ መጨረሻ ሊነግረው ቆርጧል ። ይሆን አጋ ጣሚ በከንቱ ሊያሳልፈው አልፈለገም ። ፍስሐ ሳያውቅ የቆ ሰቆሰው እሳት አበበን ፈጀው ። ራሱንም አንሜረረው ። ለክብር መቆርቆር የቤተሰብ ውርስ ስለሆነ ፣ ክብራቸው ሲደፈር አይ ወዱም ።

"ቀናህ እንዴ አቤ ? እኔ ትምህርቴን ጨርሼ በመመለሴ ቀናህብኝ እንዴ ! ይህ እኮ የዕድል ጉዳይ ነው ። ለምን በናቴ ታሳብባለህ ? እሷ እሺ ብላ ብትዋስህም ኖሮ ፣ የተሳፈርክበት አውሮፕላን ወድቆ ሊከሰክስ ይችል ነበር ። ያኔ በማን ታመ ርር ኖሮአል ? በሷ አታሳብ ። ዕድልህ ነው እንቅፋት የሆነህ ። ቆይ ቆይ ልንገርህ ። እኔ በሰላም በመመለሴ የተቆጨህ ትመስላ

ለህ ። ግን በጉዞ ላይ አደጋ ቢደርስብኝ ኖሮ ፣ ወይ ትምህርቴን ሳልጨርስ ብሞት ኖሮ ፣ 'ዕድሜ ላከስቴ እኔም ብሔድ ኖሮ እሞት ነበር' እያልክ ልታመሰግናት ነበር ። እዚያ እሰው አገር ሞቼ ብቀርልህ ኖሮ ፣ ደስ ትሰኝ ነበር ማለት ነው ። ቆይ አስጨርሰኝ እንጂ ..."

አበበ ፣ መንገዱን ሲቀጥል ፍስሐ ኩቴን ይዞ እየጐተተ አላ ስኬድ አለው ።

"ስማ ፍስሐ በንግግርህ ልታስደነግጠኝ አትሞክር ። 'ቀና ሀብኝ ወይ? ብሞትልህ ኖሮ ወዘተ...' የምትላቸው ቃላት አያስ ደነግጡኝም ። ዝም ብዬ መስማትም አላቃተኝም ። መስማትም ነበረብኝ ። ግን ዝም ብዬ ብሰማህ ብዙ ጉድ ታወራለህ ። ስማ ፣ ልንገርህ ፍስሐ ዘ በሰላም በመመለስህ ይችን ታክል አልቀና ሁም ።" አበበ አለመቅናቱን ሲገልጽ የትንሿን ጣቱን ጥፍር ባውራ ጣቱ ጥፍር እየጐረጐረ ፣ "እናትህ ዋስ አልሆንም በማ ለቷ ግን ዕድሴን ስብራዋለች ። የገንዘብ መውደድ በሽታ ባይ ጠናወታት ኖሮ ፣ እኔም ልጅዋ ነበርኩኻ ! ነፍሱን ይማረውና አባቴ ለገንዘብ ግድ አልነበረውም ። ቢፈልግ ኖሮ ከሷ የበ ለጠ መሰብሰብ ይችል ነበር ። እሷ ግን..." ንዴቱ እየባሰበት ሐዲና ሰውነቱን ላብ አጠመቀው ። ቶሎ ካልተለያየን የባሰ እን ጋጫለን ብሎ አሰበ ፤ ደሙ ሲፈላ መደባደብ እንደሚቀናው ስለሚያቅ ።

"ወደየቤታችን ብንሔድ ይሻላል" አለ አበበ አስተያየ ትም ፣ ትእዛዝም በሚመስል አነጋገር ፣ ካንደበቱ ቀዝቀዝ እንደ ማለት ብሎ ።

"እንግዲያውስ ልሸኝህ" አለ ፍስሐ የውሸቱን ። ውስጡን በሽቂል ።

"መሸኘትህ አያስፈልግም" ብሎ አበበ ወዲ ዱሮ ሰፈሩ መሐዲ ሲጀምር ብርድ ተሰማው ። ላቡ ሲደርቅለት ጊዜ ደረት ነፋስ ያመጣው ብርድ ቆጠቆጠው ፤ የጠጣው አረቂም በኖ የጠፋ

ወይም ያለቀ መስለው ። እና ፣ ጉሮሮውን ለማርጠብ እንዲሁም ንዴቱን ለማብረድ ወዶ እንድ ቡና ቤት ጉራ አለ ። በፍስሐ እየተናደደ ፣ ባክስቱም እየበሸቀ ብዙ ጠጣ ። ይህም አዲስ ስካር ፈጠረበት ። አዲስ የተፈጠረው ስካርም የተዳፈነውን ንዴት አነሳፈለበት ።

በተለይም ስለ አክስቱ ብዙ አወጣ አወረደ ። መጀመሪያ ስለሷ ደግ ደጉን እያሰበ ንዴቱን ለማብረድ ፈለገ ። ግን ምንም የቀ ለችለት ደግ ነገር ስለሌለ ፣ ክፉ ክፉው ብቻ እየመጣ ፊቱ ላይ እየተደቀነ አስቸገረው ። ሐሳብ በመጠጥ ይወገድ ይመስል ደጋ ግሞ ጠጣ ። እና ብዙ በጠጣ መጠን ፣ ያክስቱም ክፋት መቶ ዕጥፍ በዝቶ ታየው ። የወደፊት ኑሮው ደግሞ መቶ እጅ ተበላሽቶ ታየው ። ክፉ ሐሳብ መጣበት ። አክስቱን የመግደል ሐሳብ ። ''እሷ ዕድሴን እንዴ ሰበረችው ሁሉ ፣ እኔም ዛሬ የሷን ዕድል አሰብረ ዋለሁ ። ዕድሉዋን ብቻ አይደለም የሕይወቷ ፍጻሜ በዚች ሴሊት ይሆናል'' ሲል አሰበ ። አስቦም አልቀረ ። ሐሳቡን ነቅታበት ከቤቷ ትጠፋ ይመስል ፣ የብርጭቆውን አረቄ ጅው አድርጐ ጠጣና ከቡና ቤት ሒሳብ ሳይከፍል ዘሎ ሲወጣ ሲል 'ሒሳቤን' ብላ የቡና ቤቲቱ ሴት ሮጣ ተከተለችው ። አበር ሲደርስ ከኋላ ኮቱን ያዘችው ።

ይቅርታ እንኳ አልጠየቃትም ። ዐሥር ብር ሰጣትና መን ገዱን ቀጠለ ። ''አረ መልስ አለዎት'' እያለች ብትጠራው አል ሰማትም ። መስማቱን ሰምታታል ። ግን አልተመለሰም ።

ያክስቱ ቤት በገዳም ሰፈር በኩል ዐልፎ ፣ ወዶ ዮሐንስ የሚያስኪደውን አስፋልት መንገድ ተሻግሮ ትንሽ ትንሽ የኮ ረኮንች መንገድ አለው ። አበበ መንገዱን እንዴት እንዴ ሔደው አያውቅም ። ብቻ መታረቡ ነው ትዝ ያለው ። ከመቸኮሉ የተ ነሣ ፣ በፊት ለፊት በር ሔዶ ክፈትልኝ ብሎ ሊያንኳኳ ትንሽ ነበር የቀረው ።

'ልክ ዘመድ እንደሚጠይቅ ሰው መሰልኩ አይደል ?'' ብሎ አሰበና እንደ መሣቅ አለ ። ''በጓሮ በኩል መግባት አለ ብኝ ። እም ፣ በጓሮ በኩል ። ግን በምንድን ነው የምገድላት ?

አንቱ ? ኖኖ አይሆንም ። አልችላትም ። ደግሞ የጮኽች እን ደው የታሪዘኛለች ። በመግደል ሙከራ ከርቸሌ ታስገባኛለች ።' የዚህን ጊዜ ያባቱ ጠመንጃና ሽጉጥ ትዝ አለው ። አባቱ ባገል ግሎት የተሸለሙት ጠብመንጃ እዚያው አያቱ ቤት ነው ያለ ። ቤት አያቱ በክብር እየጠበቀች አስቀምጣለታለች ፤ ላውኑ ቁጭቱ ግን አይደርስለትም ። የዛሬን ቀን ግሳለፍ ግን አልፈለገም ። ተመልሶ ማምጣትም አላሰበ ። ብቻ ለትዝታው ያህል ትዝ አለው ። 'እንዴ ምንም ብዬ መኝታ ቤቷ ልግባ እንጂ በፍልጥ ወይም በዘነዘና አናቷን ብዬ እገድላታለሁ' አለ ። ልክ አብሮት ሳለው ጓደኛው የሚያማክር እንጂ የሚያስብ አይመስልም ነበር ።

በጓሮ በኩል ዘሎ ገባ ። ግቢው ልዩ ልዩ ዛፎችና አትክ ልቶች ፣ ያበባ ዕፀዋት አሉበት ። ከቤቱ ውስጥ በመስኮቶች ፍር ግርግ በኩል የኤሌክትሪክ ብርሃን ይታያል ። መተኛት አለመ ተኛታቸውን ማወቅ አልቻለም ። ያክስቱን መኝታ ቤት ስለ ሚያውቀው ቀስ እያለ ወደዚያው ተጠጋ ። ወዶ ውስጥ ለማ የት ሞከረ ። ግን አልሆነለትም ። ጉንበስ ብሎ ወዶ ሳሎን በኩል ሔዶ ። የሳሎኑ መስኮት መስተዋት ብቻ ነው የተዘጋ እና ቀስ ብሎ ቀና ብሎ እየ ። አክስቱ ጀርባዋን ለመስኮት ሰጥታ ተቀምጣለች ። ባልየው ከፊቷ ተቀምጧል ። የማደጉ ልጆች ድብብቆሽ ቢጨ ይጫወታሉ ። እናትና አባታቸውን እየ ዞሩ ፣ እየተሣሣቁ ። አበበ ቀና ብሎ እያየ ምልስ እያለ እንድ ሦስት ጊዜ አያቸውና ፣ ተመልሶ ወዶ አክስቱ መኝታ ቤት በኩል ሔዶ ። አሁኑኑ መስኮቱን ሰብሬ ካልጋዋ ሥር መደበቅ አለብኝ ብሎ መሰርሰሩን ቀጠለ ።

የዕንጨት መስኮቱ በደንብ አልተዘጋ ኖሮ ወለል ብሎ ተከፈተለት ። መስተዋቱ ግን በደንብ ተዘግቷል ። ቢለው ቢለው ፣ እምቢ አለው ። በድንጋይ ሊሰብረው ፈለገና የሚሰማ በት መሆኑን ገምቶ ተወው ። 'ደግሞ መስተዋቱ ኮሽ ሲል ሊሰሙ ይችላሉ' አለ ።

የመኝታ ቤቱ መብራት ገና አልበራም ። ወዶ መኝታ ቤቱ የሚመጣ ሰው ርምጃ የሰማ መስለው ። ቶሎ ቁጭ አለ ። በቀ ስታም ወዶ ኋላው አፈገፈገ ፣ የግድግዳውን ጥግ ሳይለቅ ።

የመኝታ ቤቱ መብራት በራ ። ከዚያም መስኮቱን ግጥም አድርጉ ዘጋው ። መጭውን ሰው በድምፅ መለየት አልቻለም ። ይሔድ አይሔድ ግን አላወቀም ። 'እስኪተኙ ድረስ ተደብቄ መቆየት ይናርብኛል' ብሎ አሰበ ።

በግምት ካሥር ደቂቃ በኋላ መስኮቱ ተከፈተና ፣ "መስኮቱን ከፈችውና ይናፈስ' አላታለሁ ዘግታው ትሔዳለች" ብላ ስትናገር ያክስቱን ድምፅ ሰማ ።

"ወየው ከፍተሽልኝ በሔድሽ" ብሎ ተመኘ ። ወዲያው የሕፃን ልጅ ድምፅ "እማዬ ዛሬም ካንቺ ጋር ልተኛ" እያለ ሲለምናት ሰማ። የሆነ ነገር እየተናገረች አክስቱ ከመኝታ ቤት ወጥታ ስትሔድ ርምጃዋን ሰማ ። ልጅዋም የተከተላት መሰለው ። እና አበበ ብድግ ሲል ከሕፃኑ ጋር ተያይ ። ሕፃኑ ልጅም 'ዋይ' ብሎ በድንጋጤ ጮኸ ። አባትና እናቱ እየተሩዋሩዋጡ መጡ ።

"ምን ሆነክ?"

"ሌባ" አለና ወደ መስኮቱ ጣቱን ቀስሮ አመለከታቸው ። የዚህን ጊዜ አበበ በሦስት ጊዜ ርምጃ ዛፎች ውስጥ ዘሎ ገባ። ያክስቱ ባል ከመኝታ ቤቱ ሽጉጡን እምጥቶ በመስኮት በኩል ዘለለና ወደ ጓሮ ሲሮጥ ሰማየ ፣ አበበ ከተደበቀበት ተነሥቶ አጥሩ ግንብ ላይ ወጣ ። ከዚያም ግንቡን ዘሎ ሊወርድ ሲል "ቁም" አለና ተኮሰ ። አበበ የኋሊት ወደ ግቢው ወደቀ ። "የት አባትክንስ!" ብሎ ደንፍቶ ሔደና በአግሩ ገልበጥ አደረገው ። ገና ያቃስታል ። ደግሞ ሊተኩስና ሊጨርሰው ሽጉጡን ካቀባበለ በኋላ ፣ መሞቱ አይቀርም ብሎ መልሶ ተወው ።

ከዚያም ሚስቱን ጠርቶ ባትሪ ይዛ እንድትመጣ አዘዛት ። እሷም ዘወትር ሲያስመርራት የነበረውን ሌባ ቆስሎ ለማየት ምኞቷ ስለነበር ፣ እየተጣደፈች ሳትቆይ ከተፍ አለችና "የትአለ?" ብላ ጠየቀችው ። ከመኪናቸው ውስጥ ሌሊት ቴፕና ዕቃዎች በተደጋጋሚ ስለ ተሰረቁ በሌቦች ላይ ቂም ይዘዋል ።

"ይኸውልሽ" አለና በእግሩ የሌባውን እንገት ቀና አደረገው ። ራቱ ላይ አበራችበት ። ስታየው በድንጋጤ ጩኸቷን ለቀቀችው ። እሱም ቢሆን ጩኸት ቀረሽ ድንጋጤ ነው የደነገጠው...

አዲሱ ሕልም

ኤልማ ፣ ቅዳሜ ጧት ከእንቅልፏ ስትነሣ ያስጨነቃት መር ካቶ ሐዶ የመገብየቱ ነገር ነበር ። ለወትሮው እንዴ ሽንኩርት ቃሪያ ፣ ክክ... የመሳሰሉትን የምትገበይላት ገረድዋ ነበረች ። ግን አክስትዋ ታመውባት ፣ ፈቃድ ጠይቃ ከሐዶች ሁለት ቀን አልፏታል ። ስለሆነም ኤልማ ብቻዋን ወደ መርካቶ ሐዲ ለመገብየት ግድ ሆነባት ። ደግነቱ ልጆችዋን አያታቸው ቤት ወስዳቸዋለች ። ቢሆንም የመሔዱ ነገር እስከዚህም ደስ አላሰኛትም ።

ኤልማ ፣ ወደ መርካቶ ስትሔድ የሚያስፈራት የሰዉ ግፊያ ነው ። ሰው ለምን መንገዱን እያየ እንደማይሔድ ዘወትር ይገርማታል ። መገረምዋ ግን የብሽቀት ነው ። ግዶ ግዶ እያየ ወይም ከመኪና ሽሽቶ ላይዋ ላይ ሲከመርባት፣ 'እያየህ እትሔድም!' ወይም ሴት ከሆነች 'እያየሽ እትሔጅም!' ብላ ትጮህባቸዋለች ። ግፊ ያውን በማሰብ ብቻ ገበያ መሔድ ያስጠላታል ። ዛሬም ግፊያው የሚያስከትልባትን ድካም በማሰብ ብቻ ፣ ገና ከቤትዋ ሳትወጣ ሐሞቱዋ ፍስስ አለ ። ቤት ውስጥ አስፈላጊው ቁሳቁስ ሁሉ እንዳለቀ እያወቀች ፣ ለገረዱዋ ፈቃድ መስጠቱዋ ምን ያህል እንዳገዳላት ተገነዘበች ።

ኤልማ ፣ እንደ ሌሎች ባለትዳር ቤቶች የባሉዋን መኪና ለመጠቀም አልታደለችም ። ጉረቤቶችዋ ሚስቶቻቸውን ጭነው በመኪና ወደ መርካቶ ሲሔዱና ገብይተው ሲመለሱ እያየች ትቀናለች ። ሁለቱ ልጆችዋ ከመወለዳቸው ፣ ማለት ከዘጠኝ ዓመት በፊት ዘመድ ጥየቃም ሆነ ገበያ መሔድ ስትፈልግ ባልዮው ያደርሳት ነበር ። ያኔ (በያኔው ትዝታ ተሸፋፍኖ ይቀመጥና) ልጆች ከተወለዱ በሁዋላ ችላ ማለት መጣ ። የጋብቻቸውን ነገር ባሰበች ቁጥር ሁሉ ልቧ በጎዝን እንደ ተሰበረ ነው ።

ብዙ ሰዎች 'ቆንጆ ነሽ' ብለው ነግረዋታል ። ባይነግሩዋትም ቆንጆ መሆኗን ራሷም አላጣችው ። እንደ መስተዋት ክብ የሆነው ፊቱዋና ውብ ጥርሶችዋ የብዙ ወንዶችን ዐይን ይስቡ እንደ ነበር ታውቃለች ። እንዲያውም ትምህርቱዋን ከዐሥረኛ ክፍል

ለማቁዋረጥ ምክንያት የሆናት ይኸው ቁንጅናዋ ነው ። የትም ሀርት ቤቱዋ ጐረምሶች ፣ 'የኔ ነሽ—የኔ ነሽ' እያሉ ይጣሉባት ነበር ። አንዳንድ ጥጋበኞች ደግሞ ፣ መንገድ ላይ እየጠበቁ ያስረ ራሩዋታል ፤ 'እምቢ ካልሽ አንገትሽን ቀንጥሼ ነው የምጥልልሽ' እያሉ ። ኤልማ የሚዝቱባት ጎረምሶች እየበዙ በሔዱ ቁጥር ፣ ከትም ሀርት ቤት መቅረት አመጣች ፣ 'ከመሞት መሰንበት' ይሻላል ብላ ።

ኤልማ ፣ አንዳንድ ጐረምሳ ተማሪዎች ፣ ሴት ተማሪዎችን ሲጐዱ አይታለች ። በሱዋ ላይ ከዛቱት ከብዙዎች አንዱ ሳይጐዳት እንደማይቀር በደንብ ከተገነዘበች በሁዋላ ፣ ከትምህርት ቤት እያከታተለች መቅረት አመጣች ። ዐሥረኛን ሁለት ጊዜ ወደቀች ። ከዚያ በሁዋላ ደግማ ለመማር አልፈለገችም ። እኩዮችዋ በሁለት ክፍል ሲበልጧት ፣ ከሁዋላዋ የነበሩት ሲደርሱባት ተበሳጨች ። እንደ ሰነፍ ተማሪ አንድ ክፍል መደጋገምዋ ስላበሸቃት ከነ ጭራሹ ተወችው ። ለዚህ ሁሉ ሰበብ የሆናት የገዛ ውበትዋ መሆኑን ዐውቃለች ። ውበትዋ መጥፊያዋ ሲሆን ጊዜ ፣ ምን ታድ ርግ? ሌላ ትምህርት ቤት ገብታ ትምህርቱዋን እንድትቀጥል የመከራት ገብሩ የሚባለው የክፍል ጉዋደኛዋ ነበር ። የሱ ጓደኝነትና ፍቅር ብቻ ነው በአእምሮዋ ተቀርጾ የቀረው ።

ልክ ትምህርቱዋን በተወች በሦስት ዓመቱዋ ባል አገባች ። ያኔ ኻያ አንድ ዓመቱዋ ነበር ። የዛሬው ባሏ መጀመሪያ ሲተዋ ወቋት ፈርታቸው ነበር ። የራስ ጸጉራቸው ከአናታቸው ሸሽቶ በስተጀርባ በኩል አለው ዳገት ሥር ደርሱዋል ። የራስ ቅላቸው የወጥ መቀቀያ ምንቸት ያክላል ። ደግሞ የተወለወለ የቅቤ ቅል መስሎ ሲያብራኮርቅ ስታይ ሳቁዋ ይመጣባትና ፣ 'እውነት ይሽ ሰው ባሌ ሊሆን ነው? የራሴ የግሌ ብየ የምኮራበት የወዴታ ባሌ ይህ ነው?' ብላ ታስብ ነበር ። ግን መጋባታቸው አልቀረም ። ለወላጆችዋ ሸክም መሆንና ቤት ውስጥ መቀመጥ ሰልችቱዋት ስለነበር ፣ ባል እንዲሆኗት ፈቃደኛ ሆነች ። ፈቃደኝነቱዋን ለመግ ለጽ ግን ፣ ብዙ ሴሊቶች ያለ እንቅልፍ አሳልፋለች ። ብዙ ሴሊቶች ከራሱዋ ጋር መክራለች ።

ከተጋቡ በሁዋላ ፣ አቶ ተሰማ ጠዋት ወደ ሥራ ሲሔዱ ኤልማን ግንባርዋ ላይ ሳም ያደርጉዋታል ። ከሥራ ሲመለሱም

እንዲሁ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ታፍር ነበር ። ቀስ በቀስ ኃፍረቱ እየተዋት ሲሔድ ፣ አጸፋውን መመለስ ጀመረች ። 'ቸር ያውልሽ—ቸር ያውልህ' ተባብሎ መለያየት ፣ የሚዋደዱ ባልና ሚስቶች በጐ ልማድ መሆን እንደሚገባው ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልወሰደባ ትም ። ለዚሁ ነው ውላ አድራ የሚወደድ ልማድ ያደረገችው ።

አቶ ተሰማ ፣ የመንግሥት ሠራተኛ ናቸው ። ሥራ በጣም ይበዛባቸዋል ። ከሰኞ እስከ ዓርብ መባከን ነው ። ቅዳሜ ከሰዓት በሁዋላና እሑድ ቤት ውስጥ ቢውሉላት ፈቃዱዋ ነበር ። ግን ጓደኞቻቸው ከተፍ ይሉና ጥሬ ሥጋና ጠጅ ፍለጋ ይዘዋቸው ይሔዳሉ። ገበያ አብረው እንዲሔዱ—የዕረፍት ጊዜአቸውን ዘመድ በመጠየቅ ወይም ሲኒማ በማየት እንዲያሳልፉት ደጋግማ ጠይቃ ቸው ፣ 'ዛሬ ብርቱ ጉዳይ አለብኝ ፣ ሌላ ጊዜ' ብለው ጓደኞቻቸ ውን ፍለጋ ይሔዳሉ ፣ ድንገት ቀድመው ከመጡ ። ከነሱ ጋር ከተገናኙ ቶሎ አይለያዩም ። ቀኑን አብረው ውለው ሌሊቱን ካጋ መሱ በኋላ ነው የሚሳቀቁ ። በተለይ ልጆች ከወለዱ በሁዋላ እየባሰባቸው ሔደ ።

አንድ ቀን ዘመድ ሞቶ መርዶ ተነገራት ። እሑድ ጠዋት ነበር ። ባልየው መርዶውን ሲሰሙ ተናደዱ ። በሳምንት አንድ ቀን ብቻ የሚመጣውን እሑድ ለቅሶ ቤት ተቀምጠው ማሳለፍ አይፈልጉም ። ሹልክ ብለው ሊወጡ ሲሉ ፣ ''ለቅሶ እንድረስ እንጂ ወዴት ልትሔድ ነው?'' አለቻቸው ። በዕድሜ ቢያጥፉዋ ትም ፣ ጸጉራቸው ከራሳቸው ላይ ቢያልቅም ፣ አንተ ነው የምትላ ቸው ።

''አሁን አንቺ ሒጂ ፣ ብርቱ ጉዳይ ስላለብኝ በኋላ እደርሳ ለሁ'' ብለዋት ውልቅ አሉ ። ይህ ግን ያንድ ቀን ድርጊት አል ነበረም ። ተደጋግሞ ያርሱዋል ። ታዲያ ኤልማን ያበሸቃት መዴ ጋገሙ ነው ። ሆኖም የተናደደችበትን ነገር ለወላጆቹዋ እትን ግራቸውም ። ባልዮው ከለቅሶ ሲቀሩ ፣ 'እምት ነው' ወይም ደግሞ 'ብርቱ ጉዳይ አጋጥሞት ነው' ኢያለች በምክንያት ትሸፋፍንላ ቸዋለች ።

ኤልማ ፣ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉዋት ። ትልቁዋ ዘጠኝ ዐመቱዋ ነው ። ትንሹዋ ደግሞ ሰባት ። ልጆች ብትወልድም ውበ

ትዋ አልደበዘዘም ። ልጆችዋን መንከባከብ እንጂ መጊያጌያጡን ትታዋለች ። ልጆችዋ የሷን ዐይነት ዕድል እንዲገጥማቸው አት ፈልግም ። በወጉ ተምረው ፡ ሥራ ይዘው ፡ ነጻ ኑሮ እንዲኖሩ ለማገዝ ራሱዋን መሥዋዕት ለማድረግ ቆርጣለች ። የጐረምሳ ዐይን ባረፈባት ቁጥር ልቡዋ ሴላ ነገር ቢመኝም ፡ ምኞትዋን በሆዱዋ አምቃ ትይዘዋለች ። ሁለት ጊዜ መውደቅ ስለማትፈ ልግ ነው ። ለትምህርቱዋ እንቅፋት የሆናት ውበትዋ ፡ ለትዳሩዋም እንቅፋት እንዲሆናት አትፈልግም ።

ሽማግሌ ባል መምረጡዋ ከመባከንና ከቅናት ለመዳን ፡ ከንትርከና ከጭቅጭቅ ለመዳን ፍቱን መድኃኒት ነው ብላ ነበር ። መሳሳቱዋ የገባት በሁዋላ ነው ። በርግጥ ባሉዋ አይጨቀጭቁ ዋትም ። ግን ችላ ብለዋታል ። መጠጥ ቤት አምሽቶው ሴሊቱ ሲጋመስ ነው ወደ ቤታቸው የሚገቡ ።

ኤልማ ፡ ያለፈውንና ያሁኑን እያሰላሰለች ልብሱዋን ከለላባ ብትና ቁርስዋን ከበላች በሁዋላ ወደ መርካቶ ሔደች ። የገዛች ውን ዕቃ አንድ ደንበኛዋ ሱቅ እያስቀመጠች ደግሞ እየገዛች ፡ እያስቀመጠች ገብይታ ከጨረሰች በሁዋላ ፡ የልጆች ልብስ ለመ ግዛት ወደ ገበያ አዳራሽ ጎራ አለች ። አዳራሹ ውስጥ ካንዱ ሱቅ ወደ ሌላው እየተዘዋወረች ማየት ጀመረች ። አዳራሹ ውስጥ የምትዘዋወር በቀስታ ስለሆነ ማፊያው አያስለቅጥም ። ካንዱ ሱቅ ወደ ሌላው እየሔደች ጠየቀች ። የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ ነጋዴዎች ዕጥፍ ዋጋ መጠየቅ ጀምረዋል ። ሚያግው ፡ ሹራቡ ፡ ሸሚዙ ፡ ቀሚሱ ... ዋጋው ከወትሮው በዕጥፍ የጨመረ በመሆኑ አበሸቃት ። ልጆችዋ አዲስ ልብስ ሳይገዛላ ቸው ዓመት በዐሉ እንዲያልፍ አትፈልግም ። ላንዱዋ ገዝታ ለሌላዋ አለ መግዛት ደግሞ ፡ ሆን ብሎ ጠብ እንደ ማብቀል ይቁጠራል ። በቂ ገንዘብ ይዛ ባለመውጣትዋ እየተቆጨችና በአ ንድ የልጆች መደብር ውስጥ የተደረደሩትን ዕቃዎች በስተውጭ ሆና ስታይ ሳለ ጀርባዋን ከበዳት ። እና ፡ ዞር ብላ አየች ። አንድ ወንድ አጠገብዋ ቆሟል ። ስታየው ደነገጠች ። የምታውቀው መሰላት ። ካጠገቡ መሔድ ፈለገች ። ግን ምን እንደ ነካት ሳታ ውቀው ጐኑ እንደ ቆመች ቀረች ።

ገብሩ 'ሴባ' ፈገግታ እያሳየ ሲቀርባትና የሴት ልጅ ፍቅር የተራቡትን ዐይናቹን ስታይ ፡ መሸሽ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘች ውም ። እንዲያውም በውስጡዋ ደስ የሚል ርጋታ ነው የተሰ ማት ። እቤም የልቡዋን ለልቡዋ እየደበቀችው ነው እንጂ የሞቀ ገላ መመኘቱዋ አልቀረም ። ግን ደግሞ ባልዋ ቢተዋትም ፡ በት ዳር ላይ መወሳሰት 'ሴብነት' ነው ኢያለች ትታዋለች ። ወንዶች በጠየቁዋት ቁጥር ግን ለሕሊናዋ ፈተና መሆናቸው አልቀረም ። እንዲህ እንደ ዛሬው ግን ፡ የምንቸገረኝነት ጠባይ አሳይታ እታ ውቅም ። ልቡዋ እንደ ቅቤ መቅለጡ ለራስዋ ተሰምቱዋታል ። ቢሆንም ለወጉ ያህል ኮስተር ብላ ጠየቀችው ።

"ስውየ ምን መሆንህ ነው?" አለች ። ይህን የጠየቀችው ገብሩ እጅዋን ከያዛት በሁዋላ ነበር ።

"የኔ ቆንጆ! ይህን የመሰለ ውበት ይዘሽ ዐይን ከፈራሽማ ለምን መርካቶ ወጣሽ?" አላት ፡ እየሳቀና በቆየ አባባል እየተጠ ቀመ ። በመቀጠልም ፡ "ደግሞ እንዳንቺ ያለች ቆንጆ ዐይን ትፈ ራለች?... እንች ረስተሽኝ ነው እንጂ ፡ እንተዋወቃለን ።"

"የት ነው የምታውቀኝ?" ብላ ዐይናቹዋን ከፊቱ ላይ ሳትነቅል አስተዋለችው ።

"መድኃኔ ዓለም ትምህርት ቤት አብረን እንማር ነበር። ስምሽ ስለ ጠፋብኝና በርግጥ እንደ ረሳሽኝ ስላወቅሁ ዝም አልኩሽ እንጂ ካየሁሽኮ ቆይቻለሁ ። ገና አዳራሹን ገባ ከማለትሽ ነው ያየሁሽ ። ባጠገቤ ስታልፊ ቀና ብለሽ እንኳ አላየሽኝም ። እንደ ረሳሽኝ ርግጠኛ ሆንኩ ። እና ፡ ስኩተልሽ ቆየሁ ።"

ኤልማ ፡ ስሙ ቢጠፋትም የምታውቀው መሆኑ ትዝ አላት ። ውበቱዋን ከሚያደንቁና ብዙም ከሚያስቸግሩዋት ወንዶች አንዱ ገብሩ ነበር ። በትምህርቱ ጐበዝ ስለነበር ፡ እንዲያስጠናቸው የሚ ከቡት ሴቶችም ብዙ ነበሩ ። ግን እንደ ኤልማ የሚወዳት ሴት አልነበረችም ። እንደ ሴሎች ወንዶች በጉልበት አስፈራርቶ እጁ ሊያደርጋት አይፈልግም ። አስጠናኝ ብላ ብትጠይቀው ደስታውን አይችለውም ነበር ። ባጠገቡ ባለፈች ቁጥር ፡ 'ዛሬ ትጠይቀኛለች'

እያለ ተስፋ ሲያደርግ ፣ እሱዋ ግን ሳትጠይቀው ስትቀር ብዙ ቀናት አሳለፉ ። እሱም ከመጠን በላይ እየጐመጀላት ፣ አንድም ቀን አብሩዋት የመዋል ዕድል ሳይገጥመው ኤልማ ትምህርቱዋን አቁዋረጠች ። እረ ብዙ አሳፋሪ ሐሳቦች በአእምሮው ተመላልሰ ውበት ነበር ። አንድ ውለታ እንዲውልላት ስትጠይቀው — ወይም እሱ ሥራ ይዞና ገንዘብ ኖሮት ፣ እሷ ተቸግራና ተረጅ ሆና አጋጣሚ ሲያገናኛቸው — እና እሱ በገንዘቡ ወይም የውለታውን አጋጣሚ ተጠቅሞ ወዳጁ ሲያደርጋት ለማየት ያስብ ነበር ። መቸም ሐሳብ መሆኑ ጠቀመው እንጂ ፣ ሐሳብ ባይሆን ኖሮስ አሁን ፊት ለፊት ሲገናኙ ኃፍረቱ አንገቱን ባስደፋው ነበር ።

አንዲት ሴት አይቶ ደስ ካለችው ፣ የትም የትም ብሎ እንደሚተዋወቃት ፣ ት/ቤት በነበረች ጊዜ ትሰማ ነበር ። አነጋገሩም ፣ አቀራረቡም ደስ ይላል እየተባለ ይወራለት እንደ ነበር ትዝ አሳት ። ያኔ ቢጠይቃት ኖሮ ፣ ጓደኛው ለመሆን አታመነታም ነበር ። ግን ሲግደረደር ቀረችበት ። እሷም በነገሩ አልተገረመችም ። ከትምህርት ቤት ስትቀርና ሦስት ዓመት ከወላጆችዋ ጋር ስትቀመጥ ውስጧም ነገር ረሳችው ። እንኩዋን ገና ያላፈቀረችውን ገብሩን የእውነተኛ ፍቅረኞቹዋን እንኩዋ ረስታቸዋለች ። ሰውን መዋላት እንደማይሆንላት ሁሉ ፣ አንድን ፍቅረኛ በአእምሮ ቀርጾ መያዝም አይሆንላትም ።

"በጣም ተለውጠሃል ። ጭራሽ ሌላ ሰው ሆነሃል ። በረሃ አገር ናረህ ነው እንዴ የመጣህ?" በማለት ፊቱን እያስተዋለች ጠየቀችው ።

"አረ ምንም ያህል አልተለወጥኩም ። ዱሮም አንች ለሰው ደንታ ስለሌለሽ ፣ ዘንግተሽኝ ነው እንጂ...ብቻ፡ የኔን እንተወው። አንች ግን ምንም ያህል አልተለወጥሽም ። ውበትሽ እንዳለ ነው ። ቤት ውስጥ እንደ በቀለ አበባ የቀትር ፀሐይ የዳሰሰሽ አትመስ ይም" አላት ። ይህ አነጋገሩ የዱሮውን ደስታዋን ቀስቀሰባት ። እና ፣ 'ለመልካም አነጋገሩ ሲባል ፣ ለጨዋታ ዐዋቂነቱ ሲባል ፣ አዲስ ጓደኝ ት ከሱ ጋር ቢመሠርቱ ምንም ጉዳት የለበ ትም ፣ ብላ አሰበች ። እሱም ፊቱዋን አይቶ ልቡዋን ያነበበ ይመ ስል እያጫወተ ተጠጋት ። ከዚያም ለቆት የነበረውን እጅዋን

እንደገና ያዝ አድርጎ ፣ "ይህን የመሰለ ውበት ይዘሽ ወንዶችን መሸሽ ታጢአት ነው ። ውበትሽን የጋን ውስጥ መብራት አታድርጊው ። ብቅ በይ ፣ ይታይ ። ወንዶች ይህን ውበትሽን አይተው ይደሰቱ" አለና የያዘውን እጅዋን ጠበቅ አደረገው ። የራሱ ድርቅና ለራሱ እስኪያስጠላው ድረስ ሙዝዝ ማለቱ ተሰማው ። ይህን በመናገሩ ንቃውና ገፍትራው የምትሔድ መሆኗን አምኖ ነበር ። እንዲህ ብላ ስትናገረው ላለማየት ፊቱን አዞረ ።

ድርቅናው እሱዋንም ቢሆን አላስደሰታት ። ገበያ መክል እንዲያ ዐይነት ነገር መኖሩና እኳኋኑ ሁሉ የሚያሳፍር መሆኑ ተሰምታት ነበር ። 'ወግድልኝ አልፈልግህም' ልትለው ፈለገች ። ግን እንደቤቱዋ አልታዘዝ አላት ። እንዲያው ፍዝዝ ብላ እየችው ። እንደ ሐሳቡዋ ቢሆን ኖሮ ፣ መንጭቃው ብትሔድ ደስ ባላት ነበር ። ግን ባንድ በኩል ማመናጨቅ የሚባለው ነገር ከእንደሱዋ ዐይነቱ ጨዋ ሴት የሚጠበቅ አይደለም ። በሌላ በኩል ደግሞ ጥንት ትምህርት ቤት የምታውቀው ሰው ነው ። ለማናቸውም 'ደኅና ዋል' ብላው በመልካም እንደበት ተሰናብታው ለመሔድ አጋጣሚውን ስትጠብቅ ፣ ገብሩ ግን ተሰናብታው እንዳትሔድ መንገዱን እየዘጋባት አስቸገራት ።

ገብሩ ፣ የተማሪነት ዘመን ጠባዩ ባሁኑ ጊዜ ተለውጧል ። እንዲያው ለጉዳዩ በመንገድ ሲሔድ እንኳ ፣ በሐሳብ ተውጦ የሚረግጠውን መሬት ሳያስተውል በሚሔድበት ጊዜ እንኩዋ እንዲያው በደመ ነፍስ አንዲት ሴት ሲከተል ፣ ወይም ቆሞ ዳሌዋን ሲያደንቅ ይነቃል ። የሚከተላት ሴት ቆንጆ ከሆነች መመዘኛውን ታሙዋላለታለች ። ለምን ጉዳይ እንደ ወጣች ፣ ወይት እንደምትሔድ ፣ ትዳር እንዳላትና እንደሌላት ማወቅ የሱ ጉዳይ አይደለም ። እሱ ያለበት ተለማምጦ ሐሳቡዋን ማስለወጥ ነው ። እና የፍትወተ ሥጋ ረሃቡን ማስታገሥ ። ኤልማ ይህን ጠባዩን አታውቅለትም ። ለሱዋ እንደ ተማሪነቱ ጊዜ መልካም ጠባዩን ይዞ የሚገኝ መስላታል ።

ገብሩ ፣ ይህን ጠባዩን እያፍርበትም ። ጥሩ ወይም መጥፎ ተግባር መሆኑንም አስቦበት አያውቅም ። ለሱ ቆንጆ ሴት ቆንጆ ናት ። መንገድ ላይ ያግኛት ወይም ሱቅ ውስጥ ልዩነት አያመጣም ። የሱ ደስታ ማየት ፣ መከታተል ፣ መቅረብ ፣ ማነጋገር ወይም

ዳሌ መዳበስ ነው እንጂ ፣ በሞራል ወይም በፍልስፍና ዐይን ማየት አይደለም ። ፈቃደኛ ናት ወይም አይደለችም ፣ ልክ ነኝ ወይስ አይደለሁም የሚለው ጥያቄ አይደለም የሚያስጨንቀው ።

ገብሩ መልክ ቀና ነው ። ሴቶች በፈገግታው ይማረኩለታል ። ካንዲት ሴት ጋር አምስት ደቂቃ ካወራ ትሸነፍለታለች ። ሣቁና ፈገግታው በሴቶች ልብ ውስጥ ፍቅርና ርኅራኄን ይፈጥራል ። የሻከረውን ልባቸውን ያለሰልሰዋል ። አምስት ደቂቃ ካወሩት በሁዋላ ዕድሜ ልካቸውን ሳይለዩት ይመኛሉ ።

ኤልማና ገብሩ ፣ እጃቸውን ማለያየት አቅቷቸው ዐይን ለዐይን እየተያዩ ፣ በዐይን እየተነጋገሩና እየተግባቡ አሁንም እንዴ ቆሙ ናቸው ። እንዱ የሴላዉን ልብ የሚያነቡ ይመስላሉ ። በተማሪነቱ ጊዜ ቀርቶ ፣ አሁን ባልታሰበ ሰዓት መጠየቁ ግራ አጋባት ። ስንት ዐመት ሙሉ ሳይተያዩ ኖረዋል ። ያኔም ቢሆን ግንኙነታቸው ከሰላምታ ያለፈ አልነበረም ። ታዲያ ምን ነክቶት ነው አለችም ያላት፣ ለበጉ ወይስ ለጥሩ፣ ኤልማ አሁንም እጅዋን ለማስለቀቅ ሞከረች ። እሱ ግን እንዳታመልጠው ቁርጥ ውሳኔ ያደረገ ይመስላል ። ጉን ለጉን እየተራመዱ ፣ እንደገና እየቆሙ ፣ እንደ ገና እየተራመዱ መተያየት ብቻ ሆነ ።

"እየሁ ባለትዳር ስለሆንኩ መጠንቀቅ ይኖርብኛል ። እጅ ለእጅ ተያይዘን እንዳለን የሚያውቁኝ ሰዎች ቢያዩኝ..." አለ ችና አጠገቡዋ ያሉ ሰዎች እንዴ ሰሙና እንዳልሰሙ ለማረጋገጥ ተገላመጣ አየች ።

"እኔም ባለትዳር ነኝ" አላት ገብሩ ለማረጋጋት ። ከተገናኙ ከዐሥር ደቂቃ ባይበልጥም በሐሳቡ ብዙ መስሎ ተሰምቶታል ። የኤልማ መቅበጥበጥ በጣም ግራ አጋብቶታል ። እሺ ያለች ትመስ ልና ፣ የተረጋጋች ትመስልና እንዴ ገና ትበረግጋለች ። ትባንናለች ። ሻይ እንጠጣ ሲላት ሲል ፣ የፊቱዋን መረበሽ ያይና መልሶ ይተ ወዋል ። ሲያያት ሲፈልግ ደግሞ እንዳይሔድ በዐይንዋ የተማጠነች ው ይመስለዋል ።

"ባለቤቴ ይገድለኛል" አለችው ። አባባሉ የውነት ይሁን የውሸት ፣ የማራቅ ይሁን የማቅረብ ገብሩ አልገባውም ። ታናሽ

እኅቱን በሚያስመስል አያያዝ ትከሻዋ ላይ እጁን ጣል አድርጎ ካዳራሹ ወጣ ። ከዚያም እንዲህ ሲል ጠየቃት ።

"ምን ብሎ ነው ባልሽ የሚገድልሽ?"

"ከማንም ጋር ትግግጫለሽ ብሎ ነዋ !"

"መጀመሪያ ነገር እኔ ጓደኛሽ ነኝ ። የትምህርት ቤት ጓደኛሽ። እና ለጉዳዩ ገበያ ወጣሁ ። አንችም ለጉዳይሽ ገበያ ወጣሽ ። በድ ንገት ተገናኘን ። ታዲያ ከጥንት ጓደኛሽ ጋር አየሁሽ ብሎ ነው የሚገድልሽ?" አላት ። ኤልማ ለዚህ ምንም መልስ አልሰጠችውም። መልስ አጥታ አይደለም ፤ ከርከር መፍጠሩ አስጠልቷዋት ነው ፤ 'በጉንጭ - አልፋ ከርከር ጊዜ መግደል ምን ይመራል?'

"ሻይ እንጠጣ?" ብሎ ጠየቃት ገብሩ ፣ ዝምታዋን እንዴ እሺታ ቆጥሮት ፤ አምቢም እሺም አላለችው ። እንደገና ተሳበችለት ፤ ዝም ብላ ተከተለችው ።

ሻይ አዘው እንዴ ተቀመጡ ፣ "ባለትዳር ነኝ አልኩኝ?" ብላ ጠየቀችው ። መልሱ የጠፋበት ይመስል ዐይኖቹን ቦዘዝ አድርጎ ዝም አላት ። 'ባለትዳር ነኝ' ብሎ ከነገራት በሁዋላ ፣ መልሶ ዝም ማለቱ አንድ ሊናገረው የማይፈልገው ነገር መኖሩን እንድትጠ ራጠር አደረጋት ።

ገብሩ ፣ ሚስቱን ከፈታት ብዙ ጊዜ ሆኖታል ። ሁለት ልጅ ቹን የሚያሳድግ ሠራተኛ ቀጥሮ ነው ። ሚስቱ ከሔደች በሁዋላ እንዴ ልቡ ሆነ ። 'ጣጣው ቀረልኝ እንጂ ፣ እፎይ አልኩኝ እንጂ ፣ ምንም አልገዶለብኝ' አለ ። ቢፈልግ ይጠጣል ። ባይፈልግ አይጠ ጣም ። ቢፈልግ ሲዶንስ ያነጋል ። ባይፈልግ ቤቱ ያድራል ። ጠጭ ሴት ከገጠመችው ፣ ይጠጣል ። አንስከር ካለችው ይሰክራል ። ቀበጥ ሴት ከገጠመችው ሌቱን በሙሉ ስንዶንስ እንደር ካለችው ሙሉ ሌሊት ሲደንስ ያድራል ። ጠባዩ በየቀኑ ይለዋወጣል ። በዕለቱ ያገኛት ሴት እንዲሆንላት የምትፈልገውን ሆኖ መገኘት ነው ።

የሱ ጠባይ የማይለዋወጥ ከሰከረ በሁዋላ ነው ። አብዛኛው ጠጭ ከሰከረ በሁዋላ ልደባደብ ይላል ። ልጩህ ይላል ። ዕቃ

ልስበር ይላል ። ወይም መንገድ ላይ ወድቆ ሲለብቀው ያድራል ። ገብሩ ግን ፣ የማትለዋወጥ ጠባይ ናት ያለችው — ሴት ልቀፍ ማለትና ሴት ልጉንትል ከማለት ሌላ አያውቅም ። ሴት አጠገቡ ካለች በቂው ነው ። ግን አብሩዋት ያመሻት ሴት ባንዳች ምክንያት ጥላው ብትሔድ ችግር ላይ መውደቁ ነው ። ወይም በሰው እጅ መሞቱ ነው ። ይችን ሲገ-ትት ፣ ያቺን ሲገ-ትት ፣ ያገኛትን ሴት ሁሉ ልቀፍ ሲል ከወንድ ጋር ይጣላል ። ይህ ችግር ዶጋማ ደርሶበታል ። ግን ብዙዎቹ በክፋት ወይም በትዕቢት ሳይሆን በስካር መንፈስ ተገፋፍቶ እንዳደረገው ሲያውቁ አምረው አይጣሉትም ። እንዲህ ማለት ግን ፣ ዐልፎ ዐልፎ ጥፊ አይቀምስም ማለት አይደለም!! በጣም ሲያበዛው ከመጠጥ ቤት ተገፍትሮ ወደ ውጭ ይጣላል ። ደግነቱ መጠጥ የሚያመጣበትን ደካማ መንፈስ በመገንዘብ ብዙ አይጠጣም ። የምታጣጣው ሴት ካላገኘማ ፣ እንኳን እስኪሰክር ሊጠጣ ጨርሶ አይቀምስም ።

ኤልማ ፣ ከጓደኛ ጋር ሻይ መጠጣትና ብስኩት መብላት ነውር የለበትም ብላ ብትደፋፈርም ፣ ጉዳዩ በዚህ እንደማያከትም ታውቃለች ። በተለይም አውን ብቸኝነት ተጫጭኗት ባለችበት ወቅት ፣ ሰው በናፈቀችበት ወቅት የምታገኘው ወንድ ልቡዋን በቀላሉ እንደሚያሸንፋት ስላወቀች ነው ፣ እንደ ልቡዋ ዘና ብላ ልታጫውተው ያልሞከረች ። በጣም ጨንቃት ። ከባልዋም ፣ ከሰው አፍም ይበልጥ ያሳሰባት የጉዳዩዋ ነገር ነው ። የልጆችዋ ነገር ነው ። ይኸው ቀዝቃዛው ጉዳዩዋም ቢሆን የባሰ እንዲበላሽባት አትፈልግም ። ገብሩ ውስጡዋን ያነበበ ይመስል ለስላሳ ለስላሳውን ኬክ ወደ ፊቱዋ ያቀርብላታል ። ሐሳቡዋን በለስላሳ ኬክና በለስላሳ አነጋገር እያስረሳት ቆየና ዘና ስትል ፣ "በውነቱ አብዛኞቻችንክ በይሉኝታ ልጓም ታስረን በዘልማድ የምንኖር ነን ። ሐሜት ስንፈራ ፣ ሰው ስንፈራ ፣ ዐይን ስንፈራ ፣ ሁሉንም ነገር ስንፈራ ነው የምንኖር ። ግን ለምን እንዲህ እንደምንሆን አይገባኝም ። እኔ ለምሳሌ ባለትዳር ነኝ ልበል ። ልጆችም ይኖሩኛል ። ካንች ጋር እንደ ተቀመጥኩ ሚስቴ ብትደርስብን አልፈራም ። የትምህርት ቤት ጓደኛዬ እንደ ነበርሽ ነግሬ አስተዋውቃችሁዋለሁ ። ገባሽ?" አላት ።

"ይኸስ አይገባኝም ። ከሴት ጋር ኩተያዝክ በሁዋላ ደግሞ ድርቅናው ምንድን ነው? እንድ ትምህርት ቤት መማራችንና መተዋወቃችን እውነት ነው ። ግን ደግሞ መተዋወቅና መወሰለት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። ሰዎች ሁሉ የሚፈሩትና የሚጠሉት መወሰለትን ነው እንጂ ፣ አብሮ ሻይ መጠጣትን ወይም ማውራትን አይደለም" አለችው ። 'መወሰለት' የሚለውን ቃል መጥቀሱ ራሱ ለፈቃደኝነትዋ ፍንጭ መስጠቱዋ መሆኑ ተሰማት ። ነገር ለማሳመር ሳይሆን ፣ ቅን ለመሆን ስትጥር መሳሳቱዋ ቅር አለኛት ። ቅሬታዋን ለመግንዘብ ገብሩ ጊዜ አልወሰደበትም ። ቶሎ ሐሳቡዋን ካላስቀየራትና በውስጥዋ የሚመላለሰውን የሕሊና ወቀሳ በቶሎ ካላስወገደላት ፣ ጓደኝነታቸው እንደማይቀጥልና ምኞቱም እንደሚበላሽበት ገባው ።

"ሴቶች ስትባሉ ብዙዎቻችሁ መሠረት በሌለው ፍርሃት ተጠምዳችሁ ነው የምትኖሩ ። ፍርሃቱን የፈጠሩት ከናንተ በፊት የነበሩ ሴቶች ናቸው ። እናንተ ወርሳችሁት ነው ። እና ሴቶች ራሳቸው የፈጠሩት መሆኑን ትረሱና የሥጋታችሁ ምንጭ ባለመታቸው እንደሆኑ ሁሉ ፣ በነሱ ስታማርሩ ዕድሚአችሁን ትገፉ ታላችሁ ። ዘመድ አትጠይቂ ፣ ጓደኛ አትጠይቂ የሚል ባል የለም ። ግን ያንዱዋ ሴት ፍርሃት በሌላዋ እየተጋባ ገዘም ብላ ትፈራለች ። እንዲህ ዐይነቱ ፍርሃት የትዳር ጠንቅ ነው" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ ።

የገብሩ ንግግር ባዶ መሆኑን ብትገነዘብም ፣ በትዳር ያሳለፈችውን ሕይወቱዋን በሐሳቡዋ ለመሳል እንድትሞክር ኮርኩሮዋታል ። ግን ትዳሩዋ የደስታ ወይም የጎዘን ኑሮ ያስከተለባት መሆኑን ርእግጠኛ መሆን አልቻለችም ። በደብዛዛ ብርሃን እንዴ ሚታይ ምስል ውልብ ብሎ ከታያት በሁዋላ ፣ መልሶ እየተሰወረ ባት በውል መገንዘብ አቃታት ።

በሐሳብ የተገባቡ እየመሰሉና ፣ እንደገና እየተራራቁ ሲያወሩ ከቆዩ በሁዋላ ፣ ገብሩ ሒሳቡን ከፍሎ ከኬክ ቤት ወጡ ። ኤልማ ልትሰናበተው እጅዋን ስትዘረጋለት ፣ "እንዲሁ በባዶው" አላት፣ ዐይኖቹ በድንጋጤ እየፈጠጡ ።

"እና ፣ ምን ይጨመርበት?" በማለት እየገረማት መልሳ ጠየቀችው ።

"ማለቴ አድራሻሽን?" ኢያለ ይውተውታት ጀመር ።

"በል እሺ ጻፍ ፣ ስልክ ቁጥሬን ልስጥህ" ስትለው ገብሩ በእንቢታ ራሱን ነቀነቀ ።

"ሴላ ምን ትፈልጋለህ!" አለችው ።

"ላደርስሽ እፈልጋለሁ ፣ እግረ መንገዴን ቤትሽን ማወቅ ስለምፈልግ ። እስከ ዛሬ ሳላገኝሽ የኖርኩ አድራሻሽን ስላላወቅሁ መሆኑን ዐውቀሻል? አሁንም ቢሆን ሠፈርሽን ማወቅ እፈልጋለሁ ። ስልክ ምን ዋጋ አለው ፣ ብለሽ ነውን ቢበላሽኮ እንደ ተለያየን ቀረን ማለት ነው ። ምናልባት እውነት አይመስልሽ ይሆናል ። ግን በጣም ነው የምወድሽ ። ቢያንስ ዐይንሽን ማየት እፈልጋለሁ ። ዛሬ ተመለስ ብትይኝም አልመለስ" ብሎ አስተዛዝኖ ነገራት ። ቤቱዋ ድረስ አብሩዋት የመሔዱ ነገር ኤልማን እላስደሰታትም ። ግን ደግሞ የትምህርት ቤት ጓደኛዋ መሆኑን ስታስብ መልሳ ተጽናናች ። 'ዘመዴ ነው ብዬ ከባሉ ጋር አስተዋውቀዋለሁ ። ጓደኛዬ ነው ብለውስ ምን ይሆናል? ያም ሆነ ይህ አስተዋውቀዋለሁ ። ከዚያ የሚለኝን አሰማለሁ ። እንዴ በፊቱ እገርፍሻለሁ ካለም ቤቱን ትቸለት አሔዳለሁ' ብላ አሰበች ።

ኤልማ ፣ ደንበኛዋ ሱቅ ያስቀመጠችው ዕቃዋን መኪናው ላይ ከጫነች በሁዋላ ፣ ገብታ አጠገቡ ተቀመጠች ። መኪናው ውስጥ ከገቡ በሁዋላ ፣ ወሬ ያለቀባቸው ይመስል ወይም መነጋገር ያልፈለጉ ይመስል ፣ ዝም ዝም ተባብለው ጉን ለጉን ተቀመጡ ። ቀሚስዋ የባሰ አጥሮ ብርቱካን መሳይ ጭኖችዋ ተጋለጡባት ። ኤልማ ፣ የቀሚስዋን ጠርዝ ይዛ እየሳበች ጭኖችዋን ለማልበስ ትታገላለች ። ገብሩ ጭኖችዋን ሰረቅ እያደረገ ኢያየ ምን ዐይነት ወሬ ማውራት እንዳለበት ያወጣል ፤ ያወርዳል ። አንዲት ሴት ካንድ ወንድ አጠገብ በዝምታ ከተቀመጠች ፣ ሐሳብ ውስጥ እንደ ምትገባና ብዙ ማሰብ ደግሞ ሥጋት ማስከተሉ እንደማይቀር ተሰማው ። ግን ወሬው ሁሉ ጠፉበት ። ቀልዱ ሁሉ ጠፉበት ። "ሠፈርሽ የት ነው?" ብሎ ጠየቃት—የሚለው ሲጠፉበት ጊዜ ።

"ቦሌ መንገድ" አለችው ።

ገብሩ ፣ መኪናውን አስነሥቶ ፣ ከመርካቶ እግረኞች ጋር እየተጋፋ በዝግታ ሲያሽከረክር ቆየና ፣ ሲኒማ ራስ አካባቢ ሲደርስ ፍጥነቱን ጨምሮ ቁልቁል ተፈተለከ ።

"ቁልቁለት መንገድ ላይ በዚህ ዐይነት ፍጥነት መንዳት ጥሩ አይደለም ። የመገልበጥ አደጋ ወይም ግጭት ሊደርስ ይችላል" አለች ኤልማ ፣ የገብሩ አንዳድ ሥጋት ፈጥሮባት ።

"አትፍሪ ፤ አልጋጭም ። ፍርሃት ፣ ሥጋት ፣ ጭንቀት ፣ አሉ ጊዜአቸውና አለቦታቸው ብቅ እያሉ ሰዎችን ማስበርገጋቸው የተለመደ ነው" አላት ፣ ገብሩ ። 'ፈሪዎችን' የሚለውን ቃል 'ሰዎችን' በሚለው የተካው ፣ 'ፈሪ' አልከኝ ብላ እንዳትቀየመው ነው ። ይህ አባባል ክርክር ስለ ፈጠረላቸው ፣ ሠፈር እስኪደርሱ ድረስ 'ልክ አይደለህም ፣ ልክ አይደለሽም' እየተባባሉና እየተጨቃቀሱ ሠፈር ደረሱ ።

"በል አውርደኝ—ደርሻለሁ" ስትለው ደስ አላለውም ። ቶሎ መድረስ ሳይሆን ብዙ ማውራት ነበር የፈለገው ።

"የቤትሽን ግቢ መግባት አይፈቀድልኝም ማለት ነው?" ሲል ትሕትና በተመላበት አንደበት ጠየቃት ።

"ቅድም ሠፈርሽን ልየው ነበር ያልከው ። አሁን ደግሞ ቤትሽን ። ቢሆንስ መኪናህን ግቢው የማስገባት ግዴታ አለብህ እንዴ?" አሰኘው እየሳቀች ።

"ኧረ አልወጣኝም" አለ እሱም ፣ ፈቃድ በማግኘቱ ደስ እየተሰኘና ፈርጠም እያለ ፤

ኤልማ ፣ ዘመዴ ነው ብላ ከባሏ ጋር ካስተዋወቀችው በኋላ ገብሩ በቀን በቀን እየደወለ ሲያነጋግራት ፣ ሲቀጥራትና ከቤቱዋ በር ላይ እንደ ጭልፊት እየነጠቀ ሲወስዳት ሰነበተ ። ፍቅራቸው እየጨመረ ፣ በየቀኑ እየተነፋፈቁ ሲሔዱ ጊዜ ፣ ኤልማ ከገብሩ ብላ ዐረፈችዉ ! ። አንድ ሳምንት ፣ ሁለት ሳምንት ፣ አንድ ወር... እያለ

ተጠለ ። ገብሩ እምቢ እያላት ነው እንጂ ፣ በሐዲ ቁጥር ቤቱዋ ቢጋበዝና እዛው ተቀምጠው ቢያወሩ ደስ ባላት ነበር ። 'ተጠፋፍ ተን እንዳንቀር ነው ቤትሽን አሳይኝ ያልኩሽ እንጂ ፣ የመዝናኛ ቦታዎችን የማላውቅ መሰለሽ?' ብሎ አንድ ቀን ከተቆጣት በውዋላ ፣ ዳግመኛ ቤት ውስጥ እንዲጫወት ወይም እንዲጋበዝ ጠይቃው አታውቅም ።

አንድ ቀን ግን ፣ ኤልማ ራሱዋን ስላመማት ወዲ ውጭ አብራው እንደማትሔድ ነገረችው ። 'መቸስ ምን አደርጋለሁ' ብሎ ተከትሎአት ሲገባ ፣ ከልብ በመነጨ ደስታ ትፍለቀለቅ ጀመር ። የደም ሥሮችዋ ሁሉ ደስታ የሚያመላልሱ መሰላት ። 'አመመኝ ያለችኝ ስታብል ነው' እያለ ሲገረም ፣ የኤልማ ሣቅ ወደ ለቅሶ ተለወጠ ።

'ዐይነ ጥላ አለባት ወይስ አስማት ተደግሞባታል?' ብሎ አሰበ ገብሩ ። ከዚያም ''ለምን ታለቅሻለሽ?'' ብሎ ጠየቃት — ድንጋጤ ቢጤ እየተሰማው ።

''ምንም አልሆንኩ ። እንዲያው ደስ ስላለኝ ነው የማለቅስ'' ካንተ ከተገናኘሁ ጀምሮ ሕይወቴ ተለውጡዋል ። የሚሰማኝ ደስታ ሌላ ነው'' አለች እንባዋን በቀሚሱዋ ጫፍ እየጠረገች ። 'እንዲያውም ደስ ቢለኝ ነው ያለቀስኩ' ትበል እንጂ የውስጡዋን መረበሽ ገብሩም ዐውቋል ። ያስለቀሳት ደስታ ለመሆኑ እርሱዋም እርግጠኛ አይደለችም ።

''ደስታ ነው ያስለቀሰሽ ? እኔ ደግሞ መዓት ወረደብሽ ብዬ ! የደስታ ለቅሶስ ጥሩ ነው ። ቀጥይበት — ብዙ ሰዎች ደስታ የሚቅ ምንጭ ብቻ ይመስላቸዋል ። እኔ ግን ፣ ደስታ ለለቅሶ መነሻ ሰበቡ እንደሆነም አሳምሬ ዐውቃለሁ ። ደስታ ሲፈነቅለኝ አለቅሳለሁ ። ግን ደስታሽ ከምን እንደመጣ ዐውቀሻል ?'' ሲል ጠየቃት ፣ በእጆቹ ጭምር እያባበለ ።

''እንተን ስላገኘሁ ደስ ብሎኝ ነው ። ደግሞ ስለመጣህ ብቻ ያለቀስኩ አይምሰልህ ። ሰሞኑን ሁሉ አብረን ቆይተን ስንለያይ አልቅሽ አልቅሽ ይለኛል ። አለቅሳለሁ ። ባሌም ብሶ በታል ። በየመጠጥ ቤቱ ቅምጥ ሴቶች ሳይኖሩት አይቀርም። ሰሞኑን ደግሞ ውጭ ማደር አምጥቶዋል ። ልጆቹንም ረስቶዋቸዋል ። የመኝታ ሰዓት ሲደርስ ብቻ ነው ፣ የኛ መኖር ትዝ የሚለው ። ከትናንት ወዲያ ውጭ አደረ ። ለኔ ግድ እንደሌለው ከገባኝ ቆይቶዋል ። ለስሙ ባልና ሚስት እንባል እንጂ ፣ ለስሙ እንድ አልጋ ላይ እንተኛ እንጂ ማቀፉን ትቶኛል። ልክ እንደ ደባል ሲነጋ ይሔዳል ፤ ሲመሽ ገብቶ ይተኛል ። እሱ ምን ችገረው — የሚሰት ችግር የለበትም!'' ንግግሩን ሳግ አቁዋረጠው ። እንባዋም እንደገና መፍሰስ ጀመረ ።

ገብሩ ፣ ሁኔታዋን ሲያይ 'ለካ እውነትም ይቺ ሴት ተበድላለች' ሲል አሰበ ። ነገር ግን ፣ ስታለቅስ ማየት ያሳዘነውን ያህል ለኤልማ መጎዳት ትኩረት አልሰጠም ። እና እንዴ ሕፃን ልጅ እያባበለ ፣ እንደ እጎት ወይም እንደ ወንድም እየተቆጣ ለቅሶዋን ለማስተው ሞከረ ። በሐሳቡ ባልዋን መውቀስ ይዙዋል ። ኤልማን የመሰለች የፍቅር እመቤት ፣ ችላ ያለበትን ምክንያት ለማወቅ አእምሮው ብዙ ግምቶች የሚፋጩበት ጦር ሜዳ ሆነ ። 'ምናልባት ባልየው በዕድሜ ስለገፋ ይሆናል ። ወይም ከሱዋ የበለጠ ቆንጆዎች አስቀምጦ ይሆናል ። በሥራ ብዛት የደከመውን ሰውነቱን በመጠጥ ስለሚያደነዝዘውም ይሆናል ። ወይም...' እያለ ሲያስብ የኤልማ ለቅሶ መለሰው ። በደስታ የጀመረችው ለቅሶ ወደ ቁጭት ተለውጦ መላ ሰውነቱዋን ይንጠው ጀመር ።

''በቃሽ እንጂ ኤልማ !'' አላት ፣ ሁኔታዋ ባያስለቅሰውም አሳዝኖት ነበር ።

''እኔኮ ፈልጌ አይደለም ። እንባዬ ዝም ብሎ ይተናነቀኛል !''

''ዝም ካላልሽ እፈዳለሁ ። የኔን መንፈስ ጭምር አወክሽው ። አንችን የመሰለች ሴት ባየሁ ቁጥር ፣ ወይም ደግሞ ስምሽን በሰማሁ ቁጥር ላገኝሽ እመኝ ነበር ። እግዚአብሔር የልቤን ዐውቆ በድንገት አገናኘን ። እንድንቀራረብም አደረገን ። ታዲያ ፣ ከኔ ጋር ስትሆኚ ነው እንዴ አልቅሽ አልቅሽ የሚልሽ ።''

ገብሩ፣ እንባ እንዶ ተናነቀው ሰው ለመነፋረት ሞከረ ። ሐሳቡዋ እንዳልገባውና እንዳልተቀበላት ስታውቅ ፣ እንደ መከፋት አለች ።

"ብዙ ነገር ልነግርህ ፈልጌ ነበር ። ለቅሶዬ ባያስበረግግህ ኖሮ ። ከታመቀው ሐሳቤ ጥቂት ቆንጥሬ ባካፍልህ የሰላም እንቅልፍ ተኝቼ አድር ነበር ።"

"ብትነግሪኝ ባልጠላሁ" አለ ገብሩ ውስጡን 'ሒድ ሒድ' የሚለውን ሐሳቡን እያዳመጠ ። 'ይሽኔ ዝም እንዳለች ካልሔድክ ለቅሶዋን እንደገና ትቀጥላለች' ይለዋል ሐሳቡ ። "ብትነግሪኝ ባልጠላሁ" አለ ጮክ ብሎ ፣ "ግን ሰዓቴ እየመሸ ነው ። ጉን ለጉን ተቀምጠን ሳለ ፣ ባለቤትሽ ቢመጣ ሰላማዊ ኑሯችሁ ይበጠበጣል ብዬ እሠጋለሁ ። ራሴን አሞኛል ስላልሽኝ ገባሁ እንጂ ቤትሽ ውስጥ መጋበዝም ሆነ ፣ ማውራት ደስ አይለኝም ።"

"ከባለቤቴ ጋር አስተዋውቂሃለው አይደለም? ታዲያ ምን ድነው ሥጋቱ ?"

"ስነግርሽ! እዚህ ሠፈር መምጣቴ ደስ አይለኝም—እን ኳን ቤትሽ ውስጥ ተቀምጠ ማውራት ። ደግሞም ስለ ወዲድኩ ሽና እንዲከፋሽ ስለማልፈልግ ፣ ለኔ ደስ የማይሉኝን ነገሮች ላንች ስል አድርጌአለሁ ። ግን እቤትሽ ውስጥ መጋበዙን ጭራሽ አልወደውም ። ደስ አይለኝም" አለ ገብሩ ራሱን በዎ ራት እያርገፈገፈ ።

"እሱኮ ቤት የሚገባው በመንፈቀ ሌሊት ነው ። ከዚያ ወዲህ አይመጣም ። ቢመጣስ? ኧረ ይምጣ ። የስንት ዓመት ልማ ዱን ድንገት የሚቀይር ይመስልሃል? ቢቀይርስ? ቢመጣስ? ይምጣ!" አለች አንጋፋዋ ወደ አልህ እየተለወጠ ።

"ቢመጣማ ትዳራችሁ ይበጠበጣል" አለ ገብሩ ማስጠ ንቀቂያ የሚሰጥ ይመስል ፣ ሴባ ጣቱን ወደ አሱዋ እየቀሰረ ።

"እንዲህ አድርጉም ትዳር የለ ! የኛ ትዳር የውሸት ትዳር ነው ። ለልጅቱ ስል ነው የተቀመጥኩ እንጂ ፣ አሱ አይፈልገ

ኝም ። መቅናቱን እንኩዋን ትቶዋል ። ልጅት ከመውለዱ በፊት አፍቃሪ ባል መስሎ ለመታየት ይጥር ነበር ። ለወጉ የቁና መስሎ ለመታየት 'የት ዋልሽ' እያለ ይገርፈኝ ነበር ። ልጅቱን ከወለድኩ በውዋላ ግን ዞር ብሎም አላየኝ ። ያ ሁሉ ማስመሰል ቀረ ። እንዲያውም ዝም ዝም..." እንደገና ዝም አለች ። መቀጠል የፈ ራች መሰለች ።

"ለምን አልገረፈኝም ብለሽ ነው የምትበሳጭ?" ብሎ ጠየቃት ፣ እየገረመውና እየገረማት ።

"ማቀፉንም ትቶኛል ስልህ ። እስኪ አንተው ፍረዱው። ሠላሳ ዓመት እንኩዋን አልሞላኝም ። ቢሞላኝስ? ዐርባስ ቢሆ ነኝ? አሮጊት የሚያሰኝ ዕድሜ ነውን?"

ጥያቄውን በሆዱ መለሰላት ፤ አነጋገርዋ አውነት አለው ። 'ግን ምን ማድረግ ይችላል ! ሰማትስ አልሰማትስ ምን ይጠ ቅመዋል?' ገብሩ የልቡን ደስታ ሲያድን ፣ የተደበቀ ብሶት ሃን ፍሎ ሊያሰጥመው ሆነ ። በሰው ብሶት ሰጥሞ መቅረት አይፈ ልግም ። በየቀኑ አዲስ ደስታ ማግኘት እንጂ ፣ እንቅፋት እንዲ ገጥመው ጭራሽ አይፈልግም ። ሐሳብ ውስጥ የሚከት ወይም የሚያሳዝን ነገር ማየት አይፈልግም ። መሰማትም አይፈልግም ።

ገብሩ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ፣ "ልሒድ ። ሴላ ቀን ፣ ሴላ ቦታ በስፈው እንጫወታለን ። በውስጤ አንዳች መጥፎ ስሜት ተፈ ጥሮብኛል ። ምንነቱን ግን ሰይቼ አላውቀውም ። ምናልባት በነገርሽኝ ነገር ተነክቼ ይሆናል ። ወይም ጎዘንሽ የተኛውን የውስጤን ጎዘን ቀስቅሶት ይሆናል ። ግን ልሒድ" አለ ሰዓቴን እያየ ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆኗል ።

"በዚህ ሁኔታ እያየኸኝ ልትሔድ ነው ?" ስትለውና ሀይን ለዐይን ሲጋጩ አንድ ሆነ ። ገብሩ እጅግ አድርጉ አዘነላት እና ተመልሶ ተቀመጠ ። ሒድ ብላ ስታሰናብተውም ላለመ ሔድ በሆዱ ወሰነ ።

"ቅድም ብጠይቅህ ዝም አልከኝ ። እንደገና በድጋሚ ልጠ ይቅህ ። 'ሚስት አለህ ወይስ የለህም ?' " ብላ ጠየቀችው ፣ ሐሳ ቡን ቀይሮ በመቀመጡ ደስ እያላት ።

"ነበረችኝ!"

"ሞተችብህ!"

"አልሞተችም ። ሴት ትወዳለህ ብላ ፈታችኝ።"

"ሴት ትወዳለህ ማለት ነው?"

"እንዴት! መውደድ ቢሉሽስ ዳር ድንበር አለውን?"

"ታዲያ መጣላት ነው እንጂ ፣ መውደድ መጥፎ ነው እንዴ?"

"እኔ ምን ዐውቄ ። እንኩዋን እንድወድ ሌላ ሴት በዐይኔ እንዳይ አትፈልግም ነበር ። እኔ ደግሞ ዐመል ሆኖ ብኜ ቀንጂ ሴት ላይ መንፈሴ ይረበሻል ። በሽታ የሚጥላቸው ሰዎች አሉ አይደል? ጋኔን ነው መሰል የሚጥላቸው ድንገት ሳያስቡት መንገድ ላይ ፣ ወይም አሳት ላይ ፣ ወይም ባሕር ላይ እንደሚጥላቸው ሁሉ ፣ እኔንም ሴት ትጥለኛለች ። የሴት ሕመም መሆኑ ነው ። ሕመሙ የያዘኝ በቅርብ ጊዜ ነው ። ከማግባቴ በፊት ነው ። ለሱዋም ነግሬአት ነበር ። 'ቅንዝረኛ ነኝ ፣ ባል አልሆንሽም ልቅርብሽ' " አልኩዋት ።

"ግድ የለም አልቀናም ። ጨዋ ነኝ ብትለኝ ኖሮ ፣ ካንች ሌላ ሴት አላውቅም ብለህ ብታታልለኝ ኖሮ ነበር የምታናድደኝ ። ግልጽ ሆነህ ሳይህማ ይበልጥ እወድሃለሁ ። 'በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም' ሲባል አልሰማህም ? እያለች እንድንጋባ በየቀኑ ትወተውተኝ ጀመር ። በሁዋላ..." ሲል እቋረጠችው ።

"አንድ ጊዜ ቆየኝ ፣ ቀን ገዝቼ ያስተመጥኩልህ ቢራ ስላለ ላምጣልህ ። ወይስ ዐረቄ ይሻልሃል?" ብላው ተነሣች ። "እሺ ምንም አልፈልግ" አለ ገብሩ ፣ እሰው ቤት መጋበዝ ያስጠላዋል ።

"እንግዲያውስ ቢራ እመርጥልሃለሁ" ብላ ወዲ ገዋዳ ገባችና ቢራ ይዛ ተመለሰች ። ክፍታም ሰጠችው ። እሱም እምቢ ማለት አልደፈረም ።

"እሺ" አለችው የጀመረውን እንዲጨርስላት ።

"ዐመሴን ከነገርኩዋት በሁዋላም እንድንጋባ ወተወተችኝ ። እሺ ተይ አይሆንም ፣ ቅናት በሚሉት በሽታ ትለከፊና እጉል እንጣላለን ። ለኔ ግድ የለኝም ። ላንችም ግድ የለኝም ። ችግር ላይ የሚወድቁት ልጆቻችን ናቸው ፣ ድንገት ከወለድን ። አብረን ብንኖርም ፣ ብንለያይም ፍቅር ከሌለን ፣ ጭቅጭቅ ከተፈጠረ ፣ በአካልም በመንፈስም ቀጫጫ ሆነው ያድጋሉ ። እኔ እንደ ሆንኩ ዐመሴን አልተውም" አልኩዋት ።

"በሽታህን ግልጽ አድርገህ ነግረሃታላ" አለች ኤልማ በሆዱ እያዘነችለት ። ዱሮ በተማሪነቱ መንፈስ ጠንካራና ዓላማ ያለው ይመስላት ነበር ። ግን እውነተኛውን እሱነቱን ሲነግራት እጅግ አዘነችለት ። ለሱ ብቻ ሳይሆን እሱን ለመሳሰሉት የሰው ልጆች ሁሉ አዘነችላቸው ። ከንፈሩዋን ደጋግማ ስትመጥ ጊዜ እሱም እንዳዘነችለት ገባው ። ሲያዝኑለት ደስ አይለውም ነበር በፊት ። አሁን ግን ቢያዝኑለትም ባያዝኑለትም ግድ የለውም ። ቢሰድቡትም ፣ ቢያመሰግኑትም ግድ የለውም ።

"እሺ!..." አለችው አሁንም ያልጨረሰውን ታሪኩን ወይም ወሬውን እንዲጨርስላት ።

"እሷም ያለችኝ ይህንኑ ነው ። 'እንኩዋን በግልጽ ነገርከኝ እንጂ ፣ ይህን መጥፎ ጠባይህን ወይም ሕመምህን ሳላስተውህ አልቀርም ። እንዴ ምንም ብዬ አድንሃለሁ ። ከውጭ የምትፈልገውን ቤት ውስጥ ካገኘህ ሌላ ምን ትፈልጋለህ?' አለችኝ ።"

'እባክሽ የኔ በሽታ ፣ ማጣት ሳይሆን ሁሉን መፈለግ ነው ። ሆዳም ሲከሳ የሚያድር እየራበው መሰለሽ? የኔ በሽታ ቤት ውስጥ ማጣት ብቻ ሳይሆን ፣ በተገኘውም' አለ መርካት ነው። እና ተይ አልኩዋት ። ይቅርብሽ አታድኚኝም' አልኩዋት ።'እብሮ የቆየ በሽታ ሳይገድል አይተውም' ብዬ ብነግራት ፣ 'በኔ ይሁን ብህ' አለችኝና ተጋባን ።"

"ምንኛ በራሱዋ ብትተማመን ነው እባክህ?"

"ምናልባት ስለ ወደደችኝ ይሆናል" አለ ገብሩ ቢራውን እየተጎነጨ ፥ "ምናልባትም የወደደችው ግልጽነቱን ይሆናል ። እን ደኔ በግልጽ ድክመቱን የሚናዘዝ ወንድ የለማ ! እኔም የምና ዘዝ ወድጄ አይደለም ። ልደብቅህ ብለውም መታወቁ አይቀ ርማ ።"

"መሳሳቱዋ የገባት በሁዋላ ነው ። የወለድነው ልጅ ዓመት ሳይሞላው ተለያየን ። ይዛው ሔደች ። ከኔ ይልቅ እሱዋ ናት የምታስፈልገው ። ከኔ ይልቅ የናቱ ጡትና ፍቅር ነው የሚያ ስፈልገው" አለና እንደ ገና ለመሔድ ተነሣ ።

"በጣም ያሳዝናል" አለች ኤልማ ፥ ከንፈሩዋን እየመጠ ጠች ። "በጣም ያሳዝናል ። እና አሁን ብቻህን ነህ ማለት ነዋ!"

"እምን ብቻዬን ነኝ ። ከእንግዲህ እኔን የምታገባ ጤነኛ ሴት ያለች አይመስለኝም ። ጤነኛ ካልሆነች ደግሞ ፥ እኔ አል ፈልጋትም !"

ኤልማ ፥ የሚነግራት ሁሉ እውነት አልመሰላት አለ ። ገና ባሌዋን አይቶ ፥ እንደ ወደደችው አይቶ ለመሸሽ የፈጠረው ዘዴ መሰላት ። ዐውቆ ነው ራሱን የሚያጣጥል ብላ አሰበች ። እሱዋ የምታውቀው ገብሩና አሁን የሚያወራት ገብሩ ፥ ሁለቱ በጣም የተለያዩ ሰዎች ሆኑባት ። ከዚያም በፊት ሚስቱ ላይ መፍረድ ጀመረች — እንዲህ እያለች ።

"መፍታት አልነበረባትም ። የልጅ አባትዋን ? ውጭ እስካላደርክ ድረስ ፥ ወይም እንደኔ ባለቤት ሁሉ ጀርባ ሆን እየሰጠሃት እስካለተኛህ ድረስ ፥ በጭራሽ መፍታት አልነ በረባትም ። ለምን ቀናች ብዬ አልፈርድባትም ። ግን ደግሞ የልጅ አባትዋ እስከ ሆንክ ድረስ ቅናትዋን አምቃ መያዝ ነበ ረባት ። እንዲህ ነበር ማድረግ የነበረባት ።"

"ምነው ሴቶች ሁሉ እንዳንች በሆኑልኝ" አለ ገብሩ የስ ጠችው ፍርድ አንጀቱን አርሶት ። "'ብቻውን መብላት ለምዶ የልጅ እናቱን አባረራት ፤ ለመጠጣትና ለመስከር እንዲያመ ቸው የገዛ ልጁን ከቤት አባረረው ። ከልጅ ተለይቶ የበላው

ምግብ ምኑን ጤና ሊሆነው ነው ?'..." እኒህን የመሳሰሉትን ቶች፤ ጀሮውን እስኪሰለቸው ሰምቶ ስለ ነበርና ሕፃን ልጅ ከእ ቅፉ ተነጥሎ በመሔዱ ፥ ሁሉ የሕሊና ወቀሳ ውስጥ ውስጡን እሰልሰው በልቶት ስለነበር ዶስ አለው ። የሚስቱን ጥፋተ ኛነት ያረጋገጠችለት ኤልማ ብቻ ሆና ተገኘች ።

"በይ እንግዲህ ልሒድ" ብሎ ቢራውን ጨልጦ ተነሣ ።

"ልባድርግ! ነገ ከሥራ እንደ ወጣህ እዚህ መምጣት እን ዳትረሳ ፥ እጠብቅሃለሁ ። የምነግርህ ብዙ ነገር አለ ።"

"ነገክ እሑድ ነው !"

"ለካስ ነገ ኡሑድ ነው ። እንግዲያውስ ምሳሀን የምትበላ እዚህ ነው ። ጥሩ ምሳ ሠርቼ እጠብቅሃለሁ ።"

እሺም እምቢም ማለቱ ከበደው ። እሺ ቢላት ነገም ከነገ ወዲ ያም ፤ እንዲሁ እንዲያደርግ ልትጠይቀው ነው ። በሰው ትዳር ጣልቃ ሲገባ ቢገኝ ፥ ለባልና ሚስቶች መታታር ምክንያት መሆኑ ነው ። የራሱን ትዳር በመፍታቱ የሚወቀሰው እንሶ ደግሞ የሌላ ሰው ትዳር ማፍረሱ ለሰው አፍ ቀርቶ ለገዛ ሕሊናውም ከበደው ። እምቢ ቢላት መቀየሙዋ ነው ። ዶስ ብላዋለች ። በጣም ወዶአታል ። በምንም ዐይነት እንድትቀየመው አይፈ ልግም ። በስርቆትም ቢሆን ዐልፎ ዐልፎ ሊያያት ይፈልጋል ። ለማንኛውም ሴሊቱን ሲያስብበት እድሮ ፥ አስታራቂ ሐሳብ አገ ኛለሁ ብሎ ተስፋ አደረገ ።

"እንግዲያውስ ኤልማ ፥ እዚህ ሳይሆን ሌላ ቦታ እንገናኝ ፤ ጐረቤቶችሽ የኔን መኪና ሲያዩ ከየቤታቸው በመውጣት ቆመው ይንሾካሾካሉ ። ሰዎች ሲባሉ በማያገባቸው ነገር መግባት ልማ ዳቸው ስለሆነ ፥ ከመካከላቸው አንች ዶስ ብሎሽ የምትኖሪ እየ መሰላቸው ፥ የሚቀኑብሽ ስለማይታጡ ብንጠነቀቅ ይሻላል ። ለባልሽ የነገሩት እንደሆነ..."

"ምነው አንተ ይህን ያህል መፍራትህ ተዋደው ተጋብተው፥ ተዋደው የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ፥ በጣም ጥቂቶችና በጣም ዕድ

ለዋች መሆን አለባቸው ። ወረት ሳይለውጣቸው ፣ ቅናት ሳያ
ሸንፋቸው ፣ አብረው የሚኖሩ ካሉ ከጸጋ ይቁጠርላቸዋል ። ያው
ሆነ ይህ ለኔ አትዘንልኝ ። ብዙም አታስብልኝ ። ግን እዚህ
መምጣት ካልፈለግህ ሌላ ቦታ እንገናኝ ። ገመቢቶቼን ችላ በላ
ቸው ። እንደ ፈለጋቸው ይንሾካሾካሉ ። የፈለጉትን ወሬ ያንካ
ሩት ። በኔ የሚቀኑ ካሉ...''

''ቢታ ነገ በለባት ሰዓት ፣ ብሔራዊ ትያትር አጠገብ እን
ጂያውም በሩ ላይ እጠብቅሻለሁ'' አላትና ተጨባብጠውና ተሳ
ስመው ሲያበቁ ወጥቶ ሔደ ።

ገብሩን ከሸንቻ በሁዋላ ፣ ኤልሣ የመቅበጥበጥ ስሚት ተሰ
ማት ። የመደሰት ይሁን የመከፋት ፣ ለይታ ማወቅ አልቻለችም ።
እንደ ማልቀስ ወይም እንደ መሣቅ አሰኛት ። ተነሣች ። ተንጐ
ራደደች ። የቤቱን ዕቃ ሁሉ ስበሪ ስበሪ አሰኛት ። ራሱዋን
በግድ ተቈጣጠረችው ። ከዚያም ሶፋው ላይ ጥቅልል ብላ ተቀ
መጠና ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። ባዶ ቤት ውስጥ ያለ ገላጋይ
አለቀሰች ። ሲበቃት ለገብሩ ገዝታለት ካስቀመጠችው ዐረቂ
ቀድታ መጠጣት ጀመረች — ደረቁን !! ይህም እንቅልፍ በቶሎ
እንዲያስወስዳት ዐውቃለች ። ያንለት ማታ አልጋዋ ላይ ተጋ
ደማ ብዙ ማሰብ አልፈለገችም ። ባለፉት ቀናት ብዙ ሴሊቶች
ያለማቋዋረጥ አስባለች ። ራሱዋን አስክትጠላው ድረስ ፣አብ
ዳለሁ ብላ እስክትፈራ ድረስ በሐሳብ ተጨንቃ ነበር ።ለዚህ ነው
ደጋግማ የጠጣች ። ባሉዋ ከመግባቱ በፊት እንቅልፍ እንዲወስዳት
ያው እንደ ተለመደው በራሳቸው መክፈቻ ከፍተው ይገባሉ ።

እንደ ተለመደው ፣ ሴሊቱ ከተገባደደ በሁዋላ ነው ባልዮው
ወደ ቤት የገቡ ። ኤልሣ አልሰማቻቸውም ። እንደ ፍላጐቱዋ
ብዙም በሐሳብ ሳትንገላታ ነው እንቅልፍ የወሰዳት ። በሩን
ከፍተው መብራቱን አጥፍተው ሲተኙ ሁሉ አትሰማቸውም ።
ተቀምጣ እንድትጠብቃቸው እሳቸውም አይፈልጉ ። ይህን ጠባ
ያቸውን እስዋም ታደንቅላቸዋለች ። እንድም ቀን ከእንት
ልፉዋ ቀስቅሰዋት አያውቁም ። ርምጃቸውን ሳያሰሙ ይገባሉ፤
ድምፃቸውን አጥፍተው ይተኛሉ !! ዐልፎ ዐልፎ ወደ ልጆች
መኝታ ቤት ይገቡና ሳይተኙ ካገኙዋቸው ጥቂት ያጫውቱዋ

ቸዋል ። ተኙተው ከሆነም ድምፃቸውን አጥፍተው በጥንቃቄ
እየተራመዱ ከክፍላቸው ወጥተው ይሔዳሉ ። ምንም መጠጥ
እንዳልጠጣ ሰው ሳይንገዳገዱ ወይም ሳይለፈልፉ አልጋቸው
ላይ ወጥተው ጥቅልል ብለው ይተኛሉ ። ኤልሣን የገሪጥ አይ
ተው እንቅልፍ ወስዱዋት ከሆነ መብራቱን ያጠፉታል ። እም
ትሰማ ከሆነም ፣ እሱዋ እንድታጠፋው ይተዉላታል ። 'ፊት ለፊት
ከተያያችሁ ትሞታላችሁ' የተባሉ ይመስል ፣ እንዳቸው የሌላውን
ዐይን ይሸሻሉ ።

በነጋታው ፣ አስከ ምሳ ሰዓት ድረስ ኤልሣ እንድም ነገር
አላከናወነችም ። ቤት ክርስቲያን ለመሔድ አስባ ስለ ረፈደባት
ተወችው ። ከወላጆችዋ ቤት ልጆችዋን ለማምጣት አስባ ነበር፣
ቀጠሮዋን በማስታወሱዋና ሠራተኛዋም ሔዳ በመቅረቱዋ ፣ እዚ
ያው እንዲያድሩ ስለ ፈለገች መሔዱን መልሳ ተወችው ።

ልክ በቀጠሯቸው ሰዓት ከገብሩ ጋር ተገናኙ ። ቀድሞ
ከቦታው ደርሶ ስለነበር እየጠበቃት ሳለ በመድረሱዋ ፣ ምቅ ያለ
ፈገግታ ገና ከሩቁ ለገሠችው ። ራስ ሼል ገብተው ከትፎ ከበሉ
በሁዋላ ቁጭ ብለው ማውራት የሚያስችላቸውን ቦታ ለመም
ረጥ ምክክር ያዙ ።

'ማዮን እንሒድ' ሲላት አይሆንም አለችው ።ሴሎች ሦስት
ያህል ሆቴሎች ቢያማርጣት ፣ ''አይሆንም'' አለችው ። በመጨ
ረሻ የካ መንገድ ወደሚገኘውና 'ሐረጉዋ ሆቴል' ወደ ተባለው
ሆቴል ለመሔድ ተስማሙ ። ሆቴሉ ከመንገድ ወጣ ያለና ግቢው
ሰፊ መሆኑን ገብሩ ሲያስረዳት ፣ ኤልሣ ባላውቀውም የሚሻል
ነው ብላ በገለጸው መሠረት ተቀበለችው ። ግን ባለቤቱዋ የካና
ጉለሌ ፣ ጥሬ ሥጋና ጠጅ የሚገኝባቸውን ቤቶች ሲያዳርሱ እን
ደሚውሉ ስለ ምታውቅ ትንሽ ፍርሃት ገባት ። ድንገት መንገድ
ላይ ሲተላለፉ እንዳያዩዋት ነጠላዋን ተከናነበች ። ነጭ ኦፔል
ከፊት ለፊት ሲመጣ ስታይ ፣ ወይም ከኋላቸው መጥቶ አልፏቸው
ሲሔድ ፣ ልብዋ ድንግጥ እያለ አስቸገራት ። በድንጉጥኛ ደም
ፍላት ወይም በስካር ረብሻ ልፍጠር ማለታቸውና እሱዋንም ማዋ
ረዳቸው እንደማይቀር ስለ ገመቱት ነው ። መሸማቀቁዋን ሲያይ
ገዜ ገብሩ እዘነላት ።

"ምነው ፈራሽ ኤልማዬ?" ብሎ ጠየቃት ፡ እንገቱን ወደሷ መልሶና በቁልምጫ አመለካከት እያያት ።

"ይህን የከተማውን ዳር ዳር እሱም ይወደዋል ሲባል ስለ ሰማሁ ፡ ልቤ ድንግጥ ድንግጥ አለብኝ ። የሰይጣን ነገር ምን ይታወቃል ብለህ ነው ?"

"ከቤትሽ ስትወጪ ጊዜ ፍርሃት ተሰማሽ እንዴ ? ቤትሽ ውስጥ ስንሆን ደግሞ ቅሌቱ የባሰ ይሆን ነበር ። ስነግርሽ ለምን እንዳልገባሽ ገርሞኝ ነበር ። እንደገና በማያሠጋበት ቦታ መሥጋት ። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ልትነግሪኝ ትችያለሽ ? ምናል ባትም ትዳር ከያዝሽ በሁዋላ ፡ የደረሰብሽ መጥፎ ነገር ይኖር ይሆን? ትናንት ይሁን ፡ ከትናንት ወዲያ ባልሽ ይገርፍሽ እንደ ነበር ማውራት ጀምረሽ መልሰሽ ተውሽው ። እንዳንድ ጊዜ በወሬሽ መኻል ባልሽን የምትፈሪ መስለሽ ትታያለሽ ። እንዳንድ ጊዜ ደግሞ ግድየለሽነትሽ ያለቅጥ ይበዛል ። ለም ሳሌ ፡ እናንተ ቤት ምሳ እንድጋበዝ ስትጠይቂኝ ወይም ቁጭ ብለን እናውራ ስትይኝ!"

ገብሩ ፡ ይህን ሲናገር ሁሉ ፡ ለግማሽ ወይም ለሩብ ደቂቃ ፊቱን ወደሷ ይመልስ ስለ ነበር ፡ 'ይጋጭ ይሆናል' እያለች ሥጋት አስጨንቋት ነበር ። ንግግሩን አቁዋርጣ ተው ልትለው ትፈ ልግና አንዳች ነገር ምላስዋን እንደ ያዛት ሁሉ አንደበቱዋ አል ታዘዝ ይላታል ። በምትኩም ዐይኑዋን ትጨፍናለች ፡ ከፊት ለፊት ከሚመጣው መኪና ጋር ሲጋጩ ላለማየት ። በዚህ ዐይ ነት ሥጋትና ፍርሃት ተውጣ ስለ ነበር ፡ የነገራትን ሁሉ በትክ ክል አላዳመጠችውም ። ያዳመጠችውንም አልተረዳችውም ነበር ።

"ትዳር ከያዝኩ በሁዋላ ፡ የደረሰብኝ መጥፎ ነገር ካለ እንድ ነግርህ የጠየቅኸኝ መሰለኝ ፡ አይደለም ?"

"ነው ። ፍርሃትሽ ከባዶ ነገር የመጣ እንዳልሆነ ይሰማ ኛል ። ድፍረትሽም እንዲሁ ።'ቢመጣ ምን ቸገረኝ' ብለሽ ትና ንት የተናገርሽ ጊዜ በጣም ነው የደነገጥኩ ። ደግሞ ዛሬ ፍርሃትሽ ሌላ ሆኗል ። ለዚህ ምክንያት ይኖርሽ ይሆን? መቸም ምክን ያት እንስጥ ከተባለ ፡ ለማንኛውም ነገር ምክንያት ይኖረዋል"

አለ ገብሩ ፡ መኖሪያ ቤት ወደ መሰለና በዛፎች ወደ ተከበበ አንድ ግቢ መኪናውን እየነዳ ።

"ካልረሳሁት ስንቀመጥ እነግርሃለሁ ። እንደ መሰለኝ ቅድም የነገርከኝ ሆቴል ይህ ነው ። እንዴት ሰፊና ደስ የሚል ግቢ ነው ። እንዲህ ዐይነት ግቢ ውስጥ ብኖር በጣም ደስ ይለኝ ነበር" አለች የግቢውን ዙሪያ በዐይኗ እየዳሰሰች ።

ለጊዜያዊ መዝናኛ የመረጠው ግቢ ይኸው ያሉበት መሆ ኑን በቃላት መንገር አላስፈለገውም ። መኪናውን አቆመና መ ኮቶቹን ዘጋግቶ ሲወርድ ኤልሣም ወረደች ። ተያይዘው ወ ሆቴሉ ጓዳ አመሩ ። እንደየምርጫቸው ለሱ ጅን ፡ ለሱዋ ቢራ አዘው ከመጣላቸው በሁዋላ ፡ ሁለት ሦስት ጊዜ እስኪጉነጩ ዝም ተባብለው ተያዩ ። ገብሩ መንገድ ላይ ብዙ ለፈለፍኩ ብሎ ስላሰበ ፡ ጥቂት ዝም ለማለት ፈለገ ። ኤልሣ ደግሞ የታየሁ እንደሁ በጉዴ መውጣቴ ነው ብላ ፈርታ ስለ ነበር ፡ ፍር ሃቱዋ እስኪለቃትና ቀልቡዋን እስክትገዛ ድረስ ዝም ለማለት ፈለገች ። ግን ባይነጋገሩም ተግባብተዋል ። ቢሆንም ኤልሣ ያስ በችውን ያህል ብዙም ዝም ብላ ለመቆየት አልቻለችም ።

"ባለፉት ቀናት ውስጥ የሕይወቴን ጉዋዳ በርብሬ ያሳየ ሁህ መስሎኝ ነበር ። የማታውቀውን ያወቅህ እየመሰለኝ ፡ ያል ነገርኩህን የነገርኩህ እየመሰለኝ ሳወራህ ብዙውን ነገር እዘለዋ ለሁ ። አሁንማ ብዙ ዘመን አብረን የኖርን ይመስለኝ ጀምሯል ።"

"ምነው ድምፅሽ ተለወጠብኝ ። የሆነ መጥፎ ትዝታ መጥቶ ፊትሽ ላይ ተደቀነብሽ እንዴ ?" ሲል ጠየቃት ።

"ቅድም ጀምሬው የነበረውን ልነግርህኮ ነው ። ሁሌ ብቻ ዬን ስሆንና ሲከፋኝ የሚያስለቅሰኝ መጥፎ ትዝታ አለኝ ። ስለ ባለቤቴ እናት ነግሬሃለሁ ?"

"የለም አልነገርሽኝም ።"

"ባለቤቴ መጥፎ እናት አለችው ። ሳታውቀኝ ሳላውቃት ነው ፡ እኔን መጥላት የጀመረች ። እንዳንጋባ ከፍተኛ ጥረት አድርጋ ነበር ። ከተጋባን በሁዋላም እንዲፈታኝ ትመክረው

ነበር አሉ ። እኔ ግን የሰው ወሬ መስሎኝ...'' መቀጠል አል
ቻለችም ። ፊቱዋን የኮሶ መድኃኒት እንደ ጠጣ ሰው ፊት ቁጥ
ርጥር አደረገችው ።

የትናንትናው እንባዋ ፣ እንዲሁ ከባዶ ነገር እንዳልመጣ
ገብሩ አስቀድሞ ገምቶዋል ። ስሜትዋን የረበሸውን ነገር ተና
ግራው ካልወጣላት ዛሬም እፎይ እንደማትል ገባው ። መስ
ተዋት መስሎ ክብ ፊትዋ የልብዋን መከፋት ወለል አድርጉ
አሳየው ። የታመቀው ስሜቱዋ ገንፍሎ እንባዋ ከመፍሰሱ
በፊት ገና በቋፍ ላይ እያለ ታየው ። ሞቅታ እንዳልሆነ ገብ
ቶታል ። ገና አንድ ቢራ ጨርሳ ሳትጠጣ ሞቅታ ከየት ይመ
ጣል ? እንዲያው ሁሉም ነገር ቀርቶ ገብስ ገብሱን ቢጫወቱ ፣
ሥቀው ተሣሥቀው ቢለያዩ ፈቃዱ ነበር ። ያንዱን ሥቃይ
ለሌላው ማካፋሉ ፣ የራስን ብሶት ለሌላው ማሰማቱ ጭራሽ
ደስ አይለውም ። ግን ምን ያድርግ ? ዛሬ አልሰማም
ቢላት ነገ ሰላም አትሰጠውም ። ዛሬ ካልተወያዩትና መፍትሔ
ካላገኙለት ፣ ወዳጅነታቸው ብሽሽቅና ጭቅጭቅ የተመላበት መሆኑ
አይቀርም ። እና ፣ ''ለምን እንደምታለቅሺ ትናንት ጫፍ ጫፉን
ነግረሽኝ ነበር ። በይ ዛሬ ንገሪኝና ልስማው ። ያንዱ ሰው ለሌ
ላው የልብ ሥቃይ ነው ። እኔ አንችን ሳገባሽ ከኀዘኔና ከብቸ
ኝነቴ የምትገላግይኝ ፣ እስከ የሌለው ደስታ የምታጐናጽፊኝ
መስሎኝ ነበር ። ግን አልሆነም ። ብዙም የደስታ ቀናት
ከማሳለፋችን በፊት መቁዋሰል ጀመርን ። የኔን ብቸኝነት ባል
ነግርሽ ኖሮ ፣ ስለ ትዳርሽ ቀዝቃዛነት አትነግሪኝም ነበር ብዬ አስ
ባለሁ ። ወይም አንች ትሆኛለሽ አስቀድመሽ ስለ ራስሽ ልት
ነግሪኝ የጀመርሽ ። ያም ሆነ ይህ እንባን በእንባ መለዋወጥ የጀመ
ርን ይመስለኛል ። ውስጤን ከፍቼ ልቤን ስላሳየሁሽ ልብሽን ገል
ጠሽ ልታሳይኝ ተገፋፋሽ ። ዱሮ ለማንም ልትነግሪው አስበሽ
የማታውቂውን ዛሬ ለማውጣት ተገደድሽ አይደለም ?'' አላት ።

''መንገርም ! አለመንገርም የሚያስፈልገው አይመስለኝም ።
የምነግርህ ምሥጢር አይደለም ። ላንተም ነገርኩህ ለሌላ ሰው
ልዩነት አያመጣም ። እንዲያው ቅርብ ለቅርብ ስለሆንን ነው ፣ ልነ
ግርህ የፈለግሁ ። እውነቱን ለመናገር ፣ ከአንተ ጋር እስከንገናኝ

ድረስ መጥፎ ነገር የደረሰብኝና ያልደረሰብኝ መሆኑን አልተ
ገነዘብኩም ነበር ። ዝም ብዬ ነበር የምኖር'' አለች ኤልሣ ፣
ምሬትዋን ያለቅጥ ያጋነነባት ስለ መሰላትና ራሱዋን መከላከል
የማትችል አስመስሎ ስላቀረባት ።

''እኔስ ሌላ ምን አልኩሽ ? ሰዎች ሲባሉ ሁሌም ይኸው
ናቸው ። ጉራ ለሚነዛባቸው የባሰ ጉረኛ ሆነው ያታይሉ ። ልቡን
ለሚከፍትላቸው የበለጠ ቅን ይሆናሉ ። የልባችንን መወያየት
ጀመርን ማለቴ ነው እንጂ ፣ ከኔ በቀር የሚሰማሽ ሰው የለም
ብዬ አልተናገርኩም ። በይ እሺ የጀመርሽውን ጨርሺልኝ ።
የባልሽ እጎት ወይም አዩትሽ ምን ሠራችሽ ?''

''አስደበደበችኝ ። ከወንድ ጋር አየሁዋት ብላ አሳብቃ
አስደበደበችኝ ። ውሸትዋንኮ ነው ! በፍጹም ከወንድ ጋር አላ
የችኝም ። እሱ ግን የነገረችውን አምኖ ተቀበለ ። ማታ በሩ
ተዘግቶ ፣ መስኮት ተዘጋግቶ ፣ ራት በልተን ! ያኔ በጊዜ ቤቱ
እየገባ ራት አብረን እንበላ ነበር ! ልንተኛ ስንል ፣ 'በይ እሜቴ
ልብስሽን አውልቂ !' አለኝ ።''

'' 'እኮ ምን አስቸኮለህ ?' አልኩት ።''

'' 'አውልቂ ነው የምልሽ' ብሎ የደበቀውን አለንጋ አያ
ወጣው መሰለህ ? እኔ ደግሞ ሲቀልድ መሰለኝ ። ጨክኖ ይገ
ርፈኛል ብዬ በፍጹም አላሰብኩም ። ከዚያ በፊት ክንዴ ወይም ደረቴ
ሲጋለጥ በጣም ይሳሳልኝ ነበር ። ወይም የሳሳልኝ መስሎ ይታይ
ነበር ። የዚያን ለት ማታ ግን ፣ ልብሴን እስካወልቅ አላደርስ ብሎት
ቀሚሴን ከላዬ ላይ ቀደደና በአለንጋ ተያያዘኝ ። እኔም ሲመጣ
ብኝ እልኸኛ ነኝ አይደል ፣ ጥርሴን ነክሼ ቻልኩት ። ታለቅ
ሳለች ወይም ትጮሃለች ብሎ ጠብቆ ኖሯል ። አለ መጮሄን
ሲረዳ ይበልጥ ተናደደ...''

ገብሩ ፣ እቁዋረጣትና ቦዩን ጠርቶ መጠጥ እንዲያመጣላ
ቸው አዘዘው ። ቦዩም አዘጋጅቶ ይጠብቅ እንደ ነበር ሁሉ ፣ በቅ
ጽበት ይዞላቸው ከተፍ አለ ።

''በይ እሺ ፣ ቀጥይ'' አለ ገብሩ ከቀረበለት ብርጭቆ ጅን
አንድ ጉንጭ ስቦ ሲያበቃ ።

"ከዚያ በሁዋላ እንዳልተርፍ አድርጉ ገረፈኝ ። ራሱን እንኳ መልሶ ሳይዘገንነው የቀረ አይመስለኝም ። ብቻ ላብ በግንባሩ አስኪንቆረቆር ድረስ ገረፈኝ ። ሲደክመው ተወኝና አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ ይሰድበኝ ጀመር ።እሱ ላይ የመጣለትን መጥፎ ስድብ ሁሉ አወረደብኝ ። ከመገረፌ ይልቅ መሰደቤ እንገበገበኝና አለቀስኩ ። ከመሰደቤም ይልቅ በደለኛ እለመሆኔ እንገበገበኝ ። ታዲያ ያኔ ፣ 'የገረፈኝ ስለ ወደደኝ ነው' ብዬ ነበር የማስብ ።"

ኤልማ ፣ በረጅሙ ተነፈሰችና ዝም አለች ። ገብሩ የደነግጥ መስለው ። ፊቱዋን ቅጭም አድርጋ ሲያያት ሆዱ ተቆረጠ በረ ። ኤልማ የምታምር ከሚቁዋ ጋር ነው ። ከረጅሙ ቢጫ ቀሚሱዋ ጋር ነው ብሎ አሰበ ። ከዚያም የተቁዋጠረውን ፊቱዋን ድንገት ብትፈታው ብሎ ፣ "አሁን ይሽ ገላ መገረፍ ይገባዋል ? እሱን ነበር መልሶ መግረፍ ። እንችስ ብትሆኝ እንደዚያ ከገረፈሽ በሁዋላ አብረሽው መኖርሽ ምን ይባላል ?"

"ታዲያ ምን ማድረግ እችል ኖሯል ?"

"ይቅርታ እንዲጠይቅሽ ማድረግ ነበረብሽ ፤ ቢያንስ እንኳ"

"እንዲያውም ከነጭራሹ ተወኝ ። እስከ እኩለ ሌሊት እያመመኝ መምጣት የጀመረው ከዚያ በሁዋላ ነው ። ይልቅ ልጨርስልህ ፣ ስማኝ ። ከገረፈኝ በሁዋላ አልተኛም ብዬ ቁጭ አልኩ ። እሱ ግን ተኛ ። ጠፍታ ትሔዳለች ፣ ወይም በንዴት ራሱዋን ትገድላለች ብሎ እንኩዋ ሳያስብ ተኛ ። እንቅልፍ ሲወስደው ጊዜዬን ሰውነቴ በንዴት ተቃጠለ !"

"አረመኔ ነው ። ከገረፈሽ በሁዋላ እንዴት እንቅልፍ ሊወስደው ቻለ ባክሽ! ይህንስ መግደል ነበር" አለ ገብሩ ከንፈሩን በቁጭት እየነከሰ ። የባሉዋን አረመኔነት የተገነዘበላትና ከሱዋጉን የቆመ ገብሩ ብቻ ነው ። ዘመዶቹዋ ሁሉ፡ 'ደግ አደረገ ። ጥፋተኛዋ እንች ነሽ ። ድሮስ ያገባሽ ላይገርፍሽ ኖሯል?' ብለው ነው የፈረዱባት ።

"እሱንስ መግደል ነበር" አለ ገብሩ በድጋሚ ።

"መግደል ኢታተኝ መስለህ ብገድለው ልጆቼን ያለ እባት ማስቀረት ነው ። እኔም ላይ እስራት ወይም የሞት ፍርድ ቢፈረ ድብኝ ሁለታችንንም አጡ ማለት ነው..."

"ልክ አይደለሽም ኤልማ ። ለዚያ አረመኔ ባልሽ ትዕግሥት ሊኖርሽ አይገባም ነበር ። በዚያች ሰዓት እንች የነበረብሽ መናደድ ነው ። የተናደደ ሰው ደግሞ ስለ እስራት ፣ ወይም ስለ ሞት ፍርድ ማሰብ የለበትም ። የሞራል ጥያቄም ማንሣት አይኖርበትም ። ባልሠራሽው ጥፋት ተገርፈሽ መቅረት አልነበረብሽም ። ሰው ያለ ጋጢአቱ !!..."

"እኔም የተሰማኝን አድርጌአለሁ" አለች ኤልማ ከብ ሬቱዋን እየቁዋጠረችና እየፈታች ። "እንቅልፍ እንደ ወሰደው ሰውቅ ራሴን ለመግደል ሙከራ አደረግሁ ። የቁዋጠርኩት ገመድ ሲበጠስና ሲወድቅ መታጠቢያ ቤት የተደረደረውን ዕቃ አተራመስኩት ። የዚህን ጊዜ ከእንቅልፉ ነቅቶ ኖሮ ፣ እየደገፈ ወደ መኝታ ቤት ሲወስደኝ ትንሽ ትንሽ ትዝ ይለኛል ። ስወድቅ ወለሉ ራሴን ስለ መታኝ ሕሊናዬን ስቼ ነበር..."

ገብሩ አንዴ ከንፈሩን ይነክሳል ። አንዴ ጠረጴዛውን ይቆረቁራል ። ወርቅ የመሰለውን ዶረታንና ገጽታዋን ሲያይ ይበልጥ ወደዳት ። እየወደዳትም አዘነላት ። ውስጡንም ቅናት ስለ ያዘው የቀረበለትን ጅን አንሥቶ ግልብጥ አደረገው ። ከዚያ በሁዋላ ቀስ እያለ መጠጣት አልሆነለትም ። ኤልማንም ከዐቅሙዋ በላይ እንድትጠጣ ይገፋፋት ጀመር ። ሁለተኛውን ቢራ ጭማሽ እንዳደረገች ነው ቢራውን ትታ በግድ አረቄ እንድትጠጣ ያስገደዳት ። ከዚያ በሁዋላ ብስጭታቸውን ለማስወገድ ወይም ለመርሳት የፈለጉ ይመስል ፣ መፎነታተልና መሣሣቅ ጀመሩ ። ግን ሣቃቸው የውሽት ና ከእንገት በላይ መሆኑን ሁለቱም ስለ ተገነዘቡ ፣ ወዲያው ተዉ ትና ከመጠጡ ይዶጋገሙ ጀመር ። ገብሩ ላብ ጭልጥ ሲያደርግ ቆየና አዲስ ሐሳብ ከሰማይ እንደ ወረደለት ሁሉ ፣ እሺንር ሲያይ ከነበረበት ሩቅ ሰማይ ዐይኖቹን ወደ ኤልማ መልሶ እንዲህ አለ ።

"ከዛሬ ጀምሮ ከኔ ጋር ትኖሪያለሽ ። የሱን ያህል የማበሳጭሽ እይመስለኝም ። የሚወለዱትን ልጆች እና ሌቱዋን ወይም ሚስ

ቱን ላለመጉዳት ስል ነው አላገባም የምል ። ገሃነም ውስጥ ከሆንሽ የኔው ሳይሻልሽ አይቀርም'' አላት ገብሩ በደነደነ ልብ። ሞቅታና ፍቅር ሰላሙን እንዴ መረዙት ገባት ።

''ዛሬውኑ?''

''ታዲያ ምን ትጠብቂያለሽ? አትወጅውም አይደል?''

''መውደድስ አልወደውም ። ግን ልጆቹስ?''

''እናሳድጋቸዋለና ! ምን ይሆናሉ ብለሽ ነው? በጣም ነው ያሳዘንሽኝ ። በጣም ነው የወደድኩሽ ። ባልሽንም በጣም ነው የጠላሁት ። ሁለት ልጆች ማሳደግ የሚያቅተኝ ይመስልሻል?,

''ታዲያ ዛሬውኑ መሆን አለበት እንዴ? ትንሽ የቸኮልን አይመስልህም? የሰካር ወይም የቸኮላ እንዳይመስል መጠንቀቅ ይኖርብናል ። እንተም እስብበት ። ለኔም የማሰቢያ ቀን ስጠኝ'' አለች ኤልማ ፣ የገብሩን ሁለት እጆች ጭብጥ አድርጋ ይዛ ። ''ምናልባት ሞቅ ብሎኝ ይሆናል ። ወድጄሽም ይሆናል ። ወይም እዝኔልሽ ይሆናል ። ወይም ከከባችን ገጥሞና አዲስ ኑር አጭቶልን ይሆናል ። ብቻ ባንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ ። እንችም እንዴኔ ጠልተሽው ከሆነ ፣ ካለሽበት ገሃነም ላወጣሽ ዝግጁ ነኝ። ከመንኩሽ አመኝኝ ። ከሱ ምን ትፈልጊያለሽ? የቤት ዕቃውን እንዳለ ተይለት ። የኔ ደሞዝ ለሁለታችን ይበቃል ። ውርደት ሽን ተበቀይው ። እሱ ባለንጋ እንደገረፈሽ ሁሉ እንችም በጸጸት ሕሊናውን ግረፈው ።''

''ስማኂያችንን ሳንቀድ መፋታት አንችልም ። የኔና እንተ መጋባትማ ጨርሶ አይታሰብም ። በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል ተብለን እንከሰሳለን ። ይሽ መቸ ይቸግራል ብለህ ነው? ዋናው ፍቅር ነው ፤ መተሳሰብ ነው — ረጋ ማለት ፤ ማሰብ፣እኔም የተሳሳትኩ በመቸኮሌ ነው ። ሽማግሌ በመሆኑ ፣ ብዙ ነገር ያየ በመሆኑ ረጋ ያለ ኑሮ እንድኖር የሚያደርገኝ መስሎኝ ነበር ። ከዕድሌም እንደው አላውቅም ።''

ገብሩ አቁዋረጣትና ፣ ''የሰከርኩ እንዳይመስልሽ ኤልማ ። የቸኮል ኩምእንዳይመስልሽ ። ስለ ወደድኩሽ ነው — ስለ ፈለግሁሽ።

አንችም እንደምትፈልጊኝ ዐውቃለሁ ። ባትወጅኝም እንኳ አስፈልግሻለሁ ። ፈቃድሽን ስጭኝ እንጂ ውደጅኝ አልልሽም ። ለሚተዛዘኑ ሰዎች መዋደድ ምን ያደርገላቸዋል? ቢያንስ እንደ ምታዝኝልኝ ዐውቃለሁ ።''

''ይልቅስ ከወደድከኝ፣ ካለሁበት ገሃነም አወጣሻለሁ ካልከኝ ፣ ነገ ከነገ ወዲያ በጥሞና እንነጋገርበት ። አሁን ግን አላም ግባት አልፈልግም ብለህ ነግረሽኝ ፣ ልከፍትኝ ነኝ ብለህ ነግረሽኝ ስታበቃ ፣ አሁን ላግባሽ ብትለኝ አይገባኝም። ምናልባትም.. ብቻ ነገ...''

''በይ ጠጪ ። ቦይ? ግነህ...?'' ብሎ ገብሩ አጨበጨበ ። ቦዩ ልጅ እግር ነው ። እንኳን ጠርተውት ሳይጠሩትም ከተፍ ይላል ። ገና ሳይጨርሱ በሴላ ብርጭቆ እያመጣ በላይ በላዩ ይቱ ጸላቸዋል ።

''እነግርሃለሁ ስል ረስቸው'' አለች ኤልማ ያመልጣት ይመስል የገብሩን እጅ እየጐተተች ፣ ''ወዲያው እንዴ ተገናኝን ነበር እነግርሃለሁ ብዬ ያሰብኩ ። በል ስማኝ ሳልረሳው ልንግርህ ። ሕልሜን ከሰማኸው በሁዋላ ፣ የፈለግሽውን ስም ልትሰጠው ትችላለህ ።''

''ንገሪኝ እሰማሻለሁ ። ግለሙ ወይም መታገሥቱ ነው እንጂ የሚያስደነግጥ ስም መስጠቱ አይደለም ።''

''እንዲህ እንዴ ዛሬው አብረን የወጣን ይመስለኛል ። ሆቴሉም ይህ ያለንበት ይመስለኛል ። ዛፍ ያለበት ግቢ ስለም ወድ ፣ ሕልም ባየሁ ቁጥር ዛፍም አያለሁ ።እና የነበርንበት ግቢ በጣም ሰፊና ጫካ የበዛበት ነበር ። የሚያምር መስክ አለው ። መስኩን አቁዋርጦ የሚፈስ ወንዝም አለው ። መስኩ ላይ ብዙ የመሰናክል ዕንጨቶች ተተክለውበታል ።

''ከሦቱ ወጥተን ልንሔድ በር ላይ ስንደርስ ኃይለኛ ዝናብ መጣል ይጀምራል ። ታክሲ ብንፈልግ ብንፈልግ እናጣለን ። ወደ ዘበኛው ቤት ገብተን እንጠለላለን ። 'መቆየታችን ካልቀረስ መጥጥ ልዘዝና ልምጣ' ከማለትህ ከዘበኛ ቤቱ ጉዋሮ ሁለት

ፈረሰኞች እየጋለቡ ያልፉ ። ትንሽ አልፍ እንዳሉ አንዷ ፈረሰኛ አደናቅፎት ከነፈረሱ ይወድቃል ። ፈረሰኛው እንደ ወደቀ ይቀራል ። ፈረሱ ግን እየጋለበ ወደኛ ይመጣል ። ሁለት እጆቼን ዘርግቼ እያባበልኩ አስጠጋውና ልጓሙን ይዤ እየላ ብኩ አምጥቼ አሰጥሃለሁ ። 'ቦዩን እጠራውና ዝናቡ እስኪያባራ ድረስ እንጠጣለን' ትልና ወደ ሆቴሉ ትጋልባለህ ። ወንዙን ተሻ ግረህ ፣ መስኩን አቁዋርጠህ እያነስክ ፣ እያነስክ ሔደህ ካይኔ እስኪ ትሰወር ቆሜ አይህና ፣ 'እንዴት የሚያቃጥል ፀሐይ ነው' ብዬ ሹራቤን እከናነባለሁ ።

"ወዲያው ቦዩና እንተ ተከታትላችሁ ትመጣላችሁ ። ቦዩ በዝርግ ሰሐን ሁለት ብርጭቆዎችና አንድ ጠርሙስ ውስኪ ይዙ ዋል ። ሳያችሁ ከተቀመጥኩበት ነጥሬ እነሣና ፣ 'ውስኪው እንዴት ሳይፈስ ቀረ?' ብዬ ስጠይቅህ ፣ 'በዝርጉ ሰሐን ራሱ ላይ ስላስቀመ ጠው ነው' ብለህ ትመልስልኛለህ ። ቦዩ ከነፈረሱ ዘበኛ ቤት ገብቶ ከግርጌ ወዴ ራስጌ ፣ ከራስጌ ወዴ ግርጌ መላልሶ እየጋለበ፣ 'እኔን ለመጥራት ስትፈልጉ ፣ መስኩቱ ሥር ያለውን ደወል መጫን ነው ። እየጋለብኩ ከተፍ አላለሁ' አለና ከነፈረሱ በመስኩት በኩል ዘሎ ወጣና እየጋለበ ተመልሶ ሔዴ ።"

ገብሩ እግሮቹን አነባብሮ ፣ የግራ እጁን ክርን ጠረጴዛው ላይ ፣ አገጩን ደግሞ መዳፉ ላይ አስደግፎ ሕልሙን ስትነግ ረው እየተገረመ አዳመጣት ።

"ከዚያ በኋላ ዝናቡ እየባሰበት ይሔዳል ። ውሽንፍር የቀ ላቀለው ዝናብ መጣል ሲጀምር አካባቢው ይታፈናል ። ከቤት ውጭ አንድ ስንዝር ርቀት ለማየት አይቻልም ነበር ። በድንገት ቦዩ ሲመጣ እየዋለሁ — እየጋለበ ። ሌላ ነገር ምንም ማየት አይቻልም ። እሱን ግን ከሩቅ አየሁት ።

" 'ምን ሆንክና ተመልሰህ መጣህ?' ብዬ እጠይቀዋለሁ። ገና ከሩቅ ሳየው ለደግ ነገር እንዳልሆነ ዐውቂአለሁ ።"

" 'ልጆችሽ እናታችን የት ጠፉች?' እያሉ አባታቸውን በለ ቅሶ ግራ ሲያጋቡት ከቆዩ በሁዋላ ፣ ከፎቅ ላይ እየተወረወሩ ወደቁ ! «ሞቱ !» ብለሽ እንደማትጠይቂኝ እርግጠኛ ነኝ ። የፎቁን

ርዝመት ራስሽም ታውቂዋለሽ ። ባለቤትሽም በድንጋጤ አፉን እንዲያዘ ቀረ' ይለኛና ተመልሶ ይሔዳል ። ለጥያቄ እንኳ ዕድል አልሰጠኝም ነበር ። እየወደቅሁ እየተነሣሁ በዚያ ውሽንፍር ወደ ቤቴ ስሔድ ከእንቅልፌ ነቃሁ ። በል እስኪ ፍታልኝ ።"

"ምን መፍታት ያስፈልጋል? የቀን ምኞትሽና ሥጋትሽ ነው ፣ በሴት ሲያባክንሽ ያደረ ። የሕሊና ወቀሳ ነው ። ለባልሽ ታማኝ መሆን ትፈልጊያለሽ ። አለመታመንም ትፈልጊያለሽ ። እንዲህ ባያርግ እንዲህ ይሆናል እያልሽ የምታስቢው ሐሳብ ወደ ሕልም ተተርጉሞ ቀረበልሽ ። በቃ ይኸው ነው ። ልትጨነቂለት የሚገባ ሕልም አይደለም ።"

የገብሩ መልስ ኤልሣን አላስደሰታትም ። የልጆቹዋን ከፎት እየተወረወሩ መሞት ፣ የባሉዋ አፉን ይዞ መቅረት ፣ የሱዋ እቤ ቱዋ አለመድረስ አንድ መዘዝ እንዳለው ገምታለች ። በሕልም ስለምታምንና ሕልም ስለምትፈራ ፣ ትርጉሙ እስኪነገራት ድረስ ትጨነቃለች ።

"ምነው ፈዘዝሽ? ጠጭ ። ሕልምሽን እርሺው ፤ ልዘን ካሉ ምን የማያሳዝን ነገር አለ? ልጨነቅ ካሉ ምን የማያስጨንቅ ነገር አለ? መርሳት ነው የሚሻል ። ለመሆኑ ባልሽ እሔድ እሔድ እንኳ ምሳውን እቤት አይበላም እንዴ?"

"ሁለተኛዋ ሚስቱ ቤት ይበላ ይሆናል" አለች ፣ የታች ከንፈሩዋን በመከፋት ስሜት ጠመም አድርጋ ።

"ሌላ ሚስት አለችው እንዴ?"

"ያውም የኻያ አምስት ዓመት ሚስቱ ናታ! ግን መኻን ናት ። የተፋቱትም ልጅ ስላልወለዱ ነው ። ልጆች እስከትወልድ ለት ድረስ ጥሩ ባል መስሎ መታየቱ ፣ እያደር ግን እውነተኛ ጠባዩን ማሳየቱ ለዚህ ነው ። ዘር ሳይተካ እንዳይሞት ነው እኔን በስተርጅና ያገባኝ ። ሁሉም ነገር የተገለጠልኝ በቅርብ ነው ። ብቻ..."

"እይ በቃሽ" አለ ገብሩ እንዴ መቆጣት እያለ ። የምትፈራውን ሕልም እንድትረሳው ለማድረግ ሲፈልግ እንደነና ሌላ

ብሽቀት ውስጥ መግባቱዋ ነው ያስቆጣው ። ገብሩ እንደ ሌሉቼ ሰዎች ሁሉ ፣ ሥቀው ተሣሥቀውና ተዝናንተው እንዲለያዩ ሲፈልግ ኤልሣ ግን ተመልሳ እዚያው ናት ። አንዱን ሲያስተዋት ሌላውን እያነሣችና እንደ ቀበጥ ልጅ እየተነጫነጨች አስቸገረችው ። ለጊዜዉ እንኳ ፍጹም ደስተኛ መስላ እንድትታይ ለማድረግ መፍትሔ መስሎ የታየው መጠጥ ነው ። ደጋግማ እንድትጠጣና ሞቅ እንዲላት ደጋግሞ ይወተውታት ጀመር ።

"ጠጭ ኤልሣዩ!"

"ዝናቡ ሳይመጣ ቤቴ አድርሰኝ ፤ ሰማዩ ያለቅጥ ከብዷል" አለች ፣ እየተግበሰበሰ የሚያልፈውን ደመና በመስኮት እያየች ።

"ምነው ምን አስቸኮለሽ?"

"ደስም አላለኝ ። ደመናው ፣ ዝናቡ ፣ ልጆቼ ፣ ይኸ መጠጥ የሚያቀርብልን ቦይ ጭምር መንፈሴን ረበሹት ። ትናንት ያየሁትን ሕልም ዛሬ የምኖረው ነው የመሰለኝ ። በተለይም ቦዩ መጠጥ ይዞልን ወደኛ በመጣ ቁጥር 'ልጆችሽ ወደቁ!' ሊለኝ ነው እያልኩ ድንግጥ እላለሁ ። እባክህ ቶሎ አድርሰኝ" ብላ የመማፀን ያህል ነገረችው ።

"ኧረ ይህን ያህልም መለመን የለብሽም ። ያዝናናሁሽ መስሎኝ ነው እንጂ እንድንዘገይ የፈለግሁ — አንችን ደስ ካላለሽማ አደርስሻለሁ" አለ ገብሩ ኪሱን እየደባበሰ ። ሒሳቡን እስኪከፍል አልጠበቀችውም ፤ ኤልሣ ቦርሳዋን አንሥታ ወደ መኪናዉ ሔደች ። እየተንገዳገደች ስትወጣ ባያያት ኖሮ ፣ ከአነጋገሩዋ ብቻ መስከሩዋን ሊያውቅ አይችልም ነበር ፣ ገብሩ ። እሱም ሞቅ ብሎታል ። ተቀምጠው ሳለ ሁለቱም ደነና የሆኑ መስሏቸው ነበር ። ስካሩ ምላሳቸውን ሳይሆን ፣ እግራቸውን ተብትቦ ይዟቸዋል ። አልቅስ አልቅስ ፣ ሣቅ ሣቅ የሚያሰኝ ስካር — ስሜት የሚለዋውጥ ስካር ።

ገብሩ ፣ መኪናውን አስነሥቶ ሲጓዙ ፣ ኤልሣ ደመናውን ነበር የምታይ ። ደመናው በጣም ከብዶና ጠቁሮ ስታየው ፣ ኃይለኛ ዶፍ የሚጥል መንገድ ላይ የሚይዛቸው መስሏት ፈራች ። ቤቱዋ

አስክትደርስ ድረስ እንዳይዘንብ በሆዱዋ ትጸልይ ጀመር ። መኪናው ውስጥ መቀመጡዋን ረሳችው ። ለሱዋ የሚታያት በሕልሙዋ እንዳየችው ሁሉ ፣ ዝናቡ እየጣለ በእግሩዋ ወደ ቤቱዋ ስትሔድ ነው ። ገብሩ እየተገላመጠ ያያታል ። መስኮቱ ላይ ተለጥፋ ወደ ውጭ ብታይም ፣ የፊቱዋን መከፋትና የውስጡዋን መረበሽ ከፊል ገጽታዋ ብቻ ነግሮታል ። ሊያወራትም ሆነ ሊያጽናናት አልሞከረም ። ዝም አላት ። ሲመክራትና ሲያጽናናት የሚብስባት መሰለው ።

እስጢፋኖስን ዐልፈው ወደ ቦሌ የሚወስደውን መንገድ እንደያዙ ፣ አንድ ኦፔል መኪና ሲከተለው አየ ። ሊቀድመው ይልና ከፊቱ መኪና ሲመጣበት ቆም ብሎ ከኋላ ከኋላ ይከተለዋል ። ባርኔጣው ፊቱን ሸፍኖታል ።

"ይኸ ባለ ኦፔል ሊገጨን ነው እንዴ?"

ኤልሣ ዞር ብላ አየችውና ፣ "እሱ ነው!!" ብላ ጮኸች ።

"እሱ ማነው? ምን ያስጮህሻል? ቀስ ብለሽ አትነግሪኝም እንዴ?"

"እንዴት አይገባህም? እሱ ነዋ! ባለቤቴ ነው!! ምን ዐይነት መጥፎ አጋጣሚ ነው እባካችሁ! ወይ ዛሬ ቀን...በጉዴ ወጣሁ... ጉዴ!!"

"ምን ይሻላል? ቤትሽ ላድርስሽ ወይስ አዙሬ ወደ መጣሁበት ልመለስ?" ብሎ ጠየቃት ። የሚደርስባትን ስላወቀ ፣ መፍራቱዋን ስለ ተገነዘበ እንጂ ለራሱ ፈርቶ አይደለም ። የሱዋን ጭንቀት ማየት ነው ያልፈለገ ። የሱዋን ጭንቀት ማስወገድ ነው ፣ የታየው ።

ኤልሣ ፣ ጭንቀቷን ወዲያው ገታችው ። ትንሽ አሰበችና ፣ ትንፋሿን ዋጥ አድርጋ ። "የፈለገው ነገር ይምጣ እንጂ ወደ ሁዋላ አልመለስም ። ሸሽቼ የትም አልደርስ ። በር ላይ ታወርደኛለህ ። እኔን ማድረስ ከፈራህ አውርደኝና ተመለስ" ስትለው ገብሩ ደሙ

ፈላ! ከዚያ በውዋላ ምንም አላናገራትም ። ዝም ብሎ ይነዳ ጀመር ። ኦፒሉዋም ለመቅደም ሙከራ እያደረገች ተከተለችው ። 'ቤቱዋ በር ላይ እድርሻት የመጣው ይመጣል ። ግራ የሆነች ፍጥረት እኔንም ግራ አጋባችኝ' ብሎ አሰበ ።

በቤቱዋ በኩል እሚታጠፈው መንገድ ላይ ሲደርሱ ኤልማ ፣ ''እኔን እዚህ አውርደኝና አንተ ተመለስ'' አለችው ፣ እጆቿን እያርገበገበች ። ገብሩ ግን መልስ አልሰጣትም ። ባልዮው እንዳያ ቀድመውና መንገድ እንዳይዘጋበት በፍጥነት ይበራል ። ባልዮው ተናዶ ይሆናል ። መኻል መንገድ ላይ ውርደት ማስከተሉ አደ ቀር ይሆናል ። ለማንኛውም ግብግብ ቢፈጠርም ሠፈር ውስጥ ቢሆን ይሻላል ። በዚሁም ላይ ኤልማን አጋፍጧት መሸሽ አልፈ ለገም ። ምን እንደሚደርስባት ምን ይታወቃል?

መድረሱን ቀድሞ ደረሰ ። መኪናዋን ወዲ ግንቡ አስጠግቶ አቆመና ፈጥኖ ወረደ ። ድብድብ አይቀርም ብሎ ስለ ገመተም ኩቴን አወለቀና የሽሚዙን እጅጌ እየጠቀለለ እግሮቹን አንፈራጦ ቆመ ። ኤልማም ከመኪና ውስጥ ወጥታ ወደቤቷ ለመግባት መንገድ እንዳ ጀመረች ፣ ባልዋ መኪናቸውን አፈቱዋ ሲያቆሙና ብእጃቸው ሽጉጥ አንዱ ያዙ ስታይ ፣ ድንግጣ ወዲ ሁዋላ ተመለ ለችና ገብሩ ላይ ጥምጥም አለችበት ።

''ለመሆኑ አንተ ማነህ? ከሱዋ ጋር ምን ትሠራለህ?'' ብለው ጠየቁት ባልዮው በችኮላ ። አጠገቡ እስኪደርሱ መጠበቅ እልሆ ነላቸውም ። ገብሩ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ መስጠት አስፈላጊ መስሎ አልታየውም ። ማንነቱን እንደሚያውቁ ያውቃል ። ኤልማ አስተዋውቃቸዋለች ። ሌላው ቀርቶ የመኪናውን ታርጋ እንደ ሚያውቁ ርግጠኛ ነበር ። ባያውቁ ሊከታተሉት አይችሉም ነበር ። ኤልማ ብትቀመጥም ተከናንባ ነበር ። አስቀድሞ ባያውቁ ሊከ ታተሉት አይችሉ እንደነበር ገምቱዋል ።

''እንተንኳ ነው! ከባለቤቴ ጋር ምን ገዳይ አለህ?'' እያሉ ተጠጉት ። የልቡ ትርታ ሲጨምርም ፣ ገብሩ በፍርሃት አልተርበደ ብደም ። ኤልማ ከሁዋላው በኩል ተደበረች ። ከፍርሃቱዋ የተነሣ መገቡን በሁለት እጆችዋ እንታ ያዘችው ። እሱ ግን ጸጥ ብሎ

ቆመ ። መሣሪያ ከያዘ ሰው ጋር በባዶ እጁ ምንም መሥራት እን ደማይችል ያውቃል ። ነፍሱን ለማዳን ቢያንስ መሸሽ ይችል ነበር ። ግን ኤልማን አተደነነ ሽጉጥ ሬት ትቶዋት መርጥ አል ፈለገም ። መጨረሻውን ለማየት ዝም ብሎ ቆመ ።

ሐሳባቸው ሁሉ ኤልማ ላይ የተነጣጠረ ይመስል ፣ ''ኤልማ በለው ጀርባ ብትጠለይም አታመልጭኝም'' አሉና የሽጉጣቸውን አፈሙዝ ወደሱዋ አዙረው ሲጠጉ ፣ ''ከኔ በፊት እሱዋን እትነ ክትም'' ብሎ ድንጋይ አነሣና ኤልማን እየከለለ ወዲ ሁዋላው አፈገፈገ ።

ባልዮው ፣ ገብሩ የያዘውን ድንጋይ ከምንም ባለመቁጠር ወደነሱ ተጠጉ ። ገብሩ በያዘው ድንጋይ ግንባራቸውን መታቸው ። አመታቱ የጨበጣ ያህል ስለ ነበረና ድንጋዩም አነስተኛ ስለ ነበር ምቱ አልጣላቸውም ። ግን አንገዳገዶአቸዋል ። እየተንገዳገዱ ተኮሱ ። ጥይቱዋ የገብሩን ጆሮት ስንጥቃ ዐለፈች ። ኤልማን አላገኘቻትም ።

ግማሽ ጆሮቷ ሳያልፍ እካባቢው በጨኸትና በሰው ተሞላ....

"ወይ አዲስ አበባ ፡ ወይ አራዳ ሆይ!..."

ለወንድሜ ለእንዳለ ተረፈ

ከተለያየንበት ቀንና ሰዓት ጀምሮ ለጤናህ እንደምን ሰንብ
ተሃል? እኔ ደኅና ነኝ፤ አምላክን አይክፋው፤ ካንተ ከውድ ወን
ድሜ ናፍቆት በስተቀር። አባባ ደኅና ነው፡ መቸም እንደ ተቀየመ
ውቃለሁ፤ መቸስ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስምና። ልክ የኪዳን
ምሕረት ዕለት አይደል ከቤት የወጣሁ? ቀኑን ሙሉ ስሔድ
ውዬ ጀንበር ልትገባ ስትል ደጅን ከተማ ደረስኩ።

ማታውኑ የሞንት መኪና አገኘሁና አዲስ አበባ ሲያደርሰኝ
ተስማምተን ስድስት ሽልንግ ከፈልኩት። አብረውኝ የተሳፈሩት
ሰዎች በኋላ ሲነግሩኝ፡ ባለመኪናውን ያገኘልኝ ደላላ እንድ ሽል
ንግ አታሎኛል።

ኩንታሉን ፡ ቆዳውን ፡ ሰዉንም ስለሜነ መሬት ሆነው
ሲያዩት ሰማይ የነካ ይመስላል። በግድ እየተገፋሁ በመሰላል
እያማሳ መሔድ ሲጀምር በጣም ፈራሁ። ባባሁ። በመንገድ ላይ
የነበረው ሰዉም ፡ ውሻዉም ፡ ዶሮዉም እግሬ አውጭኝ እያለ
ባስብኝ።

ቁልቁለቱን መውረድ ሲጀምር ወደ ቀኜ ወደ ግራ ዘመም
ሲል ፡ ተሽቀንጥሬ ገደል የምገባ መስሎኝና አቁምልኝ ልውረድ
ብዬ ብጮህ ፡ ማን ይሰማኝ? ዐይኔ እያየ ገደል አልገባም ብዬ
ብሸፋፈን ነፋሱ ጋቢዬን ገፈፈኝ። አይ! እንግዲህ ባወጣ ያው
ጣው ብዬ ገመዱን በሁለት እጄ ጥርቅም አድርጌ አጥብቄ ያዝ
ኩት። የሾፈሩ አሽከር ክልቡ ሲስቅብኝ ጊዜ፡ የኔ ነፍስ ከማን
ይበልጣል ብዬ መደፋፈር ጀመርኩ።

እንዴ መንግሥተ ሰማያት መግቢያ በጠበበው በዚያ ገደል
መኻል ወርዶ ዓባይ ድልድይ ሲደርስ ልቤ ረጋ። ጸጉቴን መው
ጣት ሲጀምር፡ ከፊት ለፊታችን ያለው ቋጥኝ ላያችን ላይ የሚደ

ረመስ ይመስላል ። ተኋላ ደግሞ ዞር ብዬ ሳይ ከዚህ የወደቀ ሰው አጥንቱን እንኳ በወረንጦ ለመልቀም ያስቸግራል ። ኸ የፈራሁት ነገር ሳይደርስብኝ በሰላም ሜዳው አገር ደረስን ።

ቆላው ሙቀት ሲቆላኝ ነበር ፤ አሁን ደግሞ ብርዱ ያንገ ዝበኝ ጀመር ። እግሬንም እጀንም ቆፈን ያዘኝ ። ትራንታው እንዲያ እያንገራ ሲሔድ አደረና በነጋው አዲስ አበባ እናት ደረስን ። ትንሽ እንቅልፍ አሸልቦኝ ስለነበር ፥ አጠገቤ የነበረው ሰው "ተነሥ አዲስ አበባን እያት" አለኝ ። ቀና ብዬ ሳይ ዐይኔን ማመን አቃ ተኝ ። በመቶ ዐይነት ጎብረ ብርሃን አዲስ አበባ ትንቀለቀላለች ። ጥርት ባለው የቢጋ ሰማይ ጨረቃ ፍንትው ብላ ስታበራ የዚህን ግማሽ አይደምቅም ። እኒያ ሁሉ ከዋክብት እንደ ዕንቁ እያንጓ ባረቁ ሲያጅቧት ፥ የብር ሰፈድ መስላ የምታሳየን ነጭ ብርሃን አዲስ አበባን አይወዳዱራትም ። በቀይ ፥ በቢጫ ፥ ባረንጓዴ ፥ በሰማያዊ...መብራት መኻል ለመኻል ስትንቦገቦግ ዙሪያዋን ደግሞ እንደ ጎዘን ቀሚስ በጥቁር ጥለት ተከባለች ።

ትንሽ እንኳ አይቼ ሳልጠግብ ፥ ቁልቁለቱን እገባደደና ከተማውን እየሰነጠቀ ዐለፈ ። አሁን ደግሞ ባሕር ዛፍ ፥ ድንጋይ ቤት ፥ እርጌ ቆርቆሮ ቤት ብቅ ጥልቅ እያሉ እንዱ ወዲያ ፥ እንዱ ወዲኋላ በሩጫ ይሰወራሉ ። የሚታየው መብራትም ተቢታትኖ የቅድሙን ውበቱን እያጣ መጣ ።

ከመኪና ላይ ከወረድኩ በኋላ ፥ ወዴት እንደምሔድ ግራ ገብቶኝ ሳለ አንድ ግጥም ትዝ አለኝ ።

"ወይ አዲስ አበባ ፥ ወይ አራዳ ሆይ!

አገርም እንደ ሰው ይናፍቃል ወይ?"

ከዚያ አንዱን ሰውዬ ጠጋ አልኩና ፥ "አራዳ የት ነው?" ብዬ ጠየቅሁት ። ትኩር ብሎ አየኝና ሳቀብኝ ። ምን ያስቀዋል ብዬ ሲገርመኝ ደበሎዬን በእጁ እየዳበሰ ፥ "ምንድን ነው የለበስከ!" አለኝ ። ዝም አልኩትና ሔድኩ ።

እንዲት ሴትዮ ፥ ከፊት ለፊቴ መጣችና አፏን ይዛ እፊቴ ቆመች ። "አራዳ ጊዮርጊስ በየት በኩል ነው?" አልኳት ። "ለም

ንድነው ድብዳብ የምትለብስ?" ብላ ጠየቀችኝ ። በኋላ አንድ ሽማግሌ መንገዱን አሳዩኝና ሔድኩ ።

ቀኑን ሙሉ ዐይኔ ጉድ ሲያይ ዋለ ። የቤቱ አሠራር ፥ የፎቆቹ አረዛዘም ፥ የመኪናው ውበት ፥ የሰዉ ግማር ፥ በጣዋት ሙራ የሚናሰቀለቀው መኪናውና የፎቁ መስተዋት አዲስ አበባን የጷድቃንና የሰማዕታት ማረፊያ ከሆነችው ከመንግሥተ ሰማያት በላይ አስብኳት ። ይኸ ሁሉ ቤት በአንድ ቦታ የተከማቸ ለምንድ ነው? ብዬ ራሴን ይገር ተደነቅሁ ።

እኒያ ድምፃቸው ሳይሰማ እንዱ ውሃ የሚፈሱ ትናንሽ መኪናዎች ፥ በሰው እጅ ተሠሩ ለማለት አያስደፍርም ። የቤተ ክርስቲያኑ ማማር ፥ የተሳላሚው ሰው ዕርጋታ ፥ የነዳያኑ ብዛት ያስደንቃል ፤ ያስደምማል ።

ሰዉ እንዱ ገሀ ዘጊ በሚያማምሩ መንገዶች ላይ እንዱ ወዴ ላይ ሌላው ወዲታች ከመኪና ጋር እየተጋፋ ሲሔድ ፥ እኛ መንደር ጠዋት ጠዋት ከብቶች ፥ በጐች ፥ ፈረሶች ፥ እምቦሶች ፥ ከሚያስመሹት ቡረቃና ጩኸት የበለጠ ዱስ ይላል ።

የሰው ሞኝ ለጽድቅ ኢየሩሳሌም ይሔዳል ። እንኳን አራዳ ጊዮርጊስን ተሳለምኩ እንጂ ቢሻው ልኮነን ። ጠዋት ዳዊቴን ደገምኩና ቁጭ እንዳልኩ ፥ አንድ ሱፍ የለበሱ አዛውንት መጡና እንካ ብለው ተኪሳቸው አውጥተው ዘረጉልኝ ። "እኔ ምን ያደርግልኛል? ለነዳይ ይስጡት" አልኳቸው ። "የለማኝ ጥጋበኛ" ብለውኝ ሔዱ ። እኔ ተማሪ ነኝ እንጂ ምጽዋተኛ ነዳይ አይደለሁ! ኋላ እንደ መሰለኝ በጋቢዬ ላይ ደርቤ የለበስኩት ደበሎ ኑሯል የአዲስ አበባን ሰው ያስደነቀው ። ቀኑን ሙሉ እየዞርኩ እንደ ሞኝ አፈጌ ከፍቼ ምኑንም እያየሁ ስገረም ዋልኩና ደጀ ሰላም ለማደር ብሔድ ዘበኛው አባረረኝ ። ደሞ ቤተ ክርስቲያን ለተማሪ ከተከለከለ የት እደርሳለሁ ብዬ ፥ ሳልወድ በግድ የግዜር እንግዳ አሳድሩኝ ልበል ብዬ ብዞር ማን ያሳድረኝ ። "እረ ባካችሁ የሰው አገር ሰው ነኝ አሳድሩኝ! ስንት ስላለኝ ለሆዴ እታስቡ" ብል ሁሉም አድሞ እምቢ አለኝ ። አንዱ ሌባ ያርደኛል ብዬ ስፈራ የባሰ እኔ ተፈራሁ ።

"ኧረ ባካችሁ እግሬን አጠቡኝ፣ አልጋ ልቀቁልኝ አልልም ባዶ ወለል ላይ አተኛለሁ" እያልኩ ብለምን ወንዱም፣ ሴቲቱም፣ ሽርሙጣዉም፣ መነኩሲዉም አላስጠጋ አለኝ።

ወንድሜ ሆይ! ምንአልባት አውነት አይመስልህ ይሆናል። የግዜር እንግዳ አሳድሩኝ ሲል፣ ባይሆን መኝታ ባይለቀቅለት፣ እግሩን ባይታጠብ፣ የፈለገው አረመኔ እንኳ የበላውን አብልቶ የጠጣውን አጠጥቶ አሳድሮ መንገድ አሳይቶ አይሸኝም? ትለኝ ይሆናል። ተሳስተሃል። ወንድሜ ሆይ! ወዶ አዲስ አበባ ሰመጣ ልብህ ስለቆመ፣ የምጽፍልህን ሁሉ እንዶ መሸንገያ አትቁጠረው። ይልቅስ ትምህርት ይሁንህ።

ደጉ፣ ክርስቲያኑ ያዲስ አበባ ሕዝብ እንድ እንግዳ አላሳድር ማለቱ ዕውነት ነው። መንበረ ፓትሪያርክ አራዳ ጊዮርጊስ እንድ ደበሎ ለባሽ ተማሪ ከቤተ ክርስቲያን ማባረሩ ዕውነት ነው። ከቤቱ በረንዳ ላይ ለማደር ብጠይቀው፣ 'ሴሊት ለመቅፈርና ለመስርሰር እንዲመችህ ነው?' አለኝ። የቀኑ ቁፋሮና እርሻ ሰልችቶኝ አይደለም እንዴ አባቱ እየረገመኝ የኰበለልኩ?

መጨረሻ ላይ፣ አንድ ደግ ሰው አገኘሁና ሳልጠይቀው ለምና ሊያሳድረኝ ወሰደኝ። ስሔድ መንገድ ዳር ብዙ ሰዎች ተኙተዋል። "እነዚህ ሁሉ እንግዶች ናቸው?" ብዬ ብጠይቀው፣ "ካሥር ዓመት በላይ የሆናቸውም አሉ" አለኝ። ምን ዐይነት ሰነፎች ቢሆኑ ነው ይህን ያህል ዓመት አንድ ጐጆ እንኳ የማይቀልሱ? ገረመኝ።

ለስንቅ የያዝኳቸውን ሽልሎች ተካፍለን በልተን ተኛን። ሴሊት ጋቢየን ሰርቆ ጠፋ። ብቻ ደበሎዬን እንኳን ትቶልኝ ሔደ። ብዳብስ ዳዊቴን ካንገቱ ላይ ማንጠልጠያውን በምላጭ ቆርጠ ውስጡ ከነበረው ዐሥር ሽልንግ ጋር ወስዶ አጣሁት። ለካስ ይህ ሁሉ ቤት አለ ነገር አልበዛም። እንዱ እንዱን ስለማያስጠጋው፣ እንግዳውም ኗሪውም ቤተ ሠሪ ሆኖ ነው።

ለአዲስ አበባ ሕዝብ ዘር ይውጣለትና፣ እንኳን እኔን እላሪ ደኛ እንጂ ደበሎዬን ጨምሮ ይግፈፈኝ። ድሮስ ከተማ ከበለጸገ፣ ጭፈራ ካበዛ፣ እንኳን ለሰው ሊያዝን ፈጣሪውንም አይፈራ።

እንዴ ነነዌና እንዴ ባቢሎን የፈጣሪ ቁጣ ይወርድበታል። የሕንፃዎቹ አረዛዘም፣ የጽንጹው ብዛት ሲታይ ፈጣሪ ሥራውን ቀስ በቀስ እንዴ ጀመረ ያሳያል። እንግዲያውማ ስዉ የእንድ ወንዝ ውሃ እየጠማና አብሮ እየኖረ፣ ዘጠና ዘጠኝ ቋንቋ መናገር ምን አመጣው? የመኪናውንና የመንገዱን ብዛት፣ የሰዉን ብዛት ብታየው፣ ይሽ ሕዝብ እንዴ ጥበቡ አበዛህ እንድ አፍና አንድ ልብ ቢሆን፣ የፈጣሪውን ሥራ የሚያስንቅ አዲስ መሬትና አዲስ ሰማይ ይሠራ ነበር። ታዲያ ምን ይሆናል፣ የክፋታቸው ክፋት፣ "ነግዶ ኮንኩ ወኢተወከፍክሙኒ" ያለውን ትልቁን የወንጌል ቃል ረስተውታል። ታዲያ አፋቸውን ቢለያየው በፈጣሪ ይታዘናል?

ወንድሜ እያልኩ ስጠራህ የሩቅ ዘመድ ስለሚያስመስል እንዳሌ፣ አፋፉ ላይ ቆመን የምናየው ያ ስማዩን ደግፎ ያየዘው ተራራ ያገር ዳቢቻ አይደለም። ከዚያም ወዲያ ወዲያ ከዚያ ወዲያ። ካዲስ አበባም ወዲያ አገር አለ፣ ደሞ ይሔድ ወይስ እየተሻለ አላውቅም።

ውዬ ሳድር፣ በኔ በራሴ መፍረድ ጀመርኩ። መኰላ ያነገሰ ውንና ሙጀሴ ያጣመመውን እግሬን አይቼ፣ ያዲስ አበባን ቤቶች እግር (ነጠላ ጫማ አድርገው ሲሔዱ) ሳስተያየው የቆማጣ ያህል ያሳፍረኛል። የአጇ ጣት እንኳ ከእነሱ የግር ጣት ዐሥር ጊዜ ይቆረፍዳል። የዐይን፣ የከናፍራቸው፣ የጥርሳቸው ማማር፣ የጸጉራቸው መለስለስ፣ ፍንጃል የመሳሰለው ዐይናቸው፣ በረዶ የመሰለው ጥርሳቸው፣ የእግራቸው ቅርጽ፣ ጠቅላላ ውበታቸው ሲታይ እንደ መኪናዎቹና ቤቶቹ ሁሉ፣ በሰው እጅ በጥንቃቄ የተሠሩ እንጂ፣ እሰው ሆድ የበቀሉ አይመስሉም። ደሞ የሚገርምህ—የዓመት በዓል ሳይኖር ሁሉም የክት ልብሱን እየለበሰ መውጣቱ ነው። ፈጣሪ ግፍ ተናገርክ አይበለኝ እንጂ፣ የእመቢታችን ሥዕል እያሉ የሚልኩልን ያዲስ አበባ ሴቶችን ፎቶ ነው፣ እስክ ማለት ደረስኩ።

ብዙ ባለመማሬ ፈጣሪን አመሰገንኩት። ዳዊት ብማርና ብዛቱን ካገሬ የወጣሁ፣ ኮሌጅ ብጨርስማ ቅብጠቱ ሞትን ፍለጋ ይሰደኝ ነበር ማለት ነው። እንተም ብዙ ባለመማርህ

ፈጣሪን አመስግነው ። ድንቁርና ወይም አለመማር ጥሩ ነው የጉ ልህ አዲስ አበቦች የተጠየፉትን የገዛ ደበሎዱን እኔም መዋላት ስለ ጀመርኩ ነው ። አንተ ግን ድሪቶህን የሚነቅፍብህ ስለሌለ አውንም ትወደዋለህ ። በዚያ ሁሉ ከተሜ መኻል የኔ ለምድ ለቅሶ መኻል ገብቶ አታሞ መደለቅ ነው ። ያንን ሁሉ እቮህ ፣ መኩሳና ፣ ቆረን በባዶ እግሬ እሔድ የነበርኩ ሰው ፣ እንደ መስተዋት በሚለሰልሰው ያዲስ አበባ መንገድ ጫማ መጠንቲ ያስገር ምህ ይሆናል ። የበለጠ ይድነቅህ እንጂ ፣ እኔስ ቦሳሌ ሱሪና ኩትም ያምረኛል ። ኧረ ሴላም ሴላም ያምረኛል ። አንተ ግን ከቴምጣ ወዲያ ሱሪ ፣ ከሣር ጉጀ ሴላ ቤት ፣ ከኩራዝ ወዲያ መብራት ያለ አይመስልህም ። ምንም ምንም አያምርህም ፣ ስላላየኸው ። 'ያላዩት አገር አይናፍቅም' ተብሏል ።

አውንማ ምንም የሚሰረቅ ነገር ስለ ሌለኝ ፣ ያለ ሥጋት እንቅልፌን እለጥጣለሁ ። ብርዱ ነው መከራ የሆነብኝ ።

በቀደምለት ጠዋት ስንነሣ ፣ ብርድ በሽታ አሞት የነበረው ጓደኞችን ሞቶ ተገኘ ። በሉ እንከፍነውና ቤተ ክርስቲያን ወስ ደን እንቅበረው ብላቸው ፣ ግማሾች ዝም ብለው ሐዱ ፤ ሌሎች ደግሞ 'ለምን ገልጠህ አየኸው ፣ ልታሳፍሰን ነው ወይ?' ብለው መዓት አወረዱብኝ ። ዐይናቹ ፈጠው ፣ ጥርሱ ገጠ ፣ እጆቹ ተዝ ርግተው ፣ እግሮቹ ተኩርምተው ላየው ሰው ልብ ይበላል ። እኛ ካልቀበርነው ማን ሊቀብረው ነው? ማዘጋጃ ቤት ።

አውን ደግሞ የባሰ መባባትና መፍራት ጀመርኩ ። ሞት እን ዲህ ርካሽና ተራ ነገር ሆኖ መገኘቱ ፣ ሞት ሳይፈራ ሟቹ መፈ ራቱ ፣ መንፈሴን አሸበረው ። የምኖር ከሰው ጋር ሳይሆን ከጭ ራቅ ጋር መሰለኝ ። ሰው ይሆን ያህል የረከሰበት አገር!

ቀኑ መምሸት ሲጀምር ፣ የማዘጋጃ ቤት ሰዎች መጡና እግ ርና ራሱን እንጠልጥለው ፣ እንደ ግንድ መኪና ውስጥ ወረወሩት ፣ ይዘውት ሐዱ ። ትንሽ ቆይቶ ሴላ የቆሻሻ መኪና መጣና ፣ ተከ ምሮ የነበረውን ቆሻሻና ያን የውሻ ራሳ ጭኖ ሐዱና ማደሪ ያችንን ከማማት አጸዳልን ።

እንዳሴ ፣ የማታ የማታው ብርድ ሳል ስለ አስያዘኝ ፣ እኔም መመለሻ የሌለኝ መሆኑ ተስማኝ ። ፍርሃቴ እየበዛ ሐዱ ። ከሞት ቡን እየከበበ ከንፈሩን ሲመጥና ምራቁን ጢት ሲል እየታየኝ ነው ። ከሞትማ ማን የሚቀር አለ ?

ምን የመሳሰሉ ገበዞች ፣ ሴት ወንጥላ በግትሽከመው እን ስራ ውሃ ሲቀዱና ለሽርሙጦች ጌሾ ሲወቅጡ ይውላሉ ። እኔም ደበሎዬን አስቀምጬ ስሸከም እውላለሁ ። የሆንኩትን ሳልነግርህ ።

ጊዮርጊስ አጠገብ አንድ መንዲስ ሰውዬ በፈረስ እንዴ ሆን የሚያሳይ ምስል አየሁ ። ይኸኮ ቤተ ክርስቲያን ያቃጥል የነበረው ግራኝ መሐመድ ይሆን ይሆናል ። ገባሬ ታምራት ጊዮርጊስ ለመቀጣጫ ገትሮት ነው ብዬ አሰብኩ ። ከዚያም ለማረጋገጥ ብዬ ሣሩን ውሃ ያጠጣ የነበረውን ሰው ፣ "ወንድሚ ይሽ የግራኝ መሐመድ ምስል ለመቀጣጫ ከቆመ ስንት ጊዜ ሆኖታል ?" ብዬ እየቀለድኩ ጠየቅሁት ። "እንት ከርፋፋ ባላገር! እምዬ ምኒልክን ነው ግራኝ መሐመድ የምትላቸውን አውን ፖሊስ ልጥራ ?" አለና የጐማውን ውሃ ላዬ ላይ አፈሰሰው ።

'የምን ምኒልክ ነው? የየት አገር ታቦት ፣ ወይስ መናኛ ነው ? ገድሉን ያላነበብኩት ጻድቅ ይሆን?' ብዬ ፖሊስ ሳይጠራ ሩጫዬን ቀጠልኩ ።

አንድ ቀን ደሞ ፣ ፈረንጆቹን ከነልጆቻቸው እንዴ ቆሙ ጠጋ ብዬ እየኋቸው ። ቆዳቸው ከመንጣቱ በስተቀር ያው እንደኛው ሰው ናቸው ። ጠጉራቸው ደሞ እንዴ ፈረስ ጋማ ለስላሳና ለሽ ብሎ የተኛ ነው ። ኩትና ሱሪ ሳይሆን የሐር መጐናጸፊያ ቢለብሱ ፣ ኢየሱስን የሚመስሉ ብዙ ወንዶች ፈረንጆች አይቻ ለሁ ።

ይልቅ ልንገርህ ። ያዲስ አበባን ቂስ ብታይ በማቅ ትሞታ ለህ ። ሲቀድሱ የሚለብሱትን ቀሚስ ከመቅደስ ውጭም ለብ ሰውት ይሐዳሉ ። ቀሚሳቸው መሬት እየጠረገ በዚያ ላይ ጋቢ

ወይ ካባ ይደርባሉ ። ደሞ የሚጠመጥሙት ሻሽ አይደለም ፥ የንግ ልጥልጥ የመሰለ ጥቁር ቆብ ነው ። ምን እንዳሳሰበኝ መገመት ትችላለህ ? ጸሐፍት ፈሪሳውያን ።

አንድ ቀን ደግሞ ፥ አንድ ረጅም ሕገ ሥር እንደ! ቆምኩ ዘመም እያለ ወጥቶ ሊወድቅብኝ መሰለኝና ፥ 'ወግድ ሊወድቅ ነው!' እያልኩ ስሮጥ መኪና ሊድጠኝ ነበር ። ባለ መኪናው አንገቱን ብቅ አደረገና ከትልቅ ሰው አፍ የማይጠበቁ ጸያፍ ስድቦችን አወረደብኝ ። አልተናደድኩም ። ያገሩ ልማድ ስለ ሆነ ፥ ነጭ ጸጉር ያበቀለው ሁሉ የባሰ ስለሚሳደብ ለምጀዋለሁ ። ተመልሼ ስመለከት ሕገ፱ው ሥር የነበሩት ሰዎች ይስቁብኛል ። ጠጋ አልኩና ቀና ብዬ ብመለከት ፥ ለካስ ደመናው ኑሯል እየተጥመለመለ የሚሔድ ። አስብ ፥ ርዝመቱን በዚህ መገመት ትችላለህ ።

ማታ ክፉኛ ሲበርደኝ አመሸና ትንሽ እንቅልፍ ሲያሸልበኝ ፥ ያ ብርድ የገደለው ጓደኛዬ በሕልሜ ታየኝ ። እሳት ለብሰ ሊያቅፈኝ ደረሰ ። 'ለምንድነው ፍታት ያላስፈታሽኝ? ለምን ድን ነው በሰው ልጅ ወግ ያልከፈንከኝ? ለምንድነው የክርስቲያን ወጉ የሚነፈገኝ? ያን ያህል ጊዜ ከሞት ጋር ታግዬ ባሳር ብንለያይ ፈሳዬ ለፀሐይ ተስጥቶ የዋለ ለምንድነው? ዐሥር ጻዊት ማንን ገደለ ? ግድ የለም! ብድሩ ይድረስህ አልልህም ፥ አንተም የኔን መንገድ እየተከተልክ ነው' አለኝ ። ደንግጬ ተነሣሁ ።

እኔ ለራሴ ጻዊት መደገም የተውኩ ሌባ ከወሰደብኝ ወዲህ ነው ። ደሞ ሕልሜ አስደንጋጭ እየሆነ ሔዷል ። ቤተ ክርስቲያንም ቅኔ ማኅሌት መቁባት አልችልም ። ሻማ ልትሰርቅ ነው እያሉ ያባርሩኛል ። አይ! አገሬ መቅደሱን እንዳልተምነሸነሹበት ሁሉ ፥ ቆሜ ማስተዳስ ልክልክል ?

ቀኑ እየበዛ ሲሔድ ፥ የሚያጋጥመኝ ነገርም የዚያኑ ያክል መብዛት ጀምሯል ። አንድ ቀን በጣም ራበኝና ኩሊነት ባገኝ ብዬ ስዘዋወር ፥ አንዲት ሸርሙጣ ጠራችኝና ፥ ''አንድ እንስራ ውሃ ቅዳልኝ ። ብትፈልግ አንድ ጣሳ ጠላ ወይ ዐሥር ሳንቲም አሰጥሃለሁ'' አለችኝ ።

አልቅስ አልቅስ አለኝ ። በጣም ተናደድኩ ። ደሞ ከሸ ዘም ወርጄ ውሃ ልቅዳ? አልፍ ስል ፈረንጆች አየው ። የሚሉትን ለመስማት ስጠጋቸው ፎቶ አነሡኝ ። ሳቅኩባቸው ። አገውኛ አይሉት ጋልኛ ፥ ውጦንቅጡ የወጣ ነው ። መቼም ትልልቁ ሕገ፱ ውስጥ የሚኖሩ እንሱ መሆናቸው አይጠረጠርም ። የትም ይኑሩ ።

ርቦኝ ስለነበር ፥ ራጥኤልን ልግፀን ብዬ ቅጥሩን ዐልፌ ገባው ። ከዚያም ዶረጃው ላይ ተደፍቼ አቡነ ዘበሰማያትን ደግሚ ስነሣ ፥ የቁሶቹ ብዛትና የመልካቸው ቅላት ፥ የጥምጥማቸው መተ ለቅ አስገረመኝ ። ባስተውላቸው ለካስ ዐረቦች ናቸው ፥ ረጃጅም እጀጠባብ ለብሰው የሚጸልዩ ። አቤት አደነጋገጤ! ደሞ በገዛ እጄ ስለምኩ ብዬ አለቀስኩ ።

በል እንግዲህ ይብዳቤውን ወደ መጨረሱ ነኝ ። የባሱን የቆሙን ዘላበድኩልህ ። ምን ላድርግ ? ብርቅ የሆነብኝን ሁሉ ልጻፍልህ ብዬ ነው ። አዶራ ፥ እስላሞች ምኩራብ ሰገዱ ብለህ እንዳታወራ ። ዐውቆ ነው እንጂ ተሳስቶ ነው የሚለኝ የለም ፥ ድንገት ላገራ ቢያበቃኝ ።

የሸዋ ውሃ አይለቅም ይባላል ። እኔስ መሣፈሪያ ገንዘብ ባገኘሁና ውሃው ባገደኝ ። ሥራ ላለው ሰው ግን ከተማን የሚያስንቅ ነገር የለም ። ሥራና ገንዘብ የሌለው ግን ፥ ያን በየመንገዱ ሲበራ የሚያድረውን ኤሌክትሪክ እንኳ ቤቱ ውስጥ ማስገባት አይችልም ። የዚህ ዐይነት መዓት ሰዎች ዐውቃለሁ ።

አንድ ቀን ማታ ደግሞ ፥ አንድ ሰውዬ ሰክሮ ሲወላገድ ጓደኞቹ እንደብድብና ንብረቱን እንውሰድ አሉኝ ። የሞተስ እንደሆነ ? ይሙታ! ሰው የተፈጠረው ለመሞት ነው ። እኛ ባንገድለው ፈጣሪ ይገድለዋል አሉ ። አልቀረለትም ። ከኛ አልፍ እንዳለ እንደ በሬ እያስጎሩ ልብሱን ገፈውት ሸሹ ። ለካስ ሲታገላቸው ጊዜ በጨቤ ወግተውት ኑሮ ጠዋት ሙቶ ተገኘ ። ብንቀድም ኑሮ ለኔም ያገሬ መግቢያ አላጣም ነበር ።

ጠዋት እኛ ታፈስንና ፖሊስ ጣቢያ ተወሰድን ፥ እናንተ ነደላችሁት ተብለን ። ቢሆንም አስር ቤታቸውን ወደድኩት ።

እግዚአብሔር በፖሊስ አዛዥ ተመስሎ [ቤታችንን ሲያዘጋጅ ልን ደስ አለኝ ። የደብረ ሊባኖስን ዳቤ የመሰለ እንጀራ እየ ጐመድኩ አምስት ወር ተቀለብኩ ። ሰይጣን የሚያመሰልበት የለም አይደል ? የፍርድ ቤቱን ዳኛ ተመስለና ለመግደላቸው ማስረጃ ብለው ከሞቀ ቤታችን አስወጡን ።

ከስር ቤት ወጣሁና ድሮ ወደማድርበት ቦታዬ ሔድኩ ። ማታውኑ ያ ሙት ጓደኛዬ በሕልሜ እንዲህ አለኝ ፥ ''ለእንግዲሁ ስሞት ዝም [ብለህ እንዳታየኝ!''

''ለመሆኑ ዕድሜ ልክህን እየተመላለስክ ስትሞት ልትኖር ነው ወይስ ከዚህ በፊት መሞትህን ረሳኸው?'' አልኩት ። ምንም አልመለሰልኝም ። አሁን እንደሚመስለኝ በእኔ የዋልከውን በሌሎች ላይ እንዳትውል ማለቱ ነው ። ወይስ ከነአማርኛው ጠፍቶታል ልበል ? ገና ከሞተ መንፈቅ ሳይሞላው ቋንቋው ከጠፋውማ አማርኛ ምኑን የመላዕክት ቋንቋ ሆነ?

በል እንዳሌ ፥ አዲስ አበባ ባንድ ዓመት ያየሁትን ከሞላ ጐደል ጽፈልሃለሁ ። በተረፈ እንግዲህ በዐይነ ሥጋ ሰመ ተያየት ያብቃን ።

ይላል ወንድምህ
አውግቸው ተረፈ

ያለፈውን ይብዳቢ እንዳነበብከው በመተማመን ዛሬ ደግሞ ይህንን ጻፍኩልህ ።

አንድ ቀን ኩሊነት ፍለጋ ስንከራተት ቅድስት ማርያም ደረስኩ ። እዚያም የድሮ ጓደኛዬን አገኘሁት ። እንደኔ ዲያቆን ሆኖ ተያዥ አምጣ ተብሎ ከቅድስት ማርያም ደጇ ሰላም የተባለ የመቀሌ ልጅ ነው ። ከቀኑ ስምንት ሰዓት ገደማ ነበር ።

''ከነጋ ምንም እህል አልቀመስኩ?'' አለኝ ።

''እኔም ምንም አልቀመስክ ?'' አልኩት ።

አንድ ላይ ተቀምጠን የዓርብ ዳቦ ስንጠብቅ ፥ አንድ ዐይነ ሥውር ዱላውን እያወዛወዘ ወደኛ መጣ ። የቤተ ክርስቲያኑ ዘበኛ ወዴት እንደሚሔድ ከጠየቀው በኋላ ፥ ''ሒድና መንገድ ዳር ያለውን የወይዘሮ ዓለምነሽን ጠጅ ቤት አሳየው'' አለኝ በዱላ እየጐሸመኝ ።

''የትኛውን መንገድ ዳር ያለውን ጠጅ ቤት ነውየ'' ብዬ ጠየቅሁት ።

''ወዲ ማንፍሴ ወንዝ በሚወስደው መንገድ ዳር ነው'' ዐይነ ሥውሩ ትከሻዬን ይዞ እንደ መኩተል እጅ ለጅ ተያ ይዘን እንሒድ'' አለኝ ።

መንገድ ላይ አንድ ሰውዬ ዳቦ ሰጡት ። ''እንካ'' አለኝ ።

''ለምን አይበሉትም? ምን ዐይነት ደግነት ነው ፥ ተመጽውተው የሚመጸውቱ ?'' ብለው ፥

''ስለማልፈልገው ነው'' አለኝ ።

ጠጅ ቤቱ ስንደርስ ሥራዬን ጠየቀኝ ። ኩሊ መሆኔን ስነግረው ፥ ''እንግዲያውስ ከኩሊነት ልመና ይሻላልና እኔን ምራኝ'' ብሎ እጄን አጥብቆ ይዞ ይለምነኝ ጀመር ። እንዲያውም ጠጅ ካልጠጣህ ብሎ በግድ አስቀዳልኝ ።

ጠጁ ግራዋ ግራዋ ይላል ። ሊጠጣልኝ አልቻለም ። ዐይነ ሥውሩ ሰውዬ ግን ምስት ብርሌ ጠጣ ።

ከዚያ እንደማይለቀኝ ዐውቄ ፥ እስቲ ከኩሊነት ልመና መሻሉንም ልይ ብዬ ቤት ሚስት ያለውና የሌለው መሆኑን ለማረጋገጥ ፥

"ቤት አለዎት" ብዬ ጠየኩት ።

"አዎን ። ቆንጆ ሚስትም አለችኝ" አለኝ ።

"ለመሆኑ ስንት ብር ቢኖርዎት ነው ፡ ሦስት ጠጅ ባንድ ጊዜ የሚጠጡ?" አልኩት ።

"ስሙኒ ይሁን ሽልንግም ይሁን ፡ ባለኝ ገንዘብ ልክ እጠጣለሁ ።"

ከዚያ በኋላ ፡ ወደ አራት ኪሎ እንድወስደውና በየጠጅ ቤቶች እንዳስለምነው ጠየቀኝ ።

አራት ኪሎ አንድ ትልቅ ጠጅ ቤት ይገኘው ገባሁ ። የቤቱ ስፋት ፡ የጠጭው ብዛት ፡ ጫጫታው ፡ ሙቀቱ... ከራስ ጸጉሬ እስከግር ጥፍሬ ላብ አሰመጠኝ ። አፍሬ ቶሎ ይገኘው ወጣሁ ። ትቼው ለመሔድ ባስብ ፡ የበላሁት ዳቦና የጠጣሁት ጠጅ ውለታ ሆነው ከበዱኝ ።

"እኔ አፈርኩ ፤ እዚያ ሁሉ ሰው ፊት መቆም አልችልም ። ከፈለጉ እቤትዎ ላድርስዎትና ልሒድ" አልኩት ።

"ደሞ ምን ያሳፍርሃል ? አልሠረቅክ ፡ አልቀጠፍክ ፡ እኔ ለለመንኩ አንተ ምን ያሳፍርሃል ? ይልቅስ እንደ አህያ ከመሸከም ፡ ለምኖ መብላት አይሻልም ? 'እኔ ልምራህ ፡ እኔ ልምራህ' እያለ የሚለምነኝ ሰው ሞልቷል ። ስሰክር እየደበደቡኝና እየሠረቁኝ ስላሰለቹኝ ነው እንጂ ። ይልቅስ ነገ ማርያም ስለሆነች በደንብ እንድለምን ለጠዋት መቅመሻ አሁን ቶሎ ቶሎ ለምነን በጊዜ ወደ ጡረታ ሠፈር እንሒድ ። ላንተም ከለመንኩት ገንዘብ አካፍልሃለሁ ። እና በሌሊት ተነሥተን ማርያም መሔድ አለብን ። አረቄና ጠጅ ካልቀመስኩ ደሞ ጉሮሮዬ ተዘግቶ መለመን አልችልም ።"

ጡረታ ሠፈር የለማኞች መንደር ነው ። እቤት እንደ ደረስን ከዚህ ቀደም ይመራው የነበረው ሰውዬ ሲፈልገው ውሎ ኑሮ ፡ ዐይነ ስውሩ ሰውዬ ቤት ውስጥ ተቀምጦ አገኘነው ። እኔን አይቶ አዝኖልኝ ይሁን ፡ ተመቅኝቶኝ እንዲህ አለኝ ። "ምና ልባት የውበቴን ጠባይ አታውቀውም ይሆናል ። በጣም ርጉም ሰው ነው ። መለመን ፡ መስከር ፡ መረበሽ ያበዛል ። እንኳን አንተ እኔ

ንኳ እየመከርኩና እያስፈራራሁ አልቻልኩትም ። ሲጠጣ እብድ ነው ። ካልጠጣ ደግሞ መንቀሳቀስ አይችልም ።

ሚስቱ ደግሞ ውሻ በጨው አይነካትም ፡ ቆንጆ ናት ብሎ የፎከረባት ፋጤ ለማኟ ።

የዚያለት ማታ ሰዉ ሁሉ ከውበቴ ይልቅ ለኔ ሲል መጸወተው ብልህ ይሻላል ። ላቤ ባሥር መንታ ሲወርድ ፡ ሰውነቴ እንደቂጠማ ሲያረግድ ፡ ዐይኖቼ እንደ ተከበበ አውሬ ሲንከራተቱ በኃፍረት ተውጬ አመሸሁ ።

ልቤ በሁለት ነገር ተከፍሎ ፡ ሌሊቱን በኀዘንና በደስታ አሳለፍኩት ። ኀዘኔ በየመጠጥ ቤቱ ስንዞር ፡ በተለይም ቀይ መብራት ባለባቸው ቡና ቤቶች ውስጥ የደረሰብኝ ኃፍረት ነው ። አንዱ ሰክሮ ሲወላገድ ፡ ሌላው በለብታ ሲለፈልፍና በምፀት አነጋገር ሲናደፍ ፡ ዘበኛው ሲገፈትረን ፡ ባለመጠጥ ቤቷ ስት ነጫነጭ ፡ ሌላው ጠጭ ከሸርሙጦች ጋር እየተላፋ የጉሪጥ ሲመለከተን ግራ ገብቶን ነበር ። ደስታዬ ግን ፡ ገንዘብ አግኝቼ ለጊዜው ወስፋቴን መግደልና ወደ ሀገሬ ለመመለስ ጓጉቼ ስለ ነበር ነው ።

አንድ ሰውዬማ ፡ የለበስኳትን ቁምጣ ሱሪ አይቶ ጭኑ ላይ እስቀምጦ የሚዳራትን ሴትዮ አጭር ቀሚሷን እየገለበ ፡ "አንተ ደግሞ ፋሺን ማድረግህ ነው ይህን ዐርባ ቅልጥምህንና ጭንህን በየቡና ቤቱ የምታስመርቅ?" አለኝ ።

ቡና ቤት የነበረው ሁሉ ሳቀብኝ ። ሰማይ ልሁን መሬት አላውቅም ። ኃፍረትና ንዴት ተናንቀውኝ ደሜ እሳት ላይ እንደ ተጣደ ጀበና ሲፈላ ፡ ላቤ በፊቴ ክንብል ብሎ ፈሰሰ ።

አይፈረድበትም ፡ የአዲስ አበባ ሰዎች ቦላሌ ሱሪ ሳይታጠቁ አይሔዱም ። ሴቶች ግን ፡ ለኃፍረት መከለያ የበለስ ቅጠል የምታህል ግልድም ነው የሚያገለድሙ ። ሲቆሙ ይሻላል እንጂ ሲቀመጡማ ሙታንቲያቸው ይታያል ። ከነሱ ይልቅ ወንዶች የሚያፍሩ ይመስላል ። ሴቶቹማ ቢያፍሩ ኖሮ ፡ ራቁታቸውን ይሔዱ ኑሯል ? ለነገሩማ ነጭ ጠጉር ያበቀለው ሰውዬ ሸርሙጣ ጭኑ

ላይ ሲያስቀምጥ ያላፈረ ፡ ወንድ የወንድነቱን መለያ ጢሙን ተላጭቶ ሕፃን ልጅ ሲመስል ያላፈረ ፡ የኔን ቁምጣ ሱሪ ከሜኒ ፋሽን ጋራ አወዳደራት አይደል !

ሌሊት ተነሥተን ወደ ቅድስት ማርያም ሔድን ። እዚያም እንደ ደረስን ፡ ውበቴ ዐረቄ ቤት አስከፈተና አነዷን ብርሌ ካቲ ካላ በባዶ ሆዱ ጨለጣት ።

እዚህ ሲለምን ዳቦ ፡ እዚያም ሲለምን ዳቦ ስለሚሰጠው ፡ "አንተ ልጅ ምንም አላወቅህበትም ። እኔ ሳንቲም እንጂ ዳቦ አልፈልግም አለኝ ። እውነትም እኔ ዳቦ የያዙ ሰዎች ብቻ ነበር የማሳድድ ። ውበቴ በልመና ዜማ ነው የሚለምን ። እሱ እን ዳለኝማ ድምፁ የአዲስ አበባ ለማኞችን ሁሉ የሚያስከነዳ ነው ። ሲያንቆረቁረው እንኳን ሳንቲም ወፍ ያረግፋል ።

እንዴት እንደሚለምን እስቲ ጥቂት ግጥሞች ልንገርህ ።

'ዐይኔን ግንባር ያርገው ብላችሁ አትማሉ ፡
ይቸግር የለም ወይ መሪ ማባበሉ ፡

* * *

ራቴም ምሳዬም ሆኖ በሰው እጅ ፡
አልቅሼ እበላለሁ ፡ እንደ ሕፃን ልጅ ።

* * *

ሙሉ አካል ነበረኝ እኔም እንደ ሰው ፡
አምላክ ወሰደብኝ የማይከሰሰው ።"

የመጨረሻው ግጥም ምን አሳሰበኝ መሰለህ ? ልጅ ሞቶ ባት ኀዘን ላይ የነበረች ሴትዮ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቃ ጥሎ ባየች ጊዜ የገጠመችው ፤

"አሮ የማርያም ልጅ ፈሶ ወልደ ማርያም ፡ አንተ እዚያ ላይ ሆነህ ስታላግጥ በሰው ፡
እናትህ ነደደች ኀዘንን ቅመሰው ።"

የልመና ግጥም ማለቂያ የለውም ። ለዚያውስ ምኑ ይጥም ብለህ ነው ? ውበቴ ይበልጥ የሚያሳዝን እንዲህ ሲል ነው ።

"ሞት ይቅር ይላሉ ሞት ቢቀር አልወድም ፡
ዕንጨቱም ድንጋዩም ከሰው ፊት አይከብድም ።"

"የጃንሆይ ብር ይሰጣል ወደሚባልበት ቦታ እንዳትወ ሰደኝ" አለኝ ።

"ለምንድን ነው ጃንሆይ ለድሆች አዝነው ብር ሲመጸውቱ እርስዎ አልቀበልም የሚሉ ?" ብዬ ጠየቅሁት ።

"አንተ የነእንትናን (የለማኝ] አለቃውን ስም ጠርቶ) ዘዴ አታውቅም ። አዝነው መሰለህ ? አይደለም ። ብዙ ጊዜ ታፍ ሰን የምንታሰር የጃንሆይን ብር ተቀበሉ ተብለን አንድ ላይ ስንኩለኩል ነው ። አፈሳ በሌለ ቀን እንኳ ፡ ዞረን እንዳንለምን ከተቀመጥንበት ቦታ እንዳንነሣ ያደርጉና ሰዉ ሲበተን ይለቁ ናል ። ስጡ በተባለ ቀን ካሥርና ከኻያ የበለጠ ለማኝ አያገኙም ። አንድ ጊዜ ባንድ ዳር ፡ ሌላ ጊዜ በሌላ ዳር ፡ ጣልቃ ገብተው አመኻል ማደል ይጀምሩና ፡ 'እኔ አልደረሰኝም ! እኔ አልደረ ሰኝም !' እያለ ለማኝ ሲፋጅ ፡ አንድ ከረጢት ብር ይዘው ይሔዱና የለማኝ አለቆችና የጃንሆይ አንጋቾች ተከፋፍለው ይበሉ ታል ። ድሮውንም የውሸት ረብሻ የሚያስነሡት ተካፍለው ለመብላት እንዲያመቻቸው ነው ።"

ዓለም ከተፈጠረ ፡ ዘመን ከተቈጠረ ጀምሮ ድሃና ድህ ነት ፡ ርግማንና ምርቃት ተለያይተው አያውቁምና ፡ ያጣ ይራገ ማል ፤ ያገኘ ይመርቃል ።

ትንሽ ቆይቶ ዕልልታው ቀለጠ ። ደወሉ ተደወለ ። ጭብጨ ባው ቀለጠ ። ጃንሆይ መጡ ፤ ኑ ተቀመጡና ብር ተቀበሉ ብለው ለማኝ አለቆች ተናገሩ ። ድሮውኑ ተኩልኩለው ከተቀመጡ መነኩሳት በስተቀር ፡ እዚህ መረብ ውስጥ ገብቶ ለመጠመድ የሚፈልግ ለማኝ ታጣ ።

ቆይቶ ፡ ቆይቶ ለማኝ በያለበት ሩጫውን ተያያዘው ። እመ ጫቶች ሁለት ሦስት ልጅ ይዘው አንዱን አዝለው ፡ ሌላውን ታቅ ፈው ሦስተኛውን እየጐተቱ ይሮጣሉ ። ሽማግሎች ይጐተታሉ ። ቆማጦች እንደ ነጋበት ጅብ ጐንበስ ቀና ይላሉ ። "የምን ሽሽት ነው ?" ብዬ አንዱን ጠየቅሁት ። "አፈሳ ተነሥቷል" አለኝ ።

የዚህን ጊዜ ውበቴ እኔን ለቀቀኝና ሩጫውን ጀመረ ። እየ ሔደ ከየሰዉ ጋር ይጋጫል ። ሮጬ ደረስኩበት ። ልብሴን ይዞ

እየጐተተ ከየድንጋዩ ፡ ከየምሰሶው እየተጋጨ ፡ እየወደቀ ፡ እየተነሣ ብዙ ሮጥን ። ጫማ ስለሌለው እግሮቹ ደም በደም ሆኑ ።

"እኮ ምንድን ነው ፡ ይህን ያህል የሚያስሮጠን?" ብለው ፡

"አፈሳ አታውቅም?" አለና ጠየቀኝ ።

"አፈሳማ ዐውቃለሁ ። ብዙ ኩሊዎች እየታፈሱ ወርቅ ቁፋሮ አዶላ ይላካሉ ሲባል ሰምቻለሁ ፡ በዐይኔም አይቻለሁ ። እኔን ያልገባኝ የለማኞች አፈሳ ነው ። እነሱም ወርቅ ቁፋሮ ይላካሉ እንዴ?" ብዬ መልሼ ጠየቅሁት ። መልሱን ሌላ ጊዜ በረጅሙ ነገረኝ ።

የማርያም ለት ሸሽተን አመለጥን ። እኔም ውዬ አድሬ ከጡረታ ሠፈር ለማኞች ብዙ ነገር ዐወቅሁ ።

"ጡረታ ሠፈር ፡ የለማኝ አለቃ ፡ አፈሳ"

እነዚህን ሦስት ቃሎች ላብራራልህ ።

ጡረታ ሠፈር ፡ ከተክለ ሃይማኖት በታች ያለ የለማኝ መንደር ነው ። ጣሊያኖች ጥቁር ሕዝብ አይወዱም ነበር ይባላል ። እንግዲህ ለማኝ ምን ያህል እንደሚጠሉ አስብ ። ለማኞችን ፡ በተለይም ቆማጦችን ፡ ካዲስ አበባ ለማጥፋት እኩሉን በመርዝ ፡ እኩሉን በጥይት ፡ ግማሹን ባካፋ ፡ ግማሹን በእሳት ገድለው ለመጨረስ አሰቡ ። ነገር ግን ፡ የለማኙ ቁጥር በማነስ ፋንታ እየበዛ ስለሔደ ፡ 'ለማኝ መፍጀት ያዲስ አበባን ሕዝብ መጨረስ ነው' ብለው ከከተማው ዳር የለማኞች ከተማ ተቆረቆረ ። ዛሬማ የከተማው እንብርት ሆኗል ። አሁን ደግሞ ያዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ እንዲፈርስ ትእዛዝ ሰጥተዋል ይባላል ። መቼም ገንዘብና ሥልጣን የሌለው ሰው አዲስ አበባ መኖር አይችልም ።

የለማኝ አለቆች ፡ ደግሞ "ዘነቡ" በምትባል የመንግሥት መኪና ድሆችን እያፈሱ ፡ በየፖሊስ ጣቢያው የሚያሳስሩ ናቸው ። እውነቱን እንናገር ከተባለ ፡ መንግሥት በደመወዝ የቀጠራቸው አንድ ጡረታ የወጣ ወታደርና አንድ ሾፌር ብቻ ናቸው ። ሌሎቹ ግን ፡ ጉቦ ለመብላትና ለማጐብጐብ የሚቋምጡ ወመኔዎች ናቸው ።

በየተዝካሩ ፡ በየሠርጉ ቤት ፡ ሳይጠሩ የሚያጋፍሩና የመኳንንቶችን ስም እያጠኑ የሚቀላውጡ ምናምንቴዎች ናቸው ። ሲማቱ ፡ ሲጥፋተሩ ፡ ለነገ አይሉም ። ሲመቻቸው ኪስ የሚበረብሩ ፡ ሳይመቻቸው የሚፈትሉ ፡ ከሆዳቸው በስተቀር ሌላ ነገር የማያውቁ እሪያዎች ናቸው ።

አፈሳ ሲጀመር ሴት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ዐዋቂ ፡ እመጫት ፡ እርጉዝ ፡ ቆማጣ ፡ ጤነኛ ሳይሉ ዐሥር ሰው በማትጭን መኪና ዐርባ ሃምሳውን አጭቀው ፡ በእሳት አደጋ መኪና ፍጥነት እያበረሩ ለማኞችን የሚያሳስሩ ናቸው ። ቶሎ ቶሎ ለማመላለስ ።

በነዚህ በቁጥር ካሥር በማይበልጡ አሳሞች እጅ የወደቅሁ ዕለት አንድ ተረት ትዝ አለኝ ።

ዘጠኝ ሰዎች አውድማ ላይ እንዳሉ ፡ አንድ ሽፍታ ይመጣባቸዋል ። እነሱም ያዩትና ጭድ ውስጥ ይደበቃሉ ። ሽፍታው ከነሱ የተረፈ ምግብ አግኝቶ ይበላና ሊሔድ ሲል ፡ የውሃ ቅል ያይና በጦር ይወጋዋል ።

"እየው ሰው መስሎት!" ይላል ከተደበቁት መካከል አንዱ ፤ ሽፍታው በጦር ወግቶ ይገድለዋል ። "ወይ አፍ አለማረፍ!" ይላል ሌላዉ ። እሱንም ይገድለዋል ። "እኔ እሻል ዝም ያልኩት!" ይላል ሌላዉ ። እሱንም ይገድለዋል ። እንዲህ አድርጎ ስምንቱን ገድሎ ይሔዳል ።

አንድ ሰው ይተርፍና ወደ መንደር ሮጦ ይሔዳል ። አፋፍ ላይ ይቆምና ፡ "ጸረ ስሚ! ስሚ!" ብሎ ሚስቱን ይጣራል ። "ወይ!" ትለዋለች ። "ዘጠኛችንን አንድ ሽፍታ ፈጀን!" ይላታል ። "ዘጠኛችንን ዘጠኝ ሽፍታ ፈጀን!"

"ለጉኖ! አንድ ብቻውን ሆኖ እየተሽሎኮሎከ ፈጀን እንጂ ፡ ዘጠኝ ከሆኑማ አንዳንዳቸውን አንይዛቸውም ኑሯል?"

መንገድ ላይ አንድ ጐረቤቱ ያገኘውና ፡ "እንዴት ሆናችሁ?" ብሎ ይጠይቀዋል ። እሱም "መቼም ምንም አንል ፤ ከዘጠኛችን አንድ ተርፈናል" አለው ይባላል ።

የለማኝ አፈሳ የተጀመረው ፡ ብዙ ያፍሪካ ነገሥታት አዲስ አበባን እንዲጐበኙ ጃንሆይ ጠርተዋቸው የመጡ ሰሞን ነው ይባላል ።

ካዲስ አበባ በስተምሥራቅ ትልቅ መጋዘን ውስጥ ብዙሺ ለማኞች ታሰሩ ። ዙሪያውን በሽቦ ታጥሮ ፡ ባጋም ተሸምጦ ፡ ሳፈላማ እንደ ተያዘ ከብት ለማኞች በ"ላም በረት" ታጐሩ ።

አፈሳ ቢሉህ ለልመና የወጡትን ብቻ መሰለህ? አይደለም ። ቆማጣ ፡ ዐይነ ሥውር ፡ ሽባ ፡ አንካሳ ፡ ዲዳ ፡ ኮልታፋ ፡ ፎቃቃ አሮጊት ፡ እመጫት ፡ እርጉዝ ፡ እነዚህ መቼም ሮጠው የማያመልጡና የመጀመሪያዎቹ ታሳሪዎች መሆናቸው አያጠራጥርም ።

የባሰ አታምጣ እንዲሉ ፡ ጨርቃሙ ፡ ዕብዱ ፡ ደንቆሮው ሳይቀር ከየቤቱ እየተለቀመ ታሰረ ። መታሰር ብቻ መስሎህ ነው? እሱማ ቢሆን... የፈጃቸው ውሃ ጥሙና ራቡ ነው ። ውሃ ጠፍቶ መስሎህ ነው? ገፈርሣ ሳይነጥፍ? እህልም አልጠፋ ። ስንቅ የሚያቀብሉ ቤተሰቦች ፈርተው ቢቀሩ እንኳ የበጐ አድራጎትና የጃንሆይ እርዳታ ይታዘዝላቸው ነበር ። ነገሩ ሌላ ነው ። ለጉብኝት የመጡት ያፍሪካ ነገሥታት ባገራቸው ድሃ የሌለ ይመስል ፡ እዚህ መጥተው ሲያዩ እንዳይሣቀቁ ተብሎ የተደረገ ዘዴ ነው ።

ጃንሆይ ከዚያ ሁሉ ደግነታቸው ፡ ከዚያ ሁሉ ፈሪሃ እግዚ አብሔር ፡ የገዛ ድሆቻቸውን እንዴት አንዳንድ ጥይት ነፈጓቸው ብዬ ተገረምኩ ።

የሚገርም ነገር ደግሞ ፡ ረሃብና በሽታ የጨረሳቸው አንሶ ፡ ሬሣ ሮጦ ያመልጥ ይመስል ፡ በወታደር በጥብቅ እንዲጠበቁ መደረጋቸው ነው ።

አፈሳው ግን ፡ ያፍሪካ ነገሥታት አዲስ አበባ ሲመጡ ብቻ ሳይሆን ፡ ጃንሆይ በሚያስቀድሱበት ቤተ ክርስቲያንና የውጭ አገር ሰዎች በሚያዘወትሩት አካባቢም ተለምዶ ቀርቷል ።

ውበቴ መለመን ብቻ አይምሰልህ ። መዝፈንም ይወዳል ። ቅኔም ተምሯል ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የልጅ የመሰለ ጥያቄ ይጠይቃል ። "ሴቶችና ወንዶች በምን ተለይተው ይታወቃሉ?"

"በብዙ ነገር ይለያያሉ ። ሴቶች ድምፃቸው ቀጭን ነው ። ጉትቻ ያደርጋሉ ። ጸጉራቸውን ያሳድጋሉ ። ይተኩሳሉ ። ሻሽ ያስራሉ ። ቀሚስ ይለብሳሉ ፤ የሴት ቦርሣ ይይዛሉ ። መልካቸው ያምራል ። ሲስቁ ያምራሉ ። ቂጣቸው ትልቅ ነው" አልኩት ። "ፋጤ ቂጥ ትልቅ ነው?" (ፋጤ ሚስቱ ናት)

"መቼም ካንተ ቂጥ ይበልጣል ።"

"ለምን አልነገረችኝም?"

"ባትጠይቃት ይሆናላ!"

"ጠጅ ምን ይመስላል?"

"ቢጫ"

"ቢጫ ምን ይመስላል?"

"አደይ አበባ ።"

"አደይ አበባስ?"

"ያዲስ አበባ ባሕታዊዎች የሚለብሱትን አንሶላ ይመስላል ።"

"ጥቁር ምን ይመስላል?"

"ኑግ"

"ኑግስ?"

"ኑግማ ከሰል ይመስላል ።"

"ከሰልስ?"

"የጳጳስ ቆብ ።"

"ፈረንጆች ነጭ ናቸው የሚባል እውነት ነው?"

"አዎን ነጭ ናቸው ።"

"ምን ዐይነት ነጭ?"

"ሊጥ የመሰለ ።"

"አረንጓዴ ሰው አለ?"

"የለም ። ቢኖርም ይታሰር ይሆናል ።"

"ለምን ይታሰራል ?"

"የሰው መልክ አረንጓዴ ስለማይሆን ነዋ! ባጋጣሚ ሆኖ -ከተገኘም ሰው እንዳያስደነግጥ ይታሰራል ፤ ወይም ይገደላል ።"

እኔማ የጃንሆይን ቤተ መንግሥት ከሩቅ ሳየው እንኳ እጠላዋለሁ ።

አዲስ አበባ እንግዳ በነበርኩ ሰሞን ፣ "አዳሪ ትምህርት ቤት እንዲያስገቡን ጃንሆይን ለምናቸው" የሚለኝ ሰው በዛና እውነት መስሎኝ አንድ ቀን መኪናቸውን አስቆምኩና ለጥ ብዬ እጅ ነሣሁ ። ከወደቅኩበት ሳልነሣ የጃንሆይ አንጋቾች ረግጠው ፣ ረግጠው በጥፊ በቡጢ ፣ በሰደፍ አሬን አበሉኝ ።

"አንድ ቀን ዐይናቸውን አይቼ ብሞትም አይቆጨኝ" ስል የነበርኩት ሰውዬ ፣ ወዲያውኑ ሞታቸውን ተመኘሁት ።

አትደብድቡት በማለት ፋነታ ሦስት ብር ምጽዋት ዘረጉ ልኝ ። እንዴት ዐይናቸው እያየ ያስደበድቡኛል ብዬ ፣ እልህ ያዘ ኝና ሦስት ብራቸውን ወርውሬላቸው ሔድኩ ።

በመንገድ ዳር የቆመው ሕዝብ "አትዎ ቱት! አትገፍት ሩት!" እያለ ሲጮህ ፣ ንጉሡ በኔ ላይ ብቻ ጦርነት ያወጁ መስለኝና ኩራት ተሰማኝ ። "ዎን ዐይነት ደግ ሕዝብ ነው!" እያልኩ የደስታና የቁጭት እንባ እያነባሁ ሔጄ ተቀላቀልኩ ።

አሽከሮቻቸውን ባይልኩብኝ ኑሮ ፣ እኔና እሳቸውን ትግል ጥሎ ቡጢ ብነገጥም አያሸንፉኝም ነበር ።

ጃንሆይ ፣ ድሃ የሚጠሉ የምራቸውን መሆኑን ዐወቅኩ ፤ ጠላ ኋቸው ።

የላም በረቱንም እልቂት እንዳይቀጥል ያደረገው ያስተማ ሪዎችና የተማሪዎች ተቃውሞ ነው አሉ ። አጥር ጥሰው ገብ ተው የሞቱትን ሰዎች ፎቶ እንሥተው ፣ ሕፃናት የሙት እናቶ ቻቸውን ጡት ሲጠቡ የሚያሳይ ፎቶ ጨምረው ለዓለም መን

ግሥታት ከክስ ደብዳቤ ጋር ባይልኩ ኑሮ ፣ ውጤቱ ከዚህም የከፋ ይሆን ነበር ።

ያኔ የድሆች እልቂት ሲሰማ ፣ ያዲሳባ ሕዝብ ማቅ ለብሶ በመድ ነስንሶ አለቀሰ ። አዲሳባ ጸጉሩን እየተላጨ ፣ እንባ እየ ተራጨ አዘነላቸው አሉ ። ድንጋጤው ፣ ስቀቀኑ ፣ ጨኸቱ ፣ የይታው ሰማየ ሰማያት ዘልቆ እስኪሰማ ድረስ አለቀሰ አሉ ።

ይህ ወሬ እምልጦ በመውጣቱ ፣ ጃንሆይ ተቆጥተው ሕዝቡ የተማሪ ወሬ ፣ የልጅ ወሬ ፣ አምና እንዳይቀበል ፣ ፎቶ ውንም ከየትም የፈረንጅ መጽሔት የለቀሙት ነው ብለው አስወሩ ።

ሳይታፈሱ ያመለጡ ለማኞች ደግሞ ፣ ከነልጆቻቸው ቤታ ቸውን ዘግተው በችጋር ተቆነደዱ ። ለሽንት ለመውጣት እንኳ ጨለማን ተገን አድርገው ካልሆነ የማይሞክር ነበር ። ለምን ቤት ውስጥ ተዘግተው እንደሚውሉ የማያውቁ ሕፃናት እንዴ ምግብ ፈልገው ፣ ሌላ ጊዜ ጨዋታ አምሯቸው ይላቀሱ ነበር ። ባሊያን ያመጣው ጣጣ ፣ ጃንሆይ ያቀዱት ብልሃት ፍዳቸውን አስጨረሳቸው ።

የያኔ ልመና የዘመነ ኔሮን ክርስትና ሆነች ። የድሃ ዐቅም ለቅሶ ነውና ፣ ድሃ አለቀሰ ። የድሃ ጉልበት እንባ ነውና ፣ አነባ ። ...ምሬት ነውና ተማረረ ።

ያኔ ሥራ የያዘው እንኳ ሳይቀር ለራሱ እየፈራ ፣ ያለችውን ልብስ እያጠበ መውጣትና የጐሪጥ እየተያየ የገዛ ጥላው ሲያባርረው መዋል ሆነ ።

እልቂት ያባባውና እንደ እግር እሳት የቆጠቆጠው ለካ ንስ ግማሽ ለራሱ ፈርቶ ኖሮአል ። ያኔ አዲስ አበቦች ያለቀሱት ለቅሶ ፣ ያሳዩት ኀዘኔታና መተሳሰብ መቼም ታይቶ አይታወቅ ይባላል ።

ያፍሪካ ነገሥታት ጉብኝት ፣ ያን ያህል ሕዝብ ያስጨረሰ የፈረንጅ ንጉሦች ቢጨመሩ ኑሮ ፣ አዲስ አበባ ምን ይውጣት ይሆን ?

ታዲያ ከዚያ ወዲህ አፈሳ በተነሣ ቁጥር ፣ ተማሪዎች አልሰሙ ይሆን ? ይባላል ። ተማሪዎች ደግሞ ለማጭበርበሪያ ለግ ስፈታት ሲሯሯጡ ተይዘው ይታሰራሉ ። አንዱ ሲታሰር ሌላው ለማስፈታት ሲጥር ጠቡ ይከራል ።

ለማጭች ከተፈቱ በኋላ ፣ "መራት ላራሹ" ብለው ይጠይቃሉ ። እንደሚባለውማ በጥያቄ ላይ ጥያቄ ፣ በሰበብ ላይ ሰበብ እየደረደሩ ፣ ንጉሡን ከሥልጣን አውርደው ለማናው እንዴ ልቡ እንዲለምን ፣ ገበሬው እንዴ ልቡ እንዲያርስ የሚያደርግ መንግሥት ለማቋቋም ነው ።

ያየሁትንና የሰማሁትን ሁሉ ጽፌ ከማሰለችህ ፣ እያለፍኩ እያለፍኩ ዋና ዋናውን ብቻ ብገልጽልህ ይሻላል ።

አዲስ አበባ ፣ ዘፈን ሁልቀን እልፈት እንዳለፈ ነው ። ቴፕ፣ ራዲዮኑ ፣ የሽክላ ማዘፈኛው በየሻይ ቤቱ ፣ በየቡና ቤቱ ፣ በየመ ናሪያ ቤቱ ቀንም ማታም ይዘፍናል ።

መኪናው ሌሊቱን ሙሉ እንዴ ሐዲ ያድራል ። ሰው መቼ ተኙቶ ፣ መቼ ይነግል የሚያሰኝ ነው ።

እኔማ "ተማሪ ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ..." ሲባል እውነት መስሎኝ ፣ ዘፈን መዓት ያመጣል እያልኩ ስሸሸው ኖርኩ ።

አዲስ አበባ ለቤትም ፣ ለሱቅም ለድልድይም ፣ ለሽንት ቤቱም ፣ ለምኑም ለምኑም ዘበኛ አለ ።

እንዲያውም ነሽጥ አድርገህ ልናጥ ብትል እንኳ መሮጥ አትችልም ። ዕብድ ነው ባትባል ፣ ሌባ ነው ተብለህ ትታሰራለህ ።

ሌላው ያልነገርኩህ ነገር ፣ ቅድስት ሥላሴ የሚባለው ደብር ሰው ሚማ ሳያወልቅ ወዴ ቅድስት ሲገቡ በዐይኔ አይቻለሁ ። በነገራችን ላይ ፣ አንጻንዶቹ ቤተ ክርስቲያኖች ቅኔ ማኅሌት የላቸውም ።

ሴቶች ሊቀድሱ ነው ተብሎ የተወራውም እዚያው ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ነው ። ሴቶች ሲዘምሩና ተሰጥኦ ሲቀበሉ ማን በዐይኔ አይቻለሁ ።

እሑድ እሑድ ታምረ ማርያም አይነበብም ፣ መክፈልት የሚባልም ነገር የለም ። ሁሉም እንዴ መንገደኛ ስንቁን ቋጥሮ ይመጣል ። ወይም አፉን ሳይሸር ወዴ ቤቱ ይመለሳል ። በስንበት ምድር ዴሞ የውሸት ቄስ ይበዛል ። የውሸት ጥምቀም ይጠመቀምና ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት አስበን ፣ ወይም ቲቃጮን ሳሉበን ፣ ልብሰ ተክህኖውን ሌባ ዘርፎን ፣ ዕጣን መግዣ ቸግሮን ይላል ሥዕሱን ታቅፎ ፣ ታጭል እያቃጨለ ፣ የታቦት ሳላ ዘርግቶ ።

እኔስ ሁሉም ነገር ሰለቸኝ ። ውበቱ እንዴ ለዓታት ቋሚ ከሴሊቱ ዐሥር ሰዓት ይቀሰቅሰኝና ጠቅላይ ግዛት አውቶቡስ ተራ ለልመና እንሔዳለን ። እዚያም ከተሳፋሪ ጋር ትንቅንቅ ፣ ከለማኝ ጋር ጭቅጭቅ ፣ ከሱቅ በደረቴና ከአውታንቲ ጋር ግብግብ እንገጥማለን ። ሲረፍድ መርካቶ አውቶቡስ ተራ ሲመሽ በየቡና ቤቱ መዞሩ ሰለቸኝ ። ከማታ እስከ ማታ ልመና ። ተለምኖ ቋቱ ጠብ ሳይል ነገር ።

የአዲስ አበባ ልመና ውሃ በወንፊት መቅዳት ነው ። ደግሞ የለማኙ መስገብገብ ፣ የመጽዋቹ መንገብገብ አይጣል ። መጽዋት ይንቀጠቀጣል ። ለማኙ ደግሞ ፣ መጽዋቹን ከበባ አድርጉ መሐጁ ይከለክልና ከጁ ለመንጠቅ ይደርሳል ።

ኤዲያ! ሁሉም ነገር ብልጠት ነው ። ማታለል ብልጠት ነው ። ውሸት መናገር ብልጠት ነው ። ካንዱ ሰው ሽፍጠ ሁለት ጊዜ ምጽዋት መቀበል ብልጠት ነው ። በዓል ሲሆን የሰው ልጅ ሠርቆ ወይም ተከራይቶ መለመኛ ማድረግ ብልጠት ነው። ልጇ ሰው ገድሎ የደም ዋጋ የምከፍለው አጥቼ እያሉ መለመን ብልጠት ነው ።

ገና ለገና ገንዘብ ለማግኘት ሲል ፣ ስንቱ ጤነኛ ሰውነቱን በእሳት አታጥሉ ያቆሰለዋል ። ጤነኛ እጆቹንና እግሮቹን በሻሽ

ያሥርና ደም የመሰለ ቀለም ተብቶ መለመን ። ያልሆኑትን መሆን የተለመደ ነው ።

እጅና እግር አጥቶ ተጉማምዶ ፣ እየተንፏቀቀ እንኳ ደብ ልጥ ለማሳዘን ሲል ሰውነቱ ደም እስቲወጣው ያከነዋል ።

ሙሉ ጤነኛ በመሆናቸው ስንቶቹ ይበሳጩ መሰለህ ፣ ለምንው በሚያድሩ በሽተኞች ይተናሉ ። ስንቶቹ የውሸት ዐይነ ሥውር ሆነው ዕድሚያቸውን በልመና ገፍተዋል ። ጤንነት ብቻውን ምን ዋጋ አለው ?

በግዞት የሚኖሩ አንድ ባሕታዊ አሉ ። ሁልጊዜ ጠፍተው ይመጡና ሲያስተምሩ ተይዘው ተመልሰው ግዞት ይላካሉ ። አንድ ቀን እየኋቸው ። ጀንሆይ ሊያስተድሱ መጥተዋል ። አንድ የውሸት ባህታዊ "የዕንጨት ቀንበሩን የሰበረ የብረት ቀንበር ይሠራበታል ። መኳንቲንና ተከታዮቹን ለሚንቅ በላዩ የምድረ በዳን አውሬ አሠለጥንበታለሁ ። ላንበሳና ለዘንዶም ተነሣ እደርገዋለሁ ።" እያሉ ይሰብኩ የነበሩትን በጣም ገሠጻቸው ።

ባሕታዊ የመሰሉ ነጭ ለባሾች እኮ ሞልተዋል ። ግዞተኛው ባሕታዊ የጃንሆይ መኪና ጆሮ አብቅላ ትሰማቸው ይመስል ጣታቸውን ወደሷ ቀስረው ፣ "እንተ ዋብዝ የተበሮ ባሕታዊ ወዮልህ !" ግርማ ሞገስ በተሞላበት አረማመድና አመለካከት ሕዝቡን እያስተዋሉ ፣ "እነዚህን ነቢያተ ሐሰት የበግ ለምድ የለበሱትን ተዋቸውና የልጆቻችሁን የተማሪዎችን ድምፅ ስሙ" አሉ ። "እግዚአብሔር በሕፃናት አንደበት ይናገራል ። ሕሊናቸው በገንዘብ ያልተሸጠ ፣ ቀንበርን የሚሰብሩና እስራትን የሚበጥሱ እነሱ ናቸውና ። መሮጥና ማምለጥ ፣ ማየትና መታገል የሚችሉ ድሆች በኃይለኞች ክንድ እየታነቁ በከባድ መዳፍ እየተደቆሱ ፣ ወደ ሞት ባድማ ወደ ላም በረት ሲጣሉ የጮኸላቸው ማነው ? ቤተ ክርስቲያን ናት ? እነአባ ናቸው ? አይደሉም !

"ለደም ክተማ ወዮላት ! በሁለንተናዋ ቅሚያ ሞልቶባታል ።" ጣታቸውን ወደ ጃንሆይ መኪና እያመለከቱ ፣ "ባለመልኳ ።" ጣታቸውን ወደ ጃንሆይ መኪና ይዘንጣል ። ድሆች በረሃብ ያልቃሉ ። አዲስ አበባ ሆይ ልብስሽን በፊት እንልማለሁ ፣ ጋሩሪት ሥጋሽንም ላንሳም መንግሥታት አላያለሁ ። ሶንሶን ፣ ፖል ዮሙ የያርተሻል ። ንጉሥሽ ወራዳ ነው ፣ ሕዝብሽን ... " ሲሉ የፉቸውን ሳይጨርሱ ፖሊሶቹ እያሉት ፣ እየጎተቱ ወሰዷቸው ።

ለካንስ እንፈታውራለ ደምስ አላምረው የጉጃምን ሕዝብ ሲያስጉትቱት ፣ በዱላ ሲቀጠቅጡት ፣ ወደራሩ ሲዘ ውሃ ቀጠን ብለው በየገበያው ሲሰቅሉት ጃንሆይ እያ ነው ዝም የሚሉ ።

የዱሮው እግዚአብሔር ሊያሩሳሌምን ሲያጠፋ ዜት ፣ ሀብታም ፣ ቄስ ፣ ነጋዴ ሳይለይ ነበር ። የዘመኑ እግዚአብ ደግሞ ፣ ከሰውም ሰው ድሆችን ፣ ከሠርም ሀገር እንዳንድ ከሆማ ብቻ ይቀጣል ።

የሠፈራችን ልጆች ውበቴን ሲያዩሽቴት ፣ "ውበቴኮ ሆላም ነው ፣ ዐሥር እንጀራ አይመክተውም" ይሉታል ፣ በጣም ይና ይሳል ። ምክንያቱም ለምግብ ይህን ያህልም ነው ። መጠ ከጠማ እህል አያምረውም ።

"ውበቴኮ አንድ ብርሌ ጠጅ መጠጣት አይችልም" ሲሉት "እንግዲያውስ እናንተ ናችው ትናንት ዐሥር ብርሌ ጠጅ የጠ ጣችሁልኝ ?" ይላቸዋል የምሩን እየተናደደ ።

የኛ ሀገር ቅዳሴ በጸጥታና በጥሞና ነው የሚከናወን ። ቅዳሴ ከጣቡ በኋላ በቅጥር ውስጥ ያለ አይወጣም ። ውጭ ያለ አይ ገባም ። መላዕክት እንደ ቅጠል ይረግፋሉ ፣ እንደ ሻሽ ይነጠ ፋሉ ስለሚባል ።

አዲስ አበባ ደግሞ የተገላቢጦሽ ነው ። ለማኞች ያረጀው ላይ እየወጡ ሲለምኑ የሚያሰሙት ዜማ ፣ ከቤተክርስቲያኑ ድምፅ ግጥያ ጋር ይርካከራል ።

እዚህ አንድ ዕብድ ይለፈልፋል ። እዚያ አንድ ባሕታዊ ይሰብካል ። በሴላ በኩል የመኪኖች ጩኸትና መርመስመስ ሌላ ጉድ ነው ።

ያዲሳባ መኳንንትና ሴት ወይዛዝርት ደግሞ ተያይተው የማያውቁ ይመስል ፥ ቤተክስርቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ወሬና መሳሳም ያበዛሉ ። አንዱ ይወጣል ። ሌላው ይገባል ። ቅዳሴ ገብተው እስቲወጡ ድረስ አስችሎት የሚቆይ የለም ።

አንድ ቀን ፥ ለገሐር ስንለምን ሁለት ባለመኪኖች ፥ "ይሽ ሕዝብ በሙሉ ለማኝ ሆነ ልበል?" አለ አንደኛው ፊቴን ኮስ አስመስሎ ። "እኔን የሚያናድዶኝ እኛን በመለመናቸው አይደለም ። አንድ ቀን አንድ አሜሪካዊ ፥ 'የሀገር ለማኞች መኀገድ ከለከሉኝ' ካለኝ ወዲህ አሜሪካዊውን ሳየው አፍራለሁ ። ለማኞች ሳይም እሸማቀቃለሁ" አለው ።

አቅኝ ለማኞች ፥ እኛን መጪዎችን አይወዱንም ። "እናንተ ከመጣችሁ ወዲህ ነው ያዲሳባ መኳንንት ልቡ የጨከነና ለማኞችን መርዞ የጠላን ። ዱሮ ለማኝ ብርቅ ነበር ። ካንድ ብር በታች የሚመጸውት አልነበረም" ይሉናል ። ግን ዐልፎ ላቸው አላየሁም ። ከኛ እኩል ልመና ይንከራተታሉ ።

መንጋ ለማኝ ፥ ሰማይ ሲዞርበት ጊዜ በኛ ያሳብባል ። ላን ዲት ፋርኖ የሚደረገው ግብግብ መፈጠርን ያስጠላል ። ዱሮ በኩሊነቱ አንድ ዘንቢል ለመሸከም ብዙ ኩሊ ግብግብ ይፈጥ ርና ይደባደብ እንደነበረው ዐይነት ነው ። እንዲያውም አዲሳባ ሣር ቅጠሉ ብር ብር ይላል ።

ንጉሡን ማማት በጥብቅ የተከለከለ ነው ። ባትወዳቸውም እወዳቸዋለሁ ማለት አለብህ ። አለበለዚያ ጆሮ ጠቢ ያሻውክብ ሃል ።

አንዱ ብልጥ በዚህ እንዴት እንደሚጠቀም ልንገርህ ። ምንም ገንዘብ ሳይኖረው መጠጥ ቤት ይገባል ። ከዚያ አንዱን መኳንንት ጠጋ ብሎ ፥ "ጌታዬ ከሁሉ አብልጠው የሚወዱትን ዐውቃለሁ" ይላቸዋል ።

"ሐሰት! አታውቅም" ይሉታል ።

"እንወራረድ!" ይላቸዋል ።

"ሃምሳ ብር እሰጥ!" ይሉታል ።

"ግድየለም ዐሥር ብር ይበቃል" ይላል አጅሬ ።

"መልካም" ይላሉ ።

"ከሁሉ አብልጠው የሚወዱ ጃንሆይን ነው" ይላቸዋል ። መቼም ከሥር ብር ሕይወት ይበልጥባቸዋልና ዐውቀው ይረታሉ ።

የጃንሆይ ነጭ ለባሽ ፥ እንዳገርህ ነጭ ለባሽ አይምሰልህ ። አንድ ነጭ ለባሽ ከበርቴዎችን ከበርቴ መስሎ ፥ ተማሪውን ተማሪ መስሎ ይጠጋል ። ዕብድ መስሎ ራቁቱን እየሔደ ነው ። አንድ ጥይት ሳይተኩስ ሺ ገድሎ የሚገባ ነው ።

ይህን ይብዳቤ አንብበህ ስትጨርስ ቅደደው ፤ አለበለዚያ መዘዝ ያመጣል ። 'ያልጠረጠረ ተመነ ጠረ' ተብሏልና ፥ በንዝህላልነት ከጅህ ካመለጠ ወዮልህ ። ጃንሆ ይ ነገርና ሰው አይንቁም ጸይመስልህ ። እኔማ ከቤተ ክርስቲያን የወጣሁለት ባላፈርስም አፍርሻለሁ ። ጃንሆይ ፊት የተደበደብኩለት ባልሞትም ሞቻለሁ ።

ጃንሆይ ፥ በቁመት ካፍ የወደቀ ጥሬ ያክላሉ ። ጠድፍ ጠድፍ እሚያካክሉ አንጋችች መካከል ስታያቸው ሕፃን ይመስላሉ ። ያ ሁሉ መኳንንት በዙሪያቸው ሲያዘጠዝጥ ያስገርማል ። ያስት ማል ።

የባሰ የሚያስገርም ደሞ ፥ ጃንሆይን ለማየት የሚደረገው ግፊ ያና ትንንት ፥ የፖሊሶች ዱላና ርግጫም አይደለም ። እንደ መልክአ ማርያም ፥ እንደ መልክአ ኢየሱስ ሁሉ መልክአ ኃይለሥላሴ ተደርሶላቸው ፥ ያዲሳባ ምዕመናን በትጋት ሲጸልዩበት ማየት ነው ይበልጥ የሚያስደንቅ ።

በቅዳሴውም ፥ በቅኔውም ፥ በጸሎቱም የጃንሆይ ስም ሺ ጊዜ ካልተጠራ ቅዳሴውም ቅዳሴ አይደለም ፤ ቅኔውም ቅኔ አይደለም ።

ለካንስ በመላዕክት ፋንታ ነው ፥ አንጋችች በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚሰለፉ ። ለካንስ በሰይፍ ፋንታ ነው አንጋችች

ሳንጃቸውን መዘው የሚቆሙ ፣ እንደ ቀሳፈ መላክ ። መላእክት እንዴ ሻሽ ይነጠፉሉ ይባላል ። እኔን ያልገባኝ እንጋጆች እንደ ሐውልት መቆማቸው ነው ።

ጃንሆይ ፣ መቸም ጃንሆይ ናቸው ፣ ሰይጣን ልባቸውን እደን ድናታል ። ካህናትስ ? ኤጭ ! እነሱስ ዱሮም ያው ናቸው ።

እረ ምዕመናን ምን ነክቷቸው ነው ፣ መዛታቸው እንሰ ገነት እንዲያገቡዋቸው ወደው የሚጸልዩ ?

ስንት ደካማ እናቶችና አባቶች ፣ ከነጸሎታቸውና ከነምሕላ ቸው ጥርኝ አፈር ሆነው የቀሩ ፣ በጃንሆይ ትዕዛዝ አይደለም ?

ያ ሁሉ ለማኝ ፣ ያ ሁሉ የልመና ቀረርቶ ፣ ያ ሁሉ ማላዘን መለማመጥ ፣ ጥርኝ አፈር ሆኖ የቀረው ፣ የስንት ለማኝ ሕፃናት ሳቅና ጨዋታ ማሳዘንና ፍች በሌለው ልሳን መንተባተብ ፣ ጥርኝ አፈር ሆኖ የቀረው በጃንሆይ ግዛት አይደለም ?

እኒያ ሁሉ ከቅዱሳት አንስት የሚቁጠሩ መነኮሳት ፣ እኒያ ሁሉ አበው የተጋደሉት ተጋድሎ በስንክሳር ሳይጻፍ ፣ በታሪክ ሳይመዘገብ ፣ "ወበዛቲ ዕለት እዕረፈ ብፁዕ ወቅዱስ አባ..." ሳይባልላቸው ቀረ ፤ በቃ ቀረ ።

ጡረታ ሠፈር የመጠጥ ዐይነት ሞልቷል ። ጠላ ፣ ጠጅ ፣ ካቲ ካላ ፣ ሻሚታ ፣ መሪሣ ፣ ሁሉም ለምኖ ባገኛት ሳንቲም ይጠጣል ።

ውበቴ ምክሩ መሬት ጠብ አይልም ። "ኩሊ ከሚበዛበት ጠጅ ቤት መግባት ቅዳሜ ቅዳሜ ነው ። ደግሞ አዲስ ልብስ መልበስና ጫማ ማድረግ የለብህም ። አሮጌ ልብስና አሮጌ ጫማ እንኳ የሌለው ኩሊ ሞልቷል ። ታዲያ በባዶ እግሩ እየሔደ ላንተ የሚመጸውት ይመስልሃል ? አይደለም ። የሚመጸውትህ ከሱ ስታንስ መሆኑን አትዘንጋ ። ባለባበስም ማሳዘን አለብን...

"ቡና ቤት የሆነ እንደሆነ ፣ እግዜር ይስጥህ ቢልም ጭጭ በለውና ቁም ። አንተ ድርቅ ብለህ ስታየው እኔ ስሙህበት ፣ ወሬውን እንዳታቋርጠው ሲፈልግ ፣ ለዐይኑ ስታስጠላው ፣ ሙዚቃው ሆይ ሆይ ሲልበት የግዱን ይሰጠናል ። ብቻ አንተ ማወቅ ያለብህ

የትኛው ጠጅ ቤት ኩሊ እንደሚገባ ፣ የትኛው ጠጅ ቤት መኳንንት እንደሚገባበት ነው ። የትኛው ቤት ስሙኒ እንደምናነኝና የትኛው ቤት ዐሥር ሣንቲም እንደምናነኝ ዕወቅ ። አንተ ጉበዝ ከሆንክ እኛኮ ከጢያሳ ለማኖች አናንስም ።

"ደሞ ለምንድነው የልደታና የጊዮርጊስ ደሞዝተኞችን ለይተህ የማታውቃቸው ? ድንገት አንድ ሚኒስትር በመንገድ ወይም ቡና ቤት ብናገኘውና ሽልንግ ቢሰጠን ጥቅም ነው ። ወይኔ ማየት በቻልኩ ኑሮ እያንጠረጠርኩ እሰያቸው ነበር ።" እኔ እንዴ ሆንኩ እንደዚያ ከሚጋረፍ ዐይን ጋር መፋጠጥ ቀርቶ ሳንቲም ሲዘረጉልን እንኳ መቀበል ያሳፍረኛል ።

"ዘበኛ የሚከለከልበት ቡና ቤት ከሆነ ብቻዬን እገባለሁ። አንተ ስታያቸው ታፍር ይሆናል ። እኔ እንዴ ሆንኩ የሚጠላኝንና የሚገላምጠኝን ፣ በዶግ ዐይን የሚያየኝን ለይቼ ማየት ስለማልችል ልዩነት አያመጣብኝም ። ሌላው ቀርቶ የምበላውን እንጀራ እንኳ አላየውም ። እንዲያው እጅና አፍ አይተጣጡም እንጂ ፣ ለኔ ብር ሃኑም ጨለማውም አንድ ነው ። እንቅፋት ሲመታኝ እንኳ ምን ዐይነት ደም ከእግሬ እንደሚወጣ ዐላውቅም ። አሁን አንተ ፣ ምላስህን አውጥተህ ብታላግጥብኝ ሰው ካልነገረኝ ማወቅ አልችልም" ይላል ውበቴ ።

ለመሆኑ ፣ የላም በረቱን አልቂት እንዳይቀጥል ያደረገው የተማሪዎች ተቃውሞ ምን ዐይነት እንደሆነ ማወቅ ትፈልጋለህ ልንገርህ ። የያኔውን አይደለም ፣ በቅርቡ ያየሁትን ።

ያገርህ የቅኔ ተማሪ ፣ ባላገርን ባስማት እንደሚያስፈራራውና እንደሚያንቀጠቀጠው ፣ ጃንሆይም ተማሪና አስተማሪ ብርክ ያስ ይዟቸዋል ።

የሚገርምህ ያስኳላ ተማሪ ፣ አስማት መድገም አይችልም ። ሽጥጥና ጠመንጃም የለውም ። አልማርም ይልና ትምህርቱን ረግጦ ፣ ደብተሩን ይዞ ፣ እስክርቢቶውን ኪሱ ውስጥ ከቶ ከትም ህርት ቤት ይወጣል ። መንገዶችንም በሰልፍ ያጥለቀልቃቸዋል ። ያንድ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚያሳዩት ስልፍና የሚያስ ሙት መዝሙር እንደ ትንሣኤ ደወል ሩቅ ቦታ ያሉትንም ተማ

ሪዎች ይቀሰቅሳቸዋል ። ፖሊሶች በሚያስለቅስ ጋዝና ባርጩሚ ሲሏቸው ፣ ተማሪዎች ደግሞ ፖሊሶችንና የከተማ አውቶቡሶችን ፣ ያሜሪካ ኤምባሲን በድንጋይ ይደበድባሉ ።

አውቶቡሶች ይሰባበራሉ ። ፖሊሶች የብረት ቆባቸውን እየ መከቱ ያባርራሉ ። የተማሪ አፈሳ ይቀጥላል ። ተሜ ለለማኞች ጥብቅና ስትቆም የዱላ ውርጅብኝና የወህኒ ቤት ራት ሁና ዕርፍ!

መቼም ሰው በራሱ መፍረድ አይፈልግም እንጂ ፣ እንዴ ለማኑ ብዛት መጠላት አይበዛብንም ።

መኳንንቱና ሴት ወይዛዝርቱ የመልካቸው ማማር ፣ የልብ ሳቸው ንጽሕና ፣ የመኖሪያ ቤታቸውና የመኪናቸው ቁንጅና፣ ያንን አይተህ አፈር የመሰለውን የድሆችን ፊትና የለበሱትን ቡትቶ ስታይ ፣ ታንድ አገርና ታንድ ወንዝ የበቀልን ያንድ አገር ሰዎች አንመስልም ። እንዲያው ሙያዬ ብለው ጥላቻቸውን ማባባ ሳቸው በዛ ብዬ ነው እንጂ መጠየፍስ ይጠየፋሉ ። አልፈርድባ ቸውም ። ምን ማለትህ ነው? ፈረንጅ አኮ ሆነዋል ። በመልክ፣ ባለባበስ ፣ ባነጋገር ፣ ባበላል... ሳይቀር ፈረንጅ ሆነዋል ።

በየመንገዱ ፣ በየግንቡ ሥር የወደቀ ድሪቶ ታይና ተሻግረ ኸው ስታልፍ ፣ ወይም ምንድን ነው? ብለህ በእግርህ ገለጥ ስታ ደርገው ፣ አፈር የመሰለ ሰው ብቅ ይላል ። ይህን ይህን ሳይ አል ፈርድባቸውም ። አንተስ?

የድሃው ብዛት ሳይሆን የድህነቱ ዐይነት ፣ ብዛቱ ፣ የበሽተ ኛው ብዛት ሳይሆን ፣ የበሽታው ዐይነት ፣ ብዛቱ ያስጠላል ። በየመ ንገዱ ፣ በየመጠጥ ቤቱ ፣ የትም የትም ቢሆን ፣ ቀንም ሆነ ማታ፣ ሀብታም በሐዲበት ቦታ እንዴ ጥላ መከተል ነው ።

መኪና ውስጥ ከቆንጆ ሴት ጋር ተቀምጠ ሳለ ፣ ''ስለ እግዚ አብሔር!...'' ብሎ ጆሮው ላይ ሲያቃጭልበት የሚያሳየውን ጥላቻ በቃላት መግለጽ ያቅታል ። የዚህን ጊዜ ልመና በሞት አስ ቀጥቷል ብልህና አንተ በሀብታሞች ቦታ ሆነህ ብታየው እንጂ ትህ ይርስ ነበር ። በኛ በለማኞች አንጀት ስታየው ግን ወንጀል ይመስልሃል ።

በዚህ ላይ የሴትኛ አዳሪዎች ፣ ያታላዮች ፣ የሴቦች ፣ ናግጅ ራት መኾዎች ብዛት አይጣልብህ ።

መቀማማት ፣ መሸነጋገል ፣ መገለማመጥ ፣ መስዳደብ ፣ መገ ፈታተር ፣ መተራረድ ፣ መወሻሸም ፣ መተቻቸት ፣ ጉቦ መበላላት ፣ አለመተማመን የከተማው ጠባይ ይመስላል ።

አንዱ ነጥቆ ይበራል ። ሌላው ያባርራል ። አንዱ ጠሙን ይውላል ፤ ሌላው በቁንጣን ይሞታል ። አንዱ መኪና ሰውን እሳ ፍሮ ይሐዳል ። ሌላው መኪና አንዱን መንገደኛ ገጭቶ ያመል ጣል ።

አንዱ የመኪናውን መንገድ እየዘረ ቢጠርግ ይውላል ። ሌላው ቆሻሻ እያመጣ ይደፋል ። አንዱ መንገድ ጸር ልሽና ይላል ፤ ሌላው አላሸናም ይላል ። አንዱ ተሽከሞ ሲንጸባጭ ፣ ሌላው በእግሩ ለመራመድ ተጠይፎ በመኪና ይሐዳል ። ሁሉም ነገር ወይ ሲያንሰው ፣ ወይ ሲትረፈረፍ ነው ።

ይላል ወንድምህ

አውግቶ ተረፈ

እንዳለ ፡ ይህን ዱብዳቤ ከጻፍሁት በኋላ መልሼ ሳነበው እንዳንድ ሐሳቦቼ አይገቡህም ብዬ ተሰማኝ ። ቢሆንም ከሚቀር ብህ ልላክልህና እንበው ። ያልገባህን በዐይነ ሥጋ ስንገናኝ በረ ጅሙ እንጫወተዋለን ። በል ፣ ደህና ሁን ።

የጴጥሮስ ውሳኔ

የአቶ ስምን ቤተሰብ ፣ ማታ ማታ ቴሌቪዥን ከበው እስከ ፕሮግራሙ ፍጻሜ ድረስ ማየት ይወዳሉ ። አቶ ስምን ግን ፣ ቴሌቪዥን የማየት ወይም ሬዲዮ የመስማት ፍላጎት የላቸውም ። ቴሌቪዥን ሲከፈት ፣ ቶሎ ብለው ወደ ማንበቢያ ክፍላቸው ይገባሉ ። ቤተና የሕግ መጻሕፍት ማንላበጥ ይጀምራሉ ። አንዲት ቀን እንኳ ስማቸው ያልተጠራበትን ቴሌቪዥን ለማየት ትዕግሥት የላቸውም ።

አቶ ስምን ፣ ሀብታም ነጋዴ ናቸው ። ሠንጋ ተራ አንድ ትልቅ ሆቴል አላቸው ። ሆቴሉም ከሠላሳ የማያንሱ መኝታ ቤቶች አሉት ። ሁለት የጭነት መኪናዎችም አሏቸው ። አባታቸው ነጋዴ፣ እሳቸውም ነጋዴ ሆነው በመቅረታቸው የሚያዝኑት አቶ ስምን ፣ ልጃቸው ጴጥሮስ የሕግ ትምህርት ተምሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ እንዲሆን አጥብቀው ይመኙ ነበር ።

አቶ ስምን ፣ ላምስቱ ቤቶች ልጆቻቸው የጴጥሮስን ያህል አያስቡላቸውም ። ጴጥሮስ ግን ፣ የሁሉም ታናሽ በመሆኑ ሳይሆን፣ በመልክ ስለሚመስላቸውና ከሁሉም ከሁሉም እሳቸው ተመኝ ተውት ሳይሆንላቸው የቀረውን የዳኝነት ሙያ አግኙት ፣ ስማቸውን እንዲያስጠራቸው ስለሚመኙ ዐይን ዐይኑን ያዩት ነበር ። ለዳኝነት የሚያበቃ ትምህርት አጥተው በንግድ ሥራ ያሳለፉትን ኑሮ ፣ እንደ ኑሮ አይቁጥሩትም ።

'ያለኝ ሀብት ሁሉ ቀርቶብኝ አንድ ተራ ሹም ሆኜ ብኖር እወድ ነበር!' ይሉታል ጴጥሮስን — ለዳኝነት ሥራ አክብሮት እንዲኖረው ለማድረግ ሲሉ ። ጴጥሮስ ግን ያለው በሌለው ፣ ነጋዴው በሹመ መቅናቱ የተለመደ መሆኑን ስለሚያውቅ ፣ ውስጥ ውስጡን የንግድ ሥራን ያደንቃል ። ላይ ላዩን ግን ያባቱን ምክር የተቀበለ በመምሰል ፣ ዳኝነትን የሚያክል ሙያ እንደሌለ አድርጎ ይነግራቸዋል ። ደስ ይሰኛሉ ። በሐሳባቸው ጊዜን ቀድ

መው ይሔዱና ጴጥሮስ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ፣ ወደ ፍርድ ቤቱ አዳራሽ ገብቶ ሲሠየም ሕዝቡ ባክብሮት ተነሥቶ እጅ ሲነሣው ይታያቸዋል። ታዲያ የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዴ ማዘጋጃ ቤት መኻል ከተማ ፣ ጉብ ካለ ቦታ ላይ ባለ መሠራቱ ይቆጫሉ።

ጴጥሮስ ፣ የዩኒቨርስቲውን የነና ፈተና ወድቆ ከዩኒቨርስቲ መባረሩን ሰሙ። የሰሙትንም ባይን አዩ። ባዩትና በሰሙት ነገር ክፉኛ ተቆጡ። በኋላም እጅግ አዘኑ። ያዘኑት ግን ልጃቸው በመባረሩ ብቻም አይደል። ወደ ቤታቸው ለሚመጡ እንግዶች ሁሉ ስለ ዕውቅ ዳኞችና ስለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኝም እንደማያወሩ በመገንዘባቸው ነው። ልጃቸው እንደሳቸው ሁሉ ነጋዴ ሆኖ መቅረቱም ታይቷቸው ነው።

እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ በትምህርት ጎበዝ የነበረው ልጃቸው ዩኒቨርስቲ ከገባ በኋላ ፣ ምን እንዳሰነፈው ሊያውቁ አልቻሉም። በዚህ እዝነውና ተከዘው ሳለ ፣ ልክ በወሩ ሽጉጣቸው ከራስጌአቸው ጠፋ። ስሞኑን ከሰው ተጣልተው ስለ ነበር ፣ ምናልባት ባለቤቴ ደብቃው ይሆን ብለው መጀመሪያ ተጠራጥረው ነበር። ግን ደግሞ በግድ ካልመጡባቸው የማይጣሉ፣ መጋደል ቀርቶ መደባደብን እንኳን የማይቃጣቸው ሰላማዊ ሰው መሆናቸውን ባለቤትዬው ያውቃሉ። ለማንኛቸውም ጠይቆ ማጣራቱ የተሻለ ስለ መሰላቸው ፣ 'ማን ወሰደው?' አሉና ጠየቋቸው። 'አላውቅም' ሲሉ ባጭሩ መለሱላቸው። ሴት ልጆቻቸውን በየተራ ጠየቋቸው። 'እናውቅም' ሆነ መልሳቸው። ጴጥሮስን ቢያስፈልጉ አጡት። ዩኒቨርስቲ ከገባ በኋላ ቤት ማደሩን ትቶት ስለ ነበር አዲስ ነገር አልሆነባቸውም። ቆይተው ግን አጠገባቸው አግኝተውት ባለመጠየቃቸው ደስ አላቸው። ዳኛ ሳይሆን እንደ ዳኛ ይቆጥሩት ስለ ነበርና ፣ 'ዳኛ አይሰርቅም ፣ ዳኛ አያዳላም ፣ ዳኛ ማንንም አይፈራም' እያሉ ይነግሩት ስለ ነበር ፣ አይሰርቅም ብለው አምነዋል። በዚህ እርግጠኛ ናቸው።

ከዚያም የቤት ሠራተኞቻቸውን ኢያስጠሩ አንድ ባንድ መረመሯቸው። ንባብ ቤታቸው ተቀምጠው ፣ የማንበቢያ መነጽራቸውን አድርገው ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከፊታቸው አኑረው

እንዴ ዳኛ መረመሯቸው። አቶ ስሞን ራሳቸውን እንዴ መኪንንት ስለሚቁጥሩ ፣ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ብዙ ሠራተኞች አሏቸው። አልጋ አንጣፊ ፣ እንጀራ ጋጋሪ ፣ ወጥ ቤት ፣ የልጆች ሞግዚት ፣ ተሳላኪ ፣ አሽከር ፣ ዘበኛና አትክልተኛ ሳይቀር ቀጥረዋል። አንድ ባንድ እያስጠሩ ፣

"አንቺ ምንድን ነው ሥራሽ?"

"ወጥ ቤት።"

"ሽጉጥ አይተሻል?"

"ኧረ አላየውም ጌታዬ!"

"ትምያለሽ?" መጽሐፍ ቅዱሱን በጣታቸው እያሳዩ።

"እምላለሁ"

"በይ ውጭ። አንተስ?" እያሉ ተራ በተራ መረመሯቸው።

በኋላ አልጋ አንጣፊዋን አስጠርተው በድጋሚ ይመረምሯት ጀመር። የንባብ ቤታቸውን ከውስጥ ቆልፈው ፣ "ሽጉጤን ማን እንዴ ሰረቀኝ ካልነገርሽኝ አሳስርሻለሁ" ብለው በቁጣ ሲጮሁባት እጅግ ፈሯች። በዚያች ቅጽበት መሬት ተከፍታ ብትውጣት በወደደች።

"እትናነሪም? ከዚህ መኝታ ቤት ከሦስታችን በቀር ማንም አይገባም። ባለቤቴ ሰረቀች እንዳልል የማይመስል ነገር ነው። ዛሬ እውነቴን ካላወጣሽ አንላቀቅም። ተያይዘን እንሔዳለን" አሏት።

"ጴጥሮስ ይሆናል የሰረቀው" አለች አልጋ አንጣፊዋ እየጨነቃትና መናገር እየፈራች።

አቶ ስሞን ፣ በመጀመሪያ ጴጥሮስ ካሽከሮቻቸው አንዱ መስላቸው ነበር። እንዲያ ያለ ስም አንዱም እንደሌለው ሲያውቁ ግን እውነቱ ተገለጠላቸው።

"ጴጥሮስ የኔ ልጅ?!!" ሲሉ ቅዝዝ ብለው ጠየቁት።

"አዎ ፣ ጴጥሮስ የርስዎ ልጅ!"

"ውሽትሽን ነው እንች ቀጣፊ ። ጴጥሮስ ቺ ብር ቢያገኝ እንሥቶ ይሰጠኛል ፣ እንኳን ሊሰርቅ! ለመሆኑ በምን ጠረጠር ቺውት?"

"ዘንድሮ አንድም የቤት ዕቃ አልተረፈውም ። የሚቴን ወርቅም አንድ ባንድ ሽጦታል ።"

"ይሽኔ እንች ትሆኖለሽ ኢያወጣሽ ላንዱ ጎረምላ የምታቀ ብይው ። እሱ ምን ሊያደርግለት ነው የሚሸጠው? ራቡው? ጠማው? ልብሱ አለቀበት? ወይስ...?"

"አልሰሙም እንዴ ጌታዬ? ቁማርና ሴት ለምዷል እየተ ባለ ይወራ የለም እንዴ?"

"ጴጥሮስ ?!"

"እዎ ጴጥሮስ ። 'ጠብቂት ። እንድም ዕቃ ይዞ እንዳይወጣ' ብለው እሚቴ ስላስጠነቀቁን እሱ ሲመጣ ቤቱ ይሸበራል" አለች እየተረጋጋች ።

"ከመቼ ጀምሮ? እንዴት አልሰማሁም?"

"ለጌቶች አትንገሯቸው ከሰሙ ይገድሉታል" ብለው እሚቴ ሁላችንንም አስጠንቅቀውናል ። እኔም በነፍስ ስለ ተያዝኩ፡ ቢጨንቀኝ ተናገርኩ እንጂ አልናገርም ነበር ። የጅ ሰዓታቸውን ከሸጠባቸው ወዲህ እሚቴ ራሳቸውም እያስጠጉትም ። ሚን ደግሞ ስለሚወዱት...ይወዱታል!"

"ውጭ ከዚህ! ዐመጸም!" አሉ አቶ ስሞን በቁጣ ፤ ገረዲቷ እየፈራችና እየተንቀጠቀጠች በሩን ከፈተችው ።

"እንዴት ያስፈራሉ ባካችሁ? ላንድ ሽጉጥ ምን እንዲህ አስቆጣቸው? ተሰርቆ የተሸጠባቸው የሚቴ ጌጥ ቢደመር ዐሥር ሽጉጥ አይገዛም?" ይህን በሆዷ እየተናገረች ወጥታ ሔደች ።

"መንጋ ልክስክስ!" አሉ አቶ ስሞን ወጥታ ከሔደች በኋላ በር በሩን እየዩ ፣ እና አሽከሮቻቸውን በዐይነ ሕሊናቸው እየገላመጡ ።

አቶ ስሞን ፣ ገረዳቸው የነገረቻቸውን እውነት ነው ብለው መቀበል አቃታቸው ። ውሸት ነው ብለው መርሳትም አልሆነላ ቸውም ። ከባለቤታቸው ሲነጋገሩበት እንደሚገባ አስበው ከነ ባብ ቤታቸው ከወጡ በኋላ ሐሳባቸውን ቀይረው ተመለሱ ። ባለቤታቸው የጴጥሮስን መበላሸት ይብቀው በማቆየታቸው ለጊ ዜው አበሳሜቸው ። ዐይናቸውንም ማየት አስጠላቸው ። አቶ ስሞን የጠሉትን ወይም ያበሽቃቸውን ሰው ማየት አይወዱም ። ራሳቸውን ያሳምማቸዋል ። ሕሊናቸውን ያቆስለውዋል ። ያላሰቡትን ያሳስባቸዋል ።

'ለመሆኑ ሌብነት ከጀመረ ስንት ጊዜ ሆናት ይሆን?' ብለው ጠየቁ ። የራሳቸው ድምፅ ባዶው ክፍል ውስጥ ነጥሮ ለራሳቸው ሲሰማቸው ነው ፡ መልስ የሚሰጣቸው ሰው ባጠገባ ቸው እንዳሌለ የተገነዘቡ ።

ከንባብ ቤታቸው በቀስታ ወደ ግድ ቤት ሔዱና ፣ ገረዳቸ ውን ጠርተው ወደ ንባብ ቤታቸው ይዘዋት ገቡ ። ዳኛ መስለው ወንበራቸው ላይ ጉብ አሉና እንደገና ምርመራውን ቀጠሉ ። ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ ሲያስቸግራት ጊዜ እንድትቀመጥ ፈቀ ዱላት ። ከዚያም እንደ እውነተኛ ዳኛ በመስቀለኛ ጥያቄ መፈና ፈኛ አሳጧት ። እውነቴን ጎልጉላ ስትነግራቸው ግን በጣም እድ ርገው ተሰሩ ቆረጡ ። ከዩኒቨርስቲ ከመባረሩ ይልቅ ወደ ሌብነት ማሽቆልቆሉ እርምት የማይደረግለት በሽታ ሆኖ ታያቸው ።

"እና ቤት ውስጥ ማደር ከተወ ወር አልፎታል ነው የም ትይ?" ብለው አፈጠጡባት ፣ የሆነውን እንዳልሆነ ማድረግ ትችል ይመስል ።

"ይህንንም አልሰሙ እንዴ ጌታዬ?"

አነጋገሯን በማበሻቀጥ አናንቀው ሲያበቁ ፣ "ሳትነግሩኝ እንዴት መስማት እችላለሁ?" አሏት በግልምጫ አተያይ እያዩ ዋት ።

"የቡና ቤቱ ታላፊ ብርቅነህ ሊነግሮት መጥቶ ነበር ። እሜቴ እግሩ ላይ ወድቀው ሲለምኑት ጊዜ ፣ 'እኔ ምን ቸገረኝ

ለሚያርሰው ጥሩት እርሶ ተጠያቂ ነዎት' ብሎ እየተነጫነጨ ወጥቶ ሔደ'' አለቻቸው ።

''በቃ ውጭልኝ ። ሁሉንም ነገር ከሱ ጠይቂ እረዳለሁ'' ብለው ከንባብ ቤታቸው ወጡ ። ገረዳቸው እሷን ለማባረር የተከተሏት ይመስል እየተገላመጠች ወደ ማድ ቤት ሔደች ። እላቸውም ኦፔላቸውን አስነሥተው ወደ ቡና ቤታቸው ያቢሯት ጀመር ። ከቦሴ ተነሥተው ሠንጋ ተራ እስኪደርሱ ድረስ ሐሳባቸው የተጠመደው ባለቤታቸው የጴጥሮስን ብልግና በመደበቅ ስላደረሱት ጉዳት በማውጣት በማውረድ ነበር ። እንደ ደረሱ ብርቅነህን አስጠሩት ። ብርቅነህ ከቤት አሽከርነት ተነሥቶ የቡና ቤታቸው ኃላፊ ለመሆን የበቃ ፣ ታማኝ አሽከራቸው ነው ። ይወዱታል ፤ ይተማመኑበታል ።

ብርቅነህ ቁመቱ ረጅም ነው ። አካሉም ግዙፍ ነው ። ጉርድ ሽርጡን ለብሶ እንደ ታላቅ ሥጋ ያፈረጠመ ጡንቻውን እያ ሳየ ፣ ቡና ቤቱ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲል ያየ ሰካራም ደፍሮ አይረብሸም ። ከረበሸም አንገቱን አንቆ ነው ኢያዳፋ የሚያስ ወጣው ። 'የሸርሙጣ አለቃ' ብለው ሊዘብቱበት የሞከሩትንም ምላሰኞች ገበሬ በሚያስመስለው ግዙፍ እጁ ፣ መንገጭላ መንገጭ ላቸውን በቡጢ እያጠመመ ልክ አግብቷቸዋል ። ያቶ ስሞንን ቡና ቤት ያስከበረውም በጉልበቱ ነው ። ከቤት አሽከርነት እውጥተው ወደ ቡና ቤት እንዲዛወር ማድረጋቸውን ሁሌ እንደ ኮሩበት ነው ። በዝውውሩ ብርቅነህ ደስ አልተሰኘም ነበር ። የጴጥሮስን ታላቅ እኅት ልዕልትን ስለሚወዳት ፣ ከሷ መለየቱ ሞት መስሎ ታይቶት ነበር ። ዳግመኛ የሚያያትም አልመሰለው ነበር ። መሳሳቱ የገባው በኋላ ነው ።

አቶ ስሞን ፣ ቀጥታ ወደ ቡና ቤት ገቡና ብርቅነህን እጁን ይዘው እየጎተቱ ወደ ጓዳ ይዘውት ገቡ ። አንዳች ነገር እንደሚነ ግሩት ከመጠርጠር በቀር ፣ የመጡበትን ትክክለኛ ምክንያት ማወቅ አልቻለም ። ዝም ብሎ ተጎተተላቸው ። ከቡና ቤቱ ጀርባ ፣ በረንዳው ላይ ሲደርሱ ቆሙ ። ቆመውም ተፋጠጡት ። ልክ ገረዳቸውን በተፋጠጡበት መልክ ተፋጠጡት ። ካሁን አሁን ይነግሩኛል ብሎ ቢጠብቅ አይነግሩትም ። ጥበቃው በዛበት ።

ፈራቸው ። ዝምታቸውን ፈራው ። አተያየታቸውን ፈራው ። እንደ ጌታ ፣ እንደ አባትም ሆነው ስላሳደጉትና እምነት ስለጣሉ በት በጣም ያከብራቸዋል ። አነሰ በዛ እያሉ እንደ ንብጋባ ነጋዴ ስለማይከራከሩም ያከብራቸዋል ። ዝምታቸውን መቋቋም ሲያቅ ተው ጊዜ መጠየቅ ግድ ሆነበት ።

''ምን ሆኑ ጌታዬ?'' አላቸው ።

አቶ ስሞን እንድም በዝምታ ፣ እንድም በጥያቄ ማፋጠጥ ይወዳሉ ። እንዴ ዝም ካሉ ዝም ነው ። የዝ አልኻቸው ጉሮሯል ቸውን ያፍናቸዋል ። ባይጠይቃቸው ኖሮ እንዲት ቃል እንደማ ይናገሩ የገመቱው ብርቅነህ አንድ ያበሳጫቸው ነገር እንዳለ ጠረጠረ ።

''ምነው ምን ሆኑ ጌታዬ?'' ሲል በድጋሚ ጠየቃቸው ።

''እቤቱ ውስጥ የተፈጠረውን ጉድ ልነግርህ ነው የመጣሁ ። እንተም የምትነግረኝ ነገር አለ'' አሉ አቶ ስሞን ፣ ዝግ አንደበ ታቸው በግድ እየተፈታላቸው ።

''ታዲያ ቀን ብናደርገውስ? ነገ ቀን ።አሁን የመጠጫ ሰዓት ነው ። ቤቴን መቋጣጠር ይኖርብኛል ።እኔ ከሌለው ሠራ ተኞችም አይሠሩ ፤ ረብሸኞችም አይቻሉ ። ቡና ቤቱ ምስቅል ቅሉ ነው የሚወጣ'' አላቸው ፣ በወትሮው ትሕትና ። ለቡና ቤቱ ገበያ እምብዛም ግድ እንዳሌላቸው ቢያውቅም ፣ ብርቅነህ የግቱቡን ከመሥራት ቸቆጥበ አያውቅም ።

''የለም አያድርም ። ዛሬውኑ ጨርሰነው ማደር አለብን ። ይልቅ አንድ ጠርሙስ ውስኪና ሁለት መለኪያ ይዘህ ቁጥር አምስት መኝታ ቤት ድረስ ና ።ምሥጢራችንን ማንም ሰው ማወቅ የለበትም ።''

ብርቅነህ የታዘዘውን ለማምጣት ሲሔድ ሰዓቱን አየ ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሁኗል ። ውስኪውን ቶሎ ይዞ ሔደና በብርጭቆ ቀድቶ ሲሰጣቸው ፣''ተቀመጥና ላንተም ቅዳ'' አሎት ።

''እኔ ቡና ቤቱ ሳይዘጋ እልጠጣም ።ኃላፊነት አለብኝ ። እኔ ከሰከርኩማ ሠራተኞቹ ሁሉ እንሰከር ማለታቸው አይቀ

ርም ። 'ተመልከት ዓላማህን ተከተል አሰታህን' አይደል የሚ
ባል...''

''ትእዛዝ ነውኮ !'' አሉ አቶ ስሞን በቁጣ ። ''የኔን ትእዛዝ
አታከብርም ማለት ነው ?የዛሬ ሽያጭ እልም ብሎ ይጥፋ! ሠራ
ተኞችም ይስከሩ! እኛም እንስከር! ቤቱም ይረበሽ ።ገንዘብ ለኔ
ደስታ ተፈጠረ እንጂ ፣እኔ ለገንዘብ አልተፈጠርኩም ።ግባ ?''

''ጌታዬ መቸስ...'' አለ ብርቅነህ እየፈራቸው ።

''መቸስ አትበለኝ ፣ ከኔ ይበልጥ ለኔ አሳቢ አትሁን ።ያንድ
ቀን ሽያጭ ቢቀርም አይጎዳኝም ። ይልቅ አታስለፍልፈኝ ።ላን
ተም ቅዳና እየጠጣህ የመጣሁበትን ልንገርህ !''

ብርቅነህ ፣አቶ ስሞንን ተከራክሮ ሊያሳምናቸው አልቻለም።
ስለሆነም ፣ትእዛዛቸውን አክብሮ ውስኪውን እየተጎነጨ ፣ የሚነ
ግሩትን እህ ብሎ ለማድመጥ ፣ የሚሰጡት አዲስ ትእዛዝ ካለም
ለመቀበል ወሰነ ። ትንሽ ጠርጥሯቸዋል ፤ ትንሽም ፈር
ቷቸዋል ። ልዕልትን ይጸሩልኝ ብሎ እንዳይጠይቃቸው ፣አሽከር
የጌታውን ልጅ የሚለምን ከመቸ ወዲህ ነው ?''ሊሉት ሆነ ።
ፍቅሩን አምቆ ዝም እንዳይል አልቻለም ።ቀን የሚያመጣውን
አያለሁ በማለት ቀኑን ይጠብቃል ።የሁለቱን መሩቀር ቤተሰብ
ሁሉ አውርቶ እንደ ጨረሰው ያውቃል ። እናትዬው ፣ ''ተይ ይቅ
ርብሽ'' ብለው ሲመክሯት ፣ ሲሰድቧት ሁሉ እንዳልሰማቻቸው
ያውቃል ። አቶ ስሞንም በጭምጭምታ መልክ ተነግሮአቸዋል።
እንዲያውም ሚስታቸው ብርቅነህን ከሥራ አባርረው ብለዋቸ
ቸው ፣''በሥራ ጎበዝ ነው ፤ እንደሱ አሚሆንልኝ አላገኝም''
በማለት ነገሩን ቸል እንዳሉት ሰምቷል ። ልዕልትም እንድ
ሰሞን ብርቅነህ ካልመጣ አልበላም ፣አልጠጣም ብላ እንዳስቸ
ገረችና በስንት ምክር ረጋ እንዳለች ለቤተሰቡ እንግዳ አይደ
ለም ። አሳቸውም ቢሆኑ በእኩልነትና በፍቅር የሚያምኑ ሰው
ናቸው...አስተሳሰባቸው እንደ ዕድሜያቸው ኋላ ቀር አይደለም..
በነጻ ሕሊና ያምናሉ...እና ግራ ሲገባው ጊዜ ልዕልት ''እባክ
ህን አባባ ብርቅነህን እንዳገባው ፍቀድልኝ?'' ብላ ለምናቸው
እሺ አሰኝታቸው ልጃቸውን እንዲያገባ ሊነግሩት የመጡም መሰ
ለው ። 'ድሃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ ፣እክክ በጨረሰው' የሚል

ተረት ትዝ ያለው ዘግይቶ ነው ።ጌታና ሎሌ አንድ ክፍል ውስጥ
ተቀምጠው ውስኪ ተካፍለው ሲጠጡ ፣ የመጀመሪያ ጊዜአቸው
መሆኑም አስገርሞታል ።

''የሽጉጤን መሰረቅ ሰማህ ብርቅነህ ?''

''አልሰማሁም'' አለ ብርቅነህ ። ወዲያው ሐሳቡ ወደ ልዕ
ልት ሔዶ ። ቶሎ የማያገባት ወይም የማይጠልፋት ከሆነ ፣ ራሷን
ለመግደል ዝታ ስለ ነበር ፣ ያባቷን ሽጉጥ ደብቃ ራሷን ለመግ
ደል የምትችልበትን ቀን የምትጠብቅ መሰለው ።

''ለመሆኑ ማን ሰረቀዎት ጌታዬ ?''

''ማን እንደ ሰረቀኝ ባውቅማ ተሰረቅኩ አልልም ነበር ።
የቤቱ ሰዎች ሁሉ አላየንም ብለው ካዱ ። አሷ እንጣፈያችን
ሆኑ ጴጥሮስ የወሰደው ይመስለሃል ?''

ብርቅነህ ፣ የቤት ሠራተኞቻቸውን በደንብ ያውቃቸዋል ።
ከነሱ ውስጥ አንድም የሚጠረጥረው ሰው የለም ። የጴጥሮስ
ጠባይ መበላሸት ግን እሱንም አሳስቦታል ።

''ምነው አመነታህ! ጴጥሮስን አትጠረጥረውም እንዴ ?
ጎረምሳ ነው ። በሱ ዕድሜ ያሉ ወጣቶች ብዙ ምኞት ይፈራረቅ
ባቸዋል ። እንዴት አትጠረጠረውም ?''

''የጴጥሮስ ነገርስ አሳሳቢ ዶረጃ ላይ ደርሷል'' አለ ብር
ቅነህ ።

''ታዲያ ለምን ቶሎ አልነገርከኝም ? እሱን ሰው ለማድ
ረግ የነበረኝን ምኞት ታውቃለህ ። አዶራ ጠብቅልኝ ብዬህም
ነበር ። ለምን አልነገርከኝም ?''

''እሚቴ ናቸው እንቅፋት የሆኑብኝ ። ገና ጨርሶ ሳይበላሽ
ልነግርዎት ነበር ። 'ላባቱ አትንገርበት ። እንደሚወደው ታውቃ
ለህ ። መባለጉን ከሰማ ልጄን አንድ ነገር ያደርግብኛል ። እንድ
ልጄን ብታሳጣኝ ምን ትጠቀማለህ !' ብለው ሲማፀኑኝ ጊዜ

ዝም አልኩ ።እውነትስ አንድ ነገር ቢሆን እሜቴ ሰው ያደር ጉኛል ?''

''ለመሆኑ መማገጥ ከጀመረ ስንት ጊዜ ሆነው ?ስለሱ የምታውቀውን አንድም ሳታስቀር ንገረኝ እስቲ'' አሉ አቶ ስሞን ፥ ትእዛዝም ማግባባትም በተቀላቀለበት ድምፅት ።

''ዩኒቨርስቲ ከገባ ጀምሮ ነው የባሰበት ። ከቤተሰብ ቁጥጥር ሲወጣ ጊዜ ተመቸው ።በፊት ያልነበረው ጠባይም ይታይ በት ጀመረ ።በቀለ ከሚባል ቁማርተኛ ጋር ጓደኝነት ባይገጥም ኖሮ ምንም አይሆንም ነበር'' አለ ብርቅነህ የጌትዮውን ግንባር ለማንበብ እየሞከረ ።

''በቀለ የማን ልጅ ነው ?''

''አባቱን አላውቃቸውም ።እንዲያውም አባት ያለው አይ መስለኝም ።የሕይወት ታሪኩን ተከታትዬ እንዳጠናሁት ከሆነ እናቱ ቡና ቤት አሳት ።እሱም የወጣትነቱን ዘመን በቁማርና በድብድብ ያሳለፈ ነው ። የቁማር ቤታቸውንም ተከታትዬ አይ ቸዋለሁ ። እሜቴ አትንገር ብለው ባይከለክሉኝ ኖሮ ፥ ያኔ እንደ መጣሁ ብነግሮት ኖሮ ፥ ጴጥሮስ ከፈተና አይወድቅም ነበር ።

''እንዴት ተገናኙ ጃል?'' ተመቻቹ በደንብ ለመስማት ።

''በቀለ እዚህ እየመጣ አንድ ሰሞን ከረንቦላ ይጫወት ነበር ። ያኔ ነው የተዋወቁት ። አዎ ፥ በክረምቱ ውስጥ ነው ። ይህን በቀለ የተባለውን ሰይጣን ቢያየትኮ....ሴትና መጠጥ የለመደው ገና በሕፃንነቱ ነው አሉ ። እውን ቢያዩት ግን የሠላሳ ዓመት ሳይሆን የሃምሳ ዓመት ሰው ይመስላል ። አጠር ቀጠን ያለ ነው ። የልጅነት መልኩ በመጠጥና በድብድብ ተበላሽቷል። ፊቱ ላይ ጠባሳው አንዱ ባንዱ ላይ ተጋድሟል ። ጀርባውም በጩቤ ተበሳስቷል ይላሉ ። ደሙ ፈሶ ስላለቀ ሲፈነክት ደም አይወጣውም ። በቀለ ማለት እሱ ነው'' አለ ብርቅነህ ፥ ውስኪውን እኩል እየተጐነጨ ።

''ይህስ የሰው ተፈጥሮ አለው ለማለት አያስደፍርም ?'' አቶ ስሞን ፥ ሲፈነክት ደም የማይወጣው ሰው በሐሳባቸው ለመ

ግል እየሞከሩ ፤ ከዚያም ''ሲፈነክቱት ደም የማይወጣው ምን ዐይነት ሰው ነው ፥ አይገርምህም?'' አሉ ።

''እኔስ ብልግናውን ስላየሁ አይገርመኝም ። ይልቅ የሚያስ ገርመኝ እስካሁን አለ መሞቱ ነው ። ለሱ ሞት የማይሳልለት አንድም ሰው አይገኝ ። ብቻ ...እዚህ ቤት ውስጥ የማይሳልለት እሱ...ለመሆኑ የሚሠሩትን የብልግና ተግባር አልሰሙም?''

''አልሰማሁም — ማን ነግሮኝ!'' አሉ አቶ ስሞን ብርቅ ነህን እያተኮሩ ።

''ኧረ እንዲህ አይምሰልዎት ጌታዬ'' አለ ብርቅነህ ፥ ''ኮረንቦላ ቤት ረብሻ እያነሡ አስቸግረዋል ። በቀለ ነው ነገር ቆስቋሽ ። በጣም ትቢተኛ ስለሆነ ከማንም ጋር ይደባደ ባል ። የርስዎ ልጅ ታዲያ ካንዱም ሁለቴ በማያውቀው ነገር አማሾለት ጠቡን በቦክስ አብሮ ተሳትፏል ። ሰዎች ሁሉ ሞቱን ለሚሳሉለት አንድ ትቢተኛ ዱርዬ ፥ እሱ አጋዥ በመሆኑ ያልተ ገረመ የለም ። የስዎ ልጅ በመሆኑ ታፈረ እንጂ....''

''ጴጥሮስ ተደባዳቢ ነው የምትለኝ? ምነው ተው አትሉ ትም?''

''መቸ ይሰማናል ብለው ነው!...እኔማ ያን ወስላታ እንገ ቱን እንቁ ላሶጣው ባልኩ ቁጥር ፥ 'ምን አገባህ?' እያለ ይከለክ ለኛል ።''

''ታዲያ ዝም አልከው እንተ?'' አሉ በተሰበረ ድምፅ ።

''ለርስዎ እስከምነግር...መቸስ ምን አደርጋለሁ... ልጅዎ እስከሆነ ድረስ ለጊዜው እሺ ብዬ ትእዛዙን ተቀበልኩ'' አለ ብርቅነህ ። ቀጠል አደረገና ፥ ''ኧረ ይቺ ሲጋርዎት በሐሰት መስክሮ ተከራክሮለታል'' አላቸው ።

''ፍርድ ቤት ሔዶ?'' አሉ አቶ ስሞን ፥ የጎደለውን ዊስኪ ቶሎ ሞላ አድርገው በጎይል ተጎነጩና ።

ብርቅነህም ብርጭቆውን ቶሎ ጨለጠና ሌላ ቀዳ ። ቀድቶ እስኪጨርስና ወደ ጨዋታው እስኪመለስ አላስቻላቸውም ።

ገና ውስኪዉን ሙሉ ካልጨረሰ ፣ ከጉሮሮእቸው ተቆራርጠው በሚወጡ ቃላት በጥያቄ ያጣድፉት ጀመር ።

"ለመሆኑ የትኛው ፍርድ ... ቤት ነው? ... አውራጃዉ ? ወይስ ከፍተኛዉ?" አሉት ፍጥጥ ብለው እያዩት ።

"ፍርድ ቤትስ አልደረሱም ። ጉዳዩ በኛው መሥሪያ ቤት ነው ያለቀው ።" ብርቅነህ ሳይታወቀው ያስደነገጣቸውን ያህል ሳያውቀው አረጋጋቸው ።

"መሥሪያ ቤት...ስትል...የት ማለትህ ነው?"

"አይ ጌቶች!...እዚሁ ነዋ...ቡና ቤታችን..."

"አሃ! አሁን ገባኝ...እዚሁ ታረቀ ማለት ነው ። ያ ማነው ስሙ... በቀለ... ጥሩ... ታዲያ ጴጥሮስም እዚሁ ነው የመሰከረው አትለኝም! ስመሆኑ ጨዋ ጨዋ ሰዎች ነበሩ በዚያን ሰዓት? ...ጴጥሮስ አጉል ምስክር ሲሆን...?"

"እንዴት ጨዋ ሰዎች?"

"ትልልቅ የከተማ ሰዎች ማለቴ ነዋ!... እነቀኛዝማች መላኩ...እነ ሐጅ ዑመር...ደሞ እኒያ የአውራጃው ፍርድ ቤት ዳኛ አቶ ስንቄ...እነሱ እነሱ ነበሩ ወይ...ምነው አንተ ደሞ ፣ ታውታቸው የለም የኔን ጓደኞች?..."

"መቸ አጣሁ እነሱንማ...ግን ከነሱ ማንም አልነበረም ። እኔና ገንዘብ ተቀባይዋ ብቻ ነበርን ለጊዜው ። ከረንቡላ የሚያጫውተውን ልጅ አይቁጠሩት ። ቢናርም እሱ ከምንም አይገባም ። ሁለቱ ሴቶች ቡና ማፍያው ጋ ነበሩ ፣ ምንም አልሰሙም ። እሪ የያንለታው ቀላል ነው ። ሌላ ብዙ አለ እንጂ ።"

አቶ ስሞን ፣ በዚህ እፎይ ቢሉም የጴጥሮስ ጥፋት ብዙ እንዳይሆንባቸው ሌላውን ለመስማት ያላቸው ጉጉት አልተቀነሰባቸውም ።

"ሌላ ደሞ ምን አለ?" አሉት ቶሎ ብለው ።

ገና "ጴጥሮስ የዋህ ነው እባክዎን...ምንም ተንኰል አያውቅም" ከማለቱ ፣ "አይዞህ...አንድም ሳታስቀር ንገረኝ... ውቅም" ከማለቱ ፣ "አይዞህ...አንድም ሳታስቀር ንገረኝ... ውስኪውንም ታዲያ እየጠጣህ...በየዋህነት ደሞ ምን አደረገ?" አሉት በስሜት ፣ ስለ ተቻኮሉ ፣ ብርጭቆውን እየሞሉለት ።

"ለቡና ቤቱ አሻሻጮች ስቀጥር በሥራዬ ጣልቃ የመግባቱ ጉዳይ ነው ፣ ይሽኛው እንኳን ።"

"ይሽኛው የቱ? ጣልቃስ እንዴት ይገባል?"

"እንግዲህ እኔ የደሞዛቸውን አካኋን ለመቁረጥ በል ፣ ብዙ ጥያቄ እጠይቃቸዋለሁ ..."

"ሴቶቹን?"

"አዎ ሴቶቹን" ብሎ ገና ሲጀምር የመገረም ሣቅ ከት አሉ ሣቁና ፣ "ደሞ እነሱን ምን አርጉ ሊል ይሆን? አዩ ፈጣሪዬ.. ጀሮ ለባለቤቱ ባዳ ኮ ነው" አሉና አጻረጡት ።

ብርቅነህ አንገቱን ሰበር አርጎ ቀጠለ ፤ "'የት ሠርተሽ ነበር? ስንት ነበር ደሞዝሽ?' ብዬ ስጠይቅ ፣ 'ምን ያደርጋል ይሽ ውሉ ጥያቄ...ሌላ ስንት የሚጠየቅ ሞልቶ...' ይለኛል!"

"እስቲ አንተ ጠይቅ አትለውም ነበር?" አሉ አቶ ስሞን ፣ ጥፋቱ በዚህ እሚያበቃ መስላቸው ትንሽ ፋታ እንዳገኙ ሁሉ።

"እነሱው ፊት ነው እኮ እንደዚህ እሚለኝ! እኔ ደሞ እንዲህ ካለኝ ያችን ሴትዮ ብሞትም አልቀጥራትም..."

"ለምን?"

"ትንቀኛለቻ... በኋላ እሺ ብላ አትታዘዘኛም..."

አቶ ስሞን ፣ ገም ብለው በቦዘ ዐይናቸው ውጭ ውጭውን በመስኩት ያዩ ጀመር ። 'ምነው ኃጢአቱ በዚሁ በተደመደመ' የሚሉ ይመስላሉ — በሆዳቸው ። ብርቅነህ ግን ይሽን ሲያጤን ላቸው አልቻለም ።

"በቀለ ነው ለዚህ ልጅ መዘዙ ...ይሽን ያወቅኩት ዛሬ አይደለም" አላቸው ።

"ምን እንድና ሁለት አለው እሱማ" አሉ ፣ ከሐሳባቸው እንደነቁ ዐይነት ፣ ድምፃቸውን ከፍ አርገው ። "ደሞ እኮ እሚገርመኝ ለሱ ጠበቃ መሆኑ..." አሉና በረጅሙ ተነፈሱ ።

"ባለፈው እሑድ የሆነውንስ አልሰሙም ጌታዬ?" አለ ብርቅነህ ድንገት ነቃ እንዳለ ዘበኛ ወንበሩ ላይ አቀማመጡን እያስተካከለ ። "እዚሁ እኛው ቡና ቤት ረብሻ መካሔዱን?"...

"ምን ይሆን ደሞ አሱ?" — ተመቻቹ ለመስማት ፣ ከውስኪው አንድ ጉንጭ ወርወር አድርገው ።

"ተወራራጁ በቀለ ነው ፤ አይዞህ አሚለው ጴጥሮስ!"

"ውርርዱ ምን ነበር ?"

"አንድ 'ጠርሙስ አረቄ በማግሽ ሰዓት ውስጥ እጨርሳ ለሁ' ብሎ ከአንድ ሰውዬ ጋር በሃምሳ ብር ሊወራረድ ሲል፣ ፀሐይ ሰውዬውን ፥ 'ይቅርብህ ትረታለህ ፤ እሱ እንደሆን ጠጥቶ በሆነ ዘዴ ወዲያው መልሶ ያስወጣዋል ' ብላ መከረችው ። በዚህ ጠብ ተነሣ !"

"ፀሐይ ደሞ ማናት?"

"ቡና ቤት የምትሠራ ነች ፤ እኛው ቡና ቤት ።"

"ታዲያ ዝም አልካቸው አንተ?"

"ምን ዝም እላለሁ... በቀለን አንገቱን አንቂ ላስወጣው ስል ጴጥሮስ ተወው አለኝ ።"

"ምስክር ሆነ በለኛ እንዴ ለመደው!..."

"ምን ምስክር ይሆናል...ተው እንዳንል ሁላችንንም አፍ አፋችንን አለን እንጂ! በቀለንም 'በገንዘቡ እንዴ ፈለገው ይውን' አለ ፤ ፀይሐንም 'በሁለቱ መኻል አትግቢ' አለና አስጠነቀቃት — ነገሩ ሲካረር በቀለ ፀሐይን ክፉኛ ደበደባት ፤ እሷም በጠርሙስ ፈንክታው ጠፋች..."

"ወይ ጴጥሮስ! ጴጥሮስ እንዲህ ተበላሽቷላ!" አሉ አቶ ስሞን ፣ በረጅሙ ተንፍሰው ።

ብርቅነህ ሲተክዙ ሲያያቸው አዘነላቸው ። 'ለምን ይሽን ሁሉ ነገርኳቸው' አለ በሆዱ ፣ እንደ መፀፀት ቃትቶ ። ወዲያው አቀረቀረና ወደ ልዕልት የሐሳብ ጉዞውን ሲጀምር ፣ ጠረጴዛውን በቡጢ መቱና አባነኑት ።

"ስማ ብርቅነህ" አሉ ፣ በቀሉት ዐይኖቻቸው ከላይ እስከ ታች ደጋግመው እየቃኙ ። "አንድ ነገር ግድረግ አለብን — መፍትሔ ፈልግ — እኔም እፈልጋለሁ ። ከዚህ ዐይነቱ ሰይጣን ንንት ነው ይሽ በቀለ? ደግሞ ለሱ ብልግና ጴጥሮስን ተባባሪ ማግኘቱ!" እያከታተሉ ተገረሙ ።

"በቀለ የሀብታም ልጆችን ገንዘብ ስረቁ እያለ ሲቀማና ቁማር ሲጫወት ነው እሚውለው..." ብርቅነህ ሰራሱ ያህል አልጎመጎመ ።

"ታይልኛለህ ፥" እንዴ ዐይኔ ብሌን የምጠብቀውን ልጄን ውሃ ሲያስበላብኝ፣ እኔ ያልታደልኩትን ክብር፣ በሱ በኩል እየተጐነጨ ብርቅነህን በመግፎን እይታ አየት ። አይተውት ሲያበቁ ፥ "አየህ ብርቅነህ? አንተም የወለድከህ ልጄ ማለት ነህ ። በሙያህና በታማኝነትህ ስለ ወደድኩህ ከፍ ከፍ አድርጌሃለሁ ። ወደፊትም ልታገኘው የሚገባህን አልነፍግህም ። ልጄና እሱ እንዲለያዩ ብታደርግ ውለታህን በእጥፍ እከፍልሃለሁ" ብለው ተማፀኑት ።

"ለምን አንድ ነገር አያስደርጉትም?" አላቸው ብርቅነህ ፣ ትንሽ ሲያስብ ቆየና ።

"'አንድ ነገር' ምን?"

"ለምን .... ለምን .... መቸም እሱ የጎበረተስብ ነቀርሳ ነው ። በበሽታው እየተመረዘ ብዙ ሰዎች ከመጥፋታቸው በፊት

እሱ መጥፋት አለበት ። የርስዎን ልጅ ብቻ ሳይሆን የብዙ ወጣቶችን ሕይወት ያድናሉ ። ብዙ ሰው ለማዳን ከሆነ አንድ ሰው ቢሞት ምንም አይደለም ። ያውም በሳንባ ነቀርሳ የተለከፈ'' !!

''ይህን ያህል ከጠላኸው ለምን አንተ አትገድለውም? መቸም እሱ ደም አይወጣውም ብለሃል ። ግደልልኝ'' አሉት ዐይኖቻቸው በደስታ እያበሩ ።

''ብገድልልዎት ምን ያደርጉልኛል?''

''የጠየከኝን እሰጥሃለሁ !!!''

ብርቅነህ ዝም አለና መሬት መሬቱን እያየ ለደቂቃ ሲያስብ ቆየ ። ምን እንደሚጠይቃቸው ማወቁ አላስቸገረውም ። እንቢ እንደማይሉትም ልቡ ነግሮታል ። ሆኖም ከአፉ እንዴት እንደሚያወጣው ከራሱ ጋር ትንሽ የልቡን ፍርጥ አድርጎ ጠየቃቸው ።

''ልዕልትን ይዳሩልኝ ብልዎ ይድሩልኛል?'' አላቸው ፣ ያሉኝን ይበሉኝ በሚል ስሜት ራሱን እያበረታታ ።

''አምስቱም ሴቶች ናቸው ። እንዳቸውም ዳኛ ሊሆኑልኝ አይችሉም ። ምን ያደርጉልኛል? ጴጥሮስ ግን ባይወሳልት ኖሮ የሕግ ትምህርቱን ሲጨርስ ትልቅ ሰው ይሆን ነበር ። አሁንም ቢሆን ተስፋ አለው ። በቀለ ከምትለው ነቀርሳ ከተለያየ እንደገና ትምህርቱን መቀጠል ይችላል ።'' አቶ ስሞን ይኸን እንደ ተና ገሩ ለአንዳፍታ ዝም አሉ ። ዝምታቸው ግን ለአባትነት ወግ ሲባል ሳይታሰብ የመጣ ነበር ።

''እውነት ልዕልትን ይድሩልኛል?'' የብርቅነህ ዐይኖች በደስታ ተንከባለሉ ።

''ልንገርህ ? እንዲያውም ሠርጋችሁን የምደግሰው እኔ ቤት ነው ። ሁለታችሁም ከኔ ቤት ነው ተሞሽራችሁ የምትወጡ ። ግን ደግሞ ተመልሳችሁ የምትገቡም እኔ ቤት ነው ። ገባህ ? ከእንግዲህ አንተ የቤተሰቤ አካል ነህ !''

'ኦ ልዕልት!' በስስ የጧት ቀሚስ በፊቱ ተመላለሰችበት ። በጉርድ ቀሚስ በሰዓት ከትምህርት ቤት ስትመለስ ታየችው ፣ ሣቅ ያፈገገው የመሰለው ፊቷ ዘና ብሎ ዐይኖቿ ተሸፍነው ስታንቀላፋ ታየችው ። እንደ ጥላዋ ከሷ ሳይለይ ጧት ማታ እያየ የሚጎመዥላት ትዝ አለው ፣ በዐይነ ሕሊናው መጣችበት ።

''እሺ በሉ ፣ ቃልዎን ይስጡኝ !''

''እጅህን አምጣ'' መዳፉን ገልብጦ ሲያቀርብላቸው ፣ በቀኝ እጃቸው መተውት ሲያበቁ ፣ ''ቃሌ ቃል ነው ፣ ብክድህ የቁልቢው ይክዳኝ'' አሉት በአስተማማኝ እንደበታቸው ።

ብርቅነህ ሁለመናው በደስታ ፈካ ። ብዙ ወጣቶችን ያስ ለቀሰ አንድ ወሮበላ ገድሎ ልዕልትን የመሰለች ቀይ ዕንቁ ማግባት ምንም ነውር እንደሌለበት ተሰማው ። እንደ ጧት ጮራ መላ ሰውነትን የምታሞቅ ዕንቁ ።

''እንግዲያው ይነሡ ጌታዬ ። አሁኑኑ ቁማር ወደሚጫወቱ በት ቤት እወስድዎታለሁ ። ቀንም—ማታም—ወጣ—ገባ ሲሉ እሚገኙ እንዲት አነስተኛ መጠጥ ቤት ጓዳ ውስጥ ተቀብረው ነው ። እዚያው እንዳቀረቀሩ ነው እጃቸውን የምንይዛቸው !''

አቶ ስሞንና ብርቅነህ ፊትና ኋላ ሆነው ከቁጥር አምስት መኝታ ቤት በጤና ቆማ ወደምትጠብቃቸው ኦፔል መኪና አመሩ ። እንደገና ጎን ለጎን ተቀመጡ ። አቶ ስሞን የመኪናቸ ውን ሞተር አስነሡና ፣ ''ወዴት ብዬ ልንዳ?'' ብለው ጠየቁት ።

''ወደ ፒያሳ ይንዱ እና የንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ አጠገብ መኪናዎን ያቆሙና ፣ ወደ ታች ወደ ሠራተኛ ሠፈር በእግር እንሔዳለን ። ከፈለጉ አብረውኝ ይመጣሉ ። ካልፈለጉም መኪናዎ ውስጥ ተቀምጠው ይጠብቁኛል'' አለ ብርቅነህ ፣ እተባለው ቦታ የደረሱ ይመስል አቅጣጫውን በጣቱ እየጠቆመ ።

''አብሬህ ሔጄ ጉዱን አየዋለሁ'' አሉ አቶ ስሞን ። ብር ቅነህ ግን የትኛውን ጉድ ማለታቸውን እንደሆነ አልገባውም

ወይም የሠፈሩን ወይም የልጃቸውን ጉድ ይሆናል ብሎ አሰበ። ከዚያም ፥

"ቤቱ እስከዚህም የታወቀ አይደለም ፥ የሴት ቤት ነው ። ሴትዮዋ ከቁማርተኞችና ከሌቦች በምታገኘው ገቢ ነው የምትተዳደር እንጂ በመጠጥ ንግድ ብቻ አይደለም ።" በቀጭኑ የእግር መንገድ ቁልቁል ወረዱ ። መጀመሪያ ወደ ግራ ታጠፉ ። ቀጥሎ ወደ ቀኝ ። ከዚያም አግድም ጥቂት እንዱ ሔዱ እንዲት ሱቅ በር ላይ ደረሱ ።

"ጌታዬ እስዎ እዚህ ይጠብቁኝ ። እኔ ልሒድና አባትህ ይጠሩሃል ብዬ ጴጥሮስን ልጥራው ። ውለታችንም ተያይዘን ከገባን ሊደነግጡ ይችላሉ ። እና ጴጥሮስን እጅዎ ካገቡ በኋላ ፥ ወደ ቡና ቤት ይሔዱና ሒሳቡን ተረክበው ለጊዜው እንዲን ኃላፊ አድርገው ይመድቡ ። እኔ ያንን በቀለ የሚሉትን ወሮበላ ከገባበት ገብቼ ያባቴን ቀን ሳልሰጠው አላድርም" ብሎ ዛት ። አባቱ በሕይወተ ሥጋ ይኑር ወይም ይሙት ብርቅነህ የሚያውቀው ነገር የለም ። ለራሱም ሲምል 'ያባቴን ቀን ይስጠኝ' ማለቱ ይቀናዋል ።

"እንዴ! ገና መኖራቸውን እንኳ ሳናረጋግጥ?"

"ለመኖራቸው እርግጠኛ ነኝ ። እርግጠኛ ባልሆን ኖሮ እርስዎን እዚህ ድረስ አለፋዎት ኖሯል ጌታዬ?" አላቸውና ከሱቁ ፊት ለፊት በቀይና በቢጫ መብራት ደብዘዝ ብላ ወደ ምትታይ መጠጥ ቤት ገባ ።

አቶ ስሞን ፥ አካባቢው በጨለማ የተዋጠ በመሆኑ ቀፈፋቸው ። ከመጋረጃ ውስጥ ብቅ ብቅ ያሉት ቀያይ አምፑሎች ደብዛዛ ምስል ከማሳየት አልፈው እውነተኛውን የሰው መልክ ማሳየት አይችሉም ። አቶ ስሞን ከዚያች መጠጥ ቤት የሚወጡትን ሰዎች አትኩረው ሲመለከቱ ፥ ብርቅነህ በጓሮ በር አድርጎ በቀር ቆሮው አጥር በኩል ከጴጥሮስ ጋር ከች አለ ።

"ያ ሰይጣንስ አለ?" ብለው በችኮላ ጠየቁት ፥ ጴጥሮስን እጅ ካገቡ በኋላ ።

"አለ ፤ ትጠራለህ ብዬ ጴጥሮስን ይዤ ስወጣ በዐይኑ ሊበላኝ ደረሰ ። እንመለሳለን ብየው ነው የመጣሁ ። ይሒዱ ። እንደ ነገርኩዎት የቡና ቤቱን ሒሳብ መረከብ አይርሱ ። የት ሔዶ ብለው ወራቱኞች እኔን ቢጠይቁዎት ፥ ልኪው ሔዷል ብለው ይንገሯቸው ።" ከዚያም ወደ ጆሮአቸው ጠጋ ብሎ፥ "ዛሬ የትም አያመልጠኝ" አላቸው ።

አቶ ስሞን ፥ የጴጥሮስን እጅ ይዘው ፥ እንደ ሕፃንነቱ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ሲወስዱት ፥ የመኪና መንገድ ሲያሻግሩት ያደርጉት እንደ ነበረው እየነቱቱ ሲወስዱት ፥ ጴጥሮስ ጎርምሻ ሰው ብሎ ሊነጥቃቸው አልሞከረም ። ቁማርተኞነቱን አባቱ ስለ ነቁበት ደንግጦአል ። መታጠፊያው ድረስ ባይኑ ሸኝቷቸው ሲያበቃ ፥ ብርቅነህ ወደ ትንሿ መጠጥ ቤት በጓዳ በኩል ገባ ።

ጓዳው በሲጋራ ጢስ ታፍኗል ። ከቧን ጠረጴዛ ከበው የቁማሩት ቁማርተኞች በሚመድቡት ገንዘብ ልክ ምኞትና ሥጋታቸው የበዛ ሆኗል ። ላብ በላብ ሆነዋል ። ብርቅነህ ፥ በቀለ አጠገብ ሔዶ ተቀመጠ ። በግማሽ የዕድሜ ዘመኑ የፊት ጥርሶቹን ያጣው ወሮበላ አፉን ሳይከፍት በዐይኖቹ ፈገግታ ተቀበለው ፥ ጴጥሮስ ተመልሶ የሚመጣ መስሎት ።

ብርቅነህ ፥ ለሌላ ጉዳይ የገባ መስሏቸው እንዳይጠረጥሩት ከያዘው የቡና ቤት ሒሳብ ውስጥ እያከታተለ መደበ ። ሳይ ቀናው አምሽቶ የነበረው በቀለ ፥ በብርቅነህ ላይ እየተጠቃቀሰ ይመድባል ። ብርቅነህም ያላየ እየመሰለ ባሥር ሲሉት በቫያ ብር ይመድባል ። በቀለ ደስ አለው ። እከታትሉ እንዲመድብም ገፋ ፋው ።

"አይዞህ ብርቅነህ ። ቁማር መጀመሪያ ላይ አስበልቶ ነው በኋላ መብላት የሚቻለው ፥ አትፍራ" አለው ።

"ግድየለም ፥ የኋላ ኋላ ይቀናኛ ይሆናል" አለ ብርቅነህ ቁማር ለመብላት የጎመጀ በመምሰል እስኪያንሸዋሽው ድረስ ተቀምጦ አመሸ ።

በቀለ መቶ ብር ያህል ከብርቅነህ ፥ ሴላ መቶ ብር ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ከበላ በኋላ ፥ 'ሽንቴን ልሸና' ብሎ ተነሣ ።

ትንሽ ገንዘብ ሲበላ ብዙ እንደሚመስለውና ያችኑ የበላትን ይዞ መፈርጠጥ እንደሚወድ ስለሚያውቅ ፣ ብርቅነህም ተከታትሎት ወጣ ። የቆርቆሮውን አጥር እንደ ወጡ ፣ "ገንዘቤን በልተህ ወዴት ነው የምትሔድ? እ? ባይሆን አንድ ሁለቴ መድብልኝ እንጂ" ብሎ ጠየቀው ብርቅነህ ።

"ምን ያህል ገንዘብ ተበላህና ነው መድብልኝ የምትለኝ" ሲል የመልስ ፍጥጫ አፈጠጠበት በቀለ ፣ ወደ ጨለማው እያፈገገ ።

"የተበላሁትን መቶ ብር ትንሽ ማድረግህ ነው?"

"ላንድ የሸርሙጣ አለቃ ብዙ ሳይሆን ይቀራል? እኔ ባንድ ምሽት አምስት መቶ ብር አስበልቼ እንኳ መድቡልኝ አልልም" አለ ደፋሩ በቀለ ፣ ካሞቲ ሳይሆን ከሕፃን ልጅ ጋር የተፋጠጠ ነው የመሰለው ።

"ማን ነው ፣ 'የሸርሙጣ አለቃ' አንተ ?!" ብርቅነህ ዘሎ በጥፊ አቀመሰው ።

"ይችን ይወዳል!" አለና በቀለ ፈንጠር አለ ። ከዚያም ከኪሱ የማይለያትን ሴንጢ አውጥቶ ወደ ብርቅነህ ሲንደረደር ፣ እንዳች የሚያክል የጫማ ጥፊ ፊቱ ላይ ተመረገበት ። ተንገዳ ገደና ሲወድቅ ብርቅነህ እንደ ጆፌ አሞራ እላዩ ላይ ገብ አለና ሰንጢውን ለመቀማት እጁን ጠመዘዘው ። ከፊት ለፊት የሚገኙ ሁለት የሴትኛ አዳሪ ቤቶች ተዘጉ ፣ ከጠበኞቹ አንዱ ቢሞት በኋላ ምስክርነት እንዳይጠሩ ። በዚያች ቀጭን የጨለማ መንገድ ይመጡ የነበሩ ሁለት ሰዎችም ወደ ኋላቸው ተመለሱ ። በቀለ ብዙም አልታገለው ። ድፍረት እንጂ ጉልበት ስለሌለው ከሥር ሆኖ ፣ "እናት... አንተ ፋራ! የተነሣሁ እንደሁ አልምርህም" እያለ እየለፈለፈ ሰንጢውን አስቀማ ። በገዛ ሰንጢው ልቡ ላይ ተወግቶ ጸጥ እስኪል ድረስ የብልግና ስድቡን አላቋረጠም ነበር ። ብርቅነህ ሰቅሰቆ ከወጋው በኋላ ፣ የጨቢውን እጀታ እስከ መጨረሻው ድረስ ወደ ውስጥ አምቆት ተነሥቶ ፈትለክ አለ ።

በየት በኩል አድርጎ እሪ በከንቱ እንደ ደረሰ ለራሱም አልገባው ። ካቢራው የግር መንገድ ዳር ፣ ዛፉ ጥላ ሥር እንዲት

ሴት እያቃሰተች ስትጮህ የሰማ መሰለው ፣ ቀስ ብሎ ርምጃውን ሳያሰማ ተጠጋት ። የሰው ቁመት እሚውጥ ሰፊ የቁቦ ጉድጓድ ውስጥ ናት ። ትቷት እንዳይሔድ አሳዘነችው ። ደግሞም የሚያ ሴት ድምፅ መሰለው ።

"ምን ስትይ እሱ ውስጥ ገባሽ!" አላት ፣ ተንጠራርቶ ።

"እባክህ መጀመሪያ አውጣኝ ። እግሬን ወለም ስላለኝ መቆም አልቻልኩም" አለችው ።

እጅዋን ይዞ እየጎተተ ካወጣት በኋላ አቧራው ላይ ተቀመጠች። እንሒድ ፣ እዚያ ብርሃን ስላለ ወለምታ ወይም ስብራት መሆኑን እናያለን" አላት ።

"በደንብ ካልደገፍከኝ አልችልም" አለችው ። ይሽን ስት ለው የሚያውቀው ድምፅ ለመሆኑ ርግጠኛ ሆነ ።

እጅዋን ትከሻው ላይ አደረገችለትና እየዶገፈ ወሰዳት ። ባይዶርስላትና ባያወጣት ኖሮ እዚያው ታድር እንደነበር እያነ ሣሣች አመሰገነችው ።

"ምን ስታዶርጊ ነባሽ!" ሲል ጠየቃት ።

"አንድ ሰው እቤቱ ሊያሳድረኝ ባምስት ብር ተስማምተን መንገድ ከጀመርን በኋላ ፣ በዚህ በኩል ነው ቤቱ ብሎ ወደ ጨለማው ወሰደኝ ። በዚያም አነቀኝ ። 'አምስት ብር ስጠኝ' አልኩት ። 'ብስብስ ሽርሙጣ — ላንች የሚገባሽ ይህ ነው' ብሎ በጥፊ መታኝ ። አነቅኩትና ሰንታግል ቁቦ ውስጥ ከቶኝ ሔደ" አለችው ።

"ፀሐይ እዚህ አገር አለሽ እንዴ!" ብሎ ጠየቃት ። የድ ፍረት ሥራዋ እያስገረመው ። የበቀለን መሞት ሊነግራት ፈልጉ መልሶ ተወው ።

"በይ እንግዲህ እኔ መሔዴ ነው ። የሚያስቸኩል ጉዳይ አለብኝ" አላት ቀጠለና ። ከዚያም ርምጃዉን ፈጠን ፈጠን እድርጎ ወደ አራት ኪሎ አመራ ። እሱዋም ማንነቱን በማወጹ ብዙ አልተቸገረችም ።

ያራት ኪሎ ቡና ቤቶች አብዛኛዎቹ ተዘግተዋል ። ትልቁ ሰዓት የሌሊቱን መገባደድ ለማብሠር ሙዚቃ-ቀመስ ደወሉን አስተጋባ ። ብርቅነህ ከሱካንዳ ቤቶች በታች አንድ ቢት አገኘና የቀረችዋን ሩብ ሌሊት ካንዲት ቤት ጋር አሳለፈ ።

በጧት ተነሥቶ በታክሲ ተሳፍሮ ወደ ሠንጋ ተራ ሒደ ። ቡና ቤቱ ያለሱ አድሮ የሚገኝ አይመስለው ስለ ነበር ፥ ሲያየው ደስ አለው ። ተረኛ ሴቶችን አስነሥቶ ቡና ቤቱን እንዲወልውሉ ከነገራቸው በኋላ በረንዳ ላይ ተቀምጦ ያስብ ጀመረ ። ማታ የሠራው ወንጀል የውስጥ ሠላሙን ነሣው ። ብዙ ስለ ራሱ ባሰበ ቁጥር ራሱ እያስጠላው ሒደ ። ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት የነበረው ወኔው እንደ ጧት ጤዛ እልም ብሎ ጠፋ ። ለብዙ ዓመታት ሲመኛት የነበረችቱን ልዕልትን አግብቶ የመኖር ምኞቱ እንደገና አገረሸበት ። ግን ደግሞ እቢን የማግኘቱ ነገር እንደ ሕልም ትውስታ በቀጭን ክር ተያይዞ ታየው ። 'ወንጀሉን ሳልፈጽም ፥ እቢንም ሳላገባ እንደ ድሮው ባሽከርነት ብኖር ይሻለኝ ነበር' ብሎ አሰበ። ወዲያው ደግሞ ልዕልት ፍርሃቱንና ጭንቀቱን ተረግጣ እንደ ጧት ፀሐይ በሐሳቡ ብቅ ስትል ፀፀቱና ፍርሃቱ ለጊዜው ትቶት ገለል ይላል ። ለሕሊና ወቀሳና ለመባነን ጉሮ ዳርጎኝ ጠፋ የሚለውን ወንጀሉን መልሶ ይወደዋል ። ይኸኔ ራሱን መጥላት ይተዋል ። ዓለምን መጥላት ይተዋል ። ሰዎችን ሁሉ መጥላት ይተዋል ። 'ይነቃብኛል ወይስ አይነቃብኝም?' የሚለው ሥጋት ይወገድለታል ።

ብርቅነህ ፥ ጧቱን በድብልቅልቅ ስሜት ተውጦ አረፈዱ ። ደስታ ይሁን ኀዘን ፥ ቅሬታ ይሁን ፍርሃት ለይቶ ያላወቀው ስሜት ወጥሮ ሲይዘው ጊዜ ፥ ወደ አቶ ስሞን ቤት ሒዶ ሊያነጋግራቸው አሰበ ። ምንም ያህል ሳይቆይ ደግሞ የመሔዱ ነገር አስጠላው ። ከጭንቀት ጋር የሚያደርገውን ትግል ስላልተረዱለት የቡና ቤቱን ሴቶች ጠላቸው ። ውስጡን ይርበዋል ። ግን ደግሞ ቁርስ ሲቀርብለት አይበላለትም ።

ወደ አቶ ስሞን ቤት ሒዶ የሱ ልትሆንም ላትሆንም የምትችለውን ልዕልትን ከማየት በስልክ ቢያነጋግራቸው

እንዴሚሻል መረጠ ። ደወለላቸው ። ከዚያም የተላከበት ጉዳይ እንዴ ተሳካለት ነገራቸው ። የገቡለትን ቃል እንደግያቱ በድ ጋሚ ነገሩት ። አመስግና ስልኩን ዘጋው ። በብስጭት ወይም በብስጭት ያላለፈው ጧቱ ቆጨው ። ከዚያም ደስ እንዳለው ዋለ ። ሴቱንም ያለ ብዙ ቅሥት አሳለፈው ።

በነጋታው ከስዓት በኋላ ፥ አቶ ስሞን የቡና ቤቱን ሒሳብ ተቂጣጥረውና ተረከበው ሲያበቁ ከብርቅነህ ጋር ወደ ቢሮአቸው ገቡ ።

"ሽጥጡን መውሰዱን አመነ?" ብሎ ጠየቃቸው ።

ሽጥጡን ብቻ ሳይሆን እየሰረቀ የሸጠውን ሁሉ ተናዘዘ ። ሁሉንም ትናንት እነግርሃለሁ ብየ ነበር ። ከባለቤቴ ጋር ስለተጣላን ጭቅጭቅ ገጥሞኝ ነው የቀረሁ" አሉት ። ብርቅነህ የጠቡ መነሻ እሱ መሆኑ ገባው ።

"በምን ተጣላችሁ ጌታዬ?" አለ ፥ ቅሬታውንም ለመግለጽ እየሞከረ ። ዋናው ያሳሰበው ግን የልዕልት ጉዳይ ነበር ።

"የቡና ቤቱን ገቢ እጥፍ ያሳደግከውንና ኤጥሮስንም ከጥሩት ጎዳና የመለስከው መሆኑን ከጠቀስኩላት በኋላ ፥ ልዕልትን ልድርልህ እንዳሰብኩ ገለጥኩላት ። ይኸኔ በቁጣ ጮራች ። 'የፈለገው ነገር ይመጣል እንኚ ልጇን ላሽከር አልድራትም' ብላ ደነፋች ። እኔም እንተያያለን ብያት ጉዳዩ ለጊዜው በዚህ አበቃ ። ቃሉን እንደማላጥፍ ግን አትጠራጠር !"

"ስለ ግድያው የሰሙት ወሬ የለም?"

"ትናንት ጧት እንዱ የኤጥሮስ ጓደኛ ስልክ ደውሎ በቀለ መገደሉን ነገረው ። ጓደኛቹም መታፈሳቸውንና እሱም መጠን ቀቅ እንዳለበት ነገረው ። ከዚህ ሌላ የሰማሁት የለም ። ኤጥሮስም ከቤት እንዳይወጣ ከልክየዋለሁ ።"

"እንግዲህ ታልዎን የማያጥፉ ከሆነ ሐሳቤ ተሳካ ማለት ነው ። ግን እሜቴ ከተቃወሙ ምን ማድረግ ይቻላል?" ሲል በትሕትና ጠየቃቸው ።

"ግድ የለም ፣ እንደ ምንም አግባባታለሁ ። እምቢ ካለችም እኔው አጫርሰዋለሁ ። ሠርጉ ይቀራል እንጂ መጋባታችሁ አይቀርም" አሉት ።

ያቶ ስሞን ቃል ፣ ብርቅነህን ሳምንት ሙሉ በደስታ አሰከረው ። ውስጥ ለውስጥ የተጠነሰሰው ደስታ እየገነፈለ በማያሥቀው ሁሉ ሲሥቅ ፣ በማያሳዝነው ሁሉ ሲያዝን ሰንበተ ። የደስታውን ምንጭ ከሱ በቀር ቡና ቤቱ ውስጥ ያወቀ አልነበረም ። የጠየቀውም አልነበረም ። አቶ ስሞን ብቻ ሒሳብ ለመረከብ ሲመጡ በፈገግታ ያነጋግሩታል ። ጉዳዩን ሲያነሣባቸውም ፣ "እይዞህ አታስብ" ይሉታል ። ከሚስታቸው ጋር ጠባቸው እየከረረ ቢሔድም ፣ የሰጡትን ቃል እንደማያጥፉ በየጊዜው ያረጋጡለታል ።

ልክ በሳምንቱ ፖሊሶች ፣ አቶ ስሞን ቤት መጥተው ጴጥሮስን ወሰዱት ። ብርቅነህም ተፈልጎ ታሰረ ። ይህ የሆነው በቀለ በሞተ በሳምንቱ ነው ። የበቀለ ጓደኞችና እትንጂ ቡና ቤት ለቁማር የሚመጡ አንዳንድ ጎረምሶች በጥርጣሬ ታፍሰው ሲመረመሩ ፣ አንድ ተደብቆና ተረስቶ የነበረ የግድያ ወንጀል መፈጸማቸውን ለፍልፈው ጴጥሮስንም ግብረ አበር ነው ብለው መሩበት ። ጴጥሮስ ታሰረ ።

አቶ ስሞን እሱን ለማስፈታት ሲሯሯጡ ባለቤታቸው ከወንድሞቻቸው ጋር ተማክረው ልዕልትን ወደ እንግሊዝ አገር ላኳት ።

344/2000

‘ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ ፤
አገርም እንደ ሰው ይናፍቃል ወይ ?’

ከሚለው የዘፈን ግጥም ርዕሷ የተወሰደውና ፥ ለዚች መጽሐፍ ርዕስ የለገሠችው ፥ አሞር ልቦለድ ብቻ ከዚህ ቀደም በ‘የካቲት’ መጽሔት የታተመች ሲሆን ፥ ሌሎቹ ግን በዚህ ‘ስብስብ’ ሥራ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሕትመት ብርሃን ያገኙ ናቸው ።

ወጣቱ ደራሲ አውጣቸው ተረፈ ፥ ለአጫሞር ልቦለዶች አፍታሪያን የማይታወቅ ባይሆንም ፥ ሥራዎቹን ስብስብ አድርጎ ባንድነት ሲያቀርብ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነው ።



ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
ዋጋው ብር 2.25
ቦሌ ማተሚያ ቤት